# ልጆችን ማስተማር
## 1ኛ ክፍል

**የሩሂ ተቋም**

**መጽሐፍ 3**

ሩሂ መጽሐፍ 3: ልጆችን ማስተማር

Ruhi Book 3: Teaching Children's Classes – Grade 1

ተዘጋጀ፤ በሩሂ ኢንስቲትዩት - ኮሎምብያ
ትርጉም፤ ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ በሳብሪ የልማት ተቋም- አዲስ አበባ

© የአዘጋጁ መብት የተጠበቀ ነው::

Copyright ® 1987 by the Ruhi Foundation, Columbia
All rights reserved.

Second Amharic Edition 2007
Publisher: Baha'i Publishing Board of Ethiopia.

በአዘጋጁ ፈቃድ በኢትዮጵያ ባሃኢዎች ብሔራዊ የህትመት ቦርድ በድጋሜ ታተመ::
መጋቢት 1999 ዓ.ም. አዲስ አበባ ::
ፓ. ሣ. ቁ. 102 አዲስ አበባ

# ማውጫ

ለተባባሪዎች ........................................................................ 1

ስለትምህርት ጽንሰ -ሃሳብ ጥቂት የባሃኢ መመሪያዎች ...................... 4

የአንደኛ ክፍል የልጆች ትምህርቶች ............................................. 23

የልጆች ትምህርትን በብቃት መምራት ......................................... 81

# ለተባባሪዎች

ይህ መጽሐፍ ሦስት ክፍሎችን ይዟል:: እነዚህም ክፍሎች ቋሚ መንፈሳዊ ትምህርት ለልጆች የመስጠትን እጅግ ምስጉን ግልጋሎት ለማበርከት የሚሹ ግለሰቦችን ለመርዳት የታለሙ ናቸው:: ይህንን መጽሐፍ ለማጥናት የሚፈልጉ ተሳታፊዎች በቅድሚያ ቢያንስ የሩሂ ተቋም አንደኛውን መጽሐፍ ማጥ ናት ይኖርባቸዋል::

የሩሂ ተቋም የልጆች ትምህርት ላይ ከፍተኛ ትኩረት የሰጠው በስፋት የባሃኢ እምነትን በተቀበሉ አካባቢዎች በተለይ በገጠርና ከተማ ቀመስ በሆኑ መንደሮች ያሉ ባሃኢዎች ልጆቻቸውን በባሃኢ የትምህርት ስርዓት መሠረት እንዲማሩላቸው ያላቸውን ጽኑ ፍላጎት በሚገባ ስላስተዋለ ነው:: ለዚህ ምክንያታዊ ለሆነ ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት በቂ መምህራን አለመኖራቸው ግን የሚያሳዝን ነው:: ይባስብሎ ሕፃናትን የማስተማር ብቃት ያላቸው ብዙ ባሃኢዎች በተለያዩ ምክንያቶች የአዲሱ ትውልድ ተስፋ ለሚወሰንበት ለዚህ የአገልግሎት ተግባር በቂ ትኩረት ሊሰጡት አልቻሉም::

የባሃኢ የልጆች ትምህርቶች የሃይማኖት ሥርዓቶችን በትጽእኖ እንዲማሩና እንዲቀበሉ ለማድረግ የታለመ አለመሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል:: ምንም እንኳን የባሃኢ ሃይማኖትን መንፈሳዊ መመሪያዎችና ትምህርቶች እንዲማሩ ቢደረግም ትኩረት የሚሰጠው ግን ሕፃናት ማሰብን፣ማሰላሰልንና መንፈሳዊ ሕግ ጋትን በተግባር ማሳየትን እንዲማሩ ማድረግ ላይ ነው:: በተለይ በልጅነት የመጀመሪያዎቹ ዓመታት መንፈሳዊ ባህሪያትን ማዳበርና አንድ መንፈሳዊ ሰውን ሊያስጌጡ ለሚገቡ እምነቶች፣ ልማዶችና ባህሪ ያት ትኩረት መስጠት ተገቢ ነው::

የሃይማኖት ሥርዓቶችን በትጽእኖ እንዲተገብሩ የሚደረግበትን የሃይማኖት ትምህርት ማስወገድ አለብን ስንል የሃይማኖት መንፈሳዊ ትምህርትን ችላ ማለት አለብን ማለት አይደለም:: ሃይማኖታዊ ትምህ ርትን ችላ በማለት ህፃናት ከህብረተሰቡ ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት የራሳቸውን አመለካከትና እምነት እንዲያዳብሩ በነፃነት ስም ልቅ መተው በዚህ ዘመን በስፋት ለሚታየው የሞራል ውድቀት ትልቅ አስተዋጾ አድርጓል:: ቀጣዩ ትውልድ መሰረቱ መንፈሳዊ የሆነ ትምህርት ሳይቀስም የተሻለ ዓለም ይገነባል ብሎ ለመገመት የሚያስችል ምክንያት የለንም:: የሰው ልጅ ያለ መለኮታዊ መርሐ በዘፈቀደ በሚኖርበት ጊዜ ከብጥብጥ፣ ከፍትሕ-አልበኝነትና ከስቃይ በስተቀር ሌላ አያተርፍም::

ምንም እንኳን በመላው የዓለም ባሃኢዎች ዘንድ በባሃኢዎች ዓለም የህፃናት ትምህርት የሚካሄ ድበት መንገድ እንደየማሕበረሰቡ የተለየ ቢሆንም ተግባሩ አስፈላጊ መሆኑ ላይ ግን ሁሉም ሊስማሙ የሚችሉበት ጉዳይ ነው:: በተጨምሪም ብዙ ቁጥር ላላቸው ሕጻናት መንፈሳዊ ትምህርት ለመስጠት ለሚደረግ እቅድ መሳካት ቁልፉ የሕፃናት አስተማሪዎችን ማሰልጠን ነው:: የባሃኢ ተቋማት፣ በተለይም ብሔራዊና ክልላዊ የስልጠና ተቋማት ለማገልገል ፍላጎት ያላቸውና የሰለጠኑ የሕፃናት አስተማሪዎችን ለማበራከት ለሚያደርጉት ጥረት ይህ መጽሐፍ ከፍተኛ እገዛ ይሰጣል ብለን ተስፋ እናደርጋለን::

የዚህ መጽሐፍ የመጀመሪያ ክፍል "ስለትምህርት ጽንሰ-ሃሳብ ጥቂት የባሃኢ መመሪያዎች" በሚል ርዕስ የቀረበ ሲሆን ትምህርትን አስመልክቶ በቅዱሳን ጽሑፎች ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ መሰረታዊ ፅንሰ ሐሳቦችን ይዳስሳል:: በአሁኑ ጊዜ ወጥ የሆነ የባሃኢ የትምህርት አሰጣጥ ስልት፣ ተብሎ የሚታወቅ በዓለም ላይ የለም:: ወጥ የሆነ ስልት ወደፊት በተለያዩ ቦታዎችና ባሕሎች መካከል የሚሰሩ ብዙ የትምህርት ባለሙያዎች የረዥም ጊዜ ጥረትና ጥናት ካደረጉ በኂላ የማቀረጽ ይሆናል:: ይሁንና ሥርዓተ-ትምህርትን ለመገንባት የሚደረጉ ጥረቶችን ሊመሩ የሚገቡ አንዳንድ መመሪያዎችና ጽንሰ-ሐሳቦች ከ(የባሃኢ)ቅዱሳን ጽሑፎች ውስጥ እናገኛለን:: በዚህ ክፍል ውስጥ ከእነዚህ መካከል ጥቂቶቹን እንመረምራለን::

በክፍል አንድ ውስጥ ከተብራሩት ጽንሰ-ሐሳቦች መካከል ዋናው የሰው ክቡርነት ነው:: የልጆች አስተማሪ የሚሆኑት የዚህ ስልጠና ተካፋዮች ይህ እጅግ ወሳኝ የሆነ ጽንሰ-ሐሳብ በሚሰጡት ትምህርት ላይ የሚኖረውን ተጽዕኖ መረዳት አስፈላጊ ነው:: አንድ ተማሪ ወይንም ልጅ ልክ እንደማዕድን ሥፍራ በውስጡ በዋጋ ሊተመን የማይችል እንቁዎች አሉት:: ብሎ ማመን ወይንም ማሰብ ብቻ ለአንድ ጀማሪ የልጆች አስተማሪ ከተለመደው የመማር-ማስተማር ልምድ እንዲላቀቅና

የላቀ ደረጃ ላይ እንዲደርስ ይረዳዋል፡፡ ሆኖም ይህንን ጽንሰ-ሐሳብ መቀበል ብቻ በራሱ በቂ አይደለም፡፡ የልጆች አስተማሪዎች ስለመንፈሳዊ ባሕሪያት ምንነት ግንዛቤ መጨበጥ፣ ስለተሰጥኦና ችሎታ በቂ እውቀት ማግኘት ይገባቸዋል፡፡ ይህም በተማሪዎቻቸው ውስጥ ያሉትን እነዚህ እንቁዎችን ለማወቅና እንዲዳብሩም ለመርዳት ያስችሏቸዋል፡፡ ልጆች ከባሃኢ አኗኗር ጋር የሚስማሙ ልማዶችንና ባህሪዎችን እንዲያዳብሩ የመርዳት አስፈላጊነትንም ሊገነዘቡ ይገባል፡፡

ይህንን የሩሂ ተቋም ሦስተኛ መጽሐፍ በቀላሉ ለመረዳት በሌሎች የሩሂ ተቋም መጽሐፍት ክፍሎች እንደሚደረገው በዚህም ክፍል ውስጥ ያለው ትምህርት የሚሰጠው በመማማር መልክ ነው፡፡ መማማሩም ውጤታማ እንዲሆን ተሳታፊዎቻችን በቡድን መከፋፈልና እያንዳንዱ ቡድንም በራሱ ፍጥነትና ስልት እንዲሄድ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ አንዳንዶቹ ከሌሎቹ እኩል እንዲሄዱ ማጣደፍ የትምህርት ሂደቱን ስለሚያሰናክለው መጠንቀቅም ይገባል፡፡ በዚህ ረገድ አስጠኚው ፈጣን የመረዳት ችሎታ ያላቸውንና በዝግታ የመረዳት ችሎታ ያላቸውን ለመርዳት የሚኖረው ሚና ተመጣጣኝ መሆን ይኖርበታል፡፡ አስጠኚው ከእያንዳንዱ የአጥኝዎች ቡድን ጋር በመሆን በሁሉም ምዕራፎች ላይ ውይይት ማድረግ አለበት፡፡ የሩሂ ተቋም ትምህርቶች ተሳታፊዎች ለየብቻቸው ቢያጠኗአቸው የሚበቃ ተደርገው ሊወሰዱ አይገባም፡፡ በየምዕራፎቹ ውስጥ የተሰጡትን ሐሳቦች በሦስቱ የመረዳት ደረጃዎች መሰረት እንዲረዷቸው ከተፈለገ ከአስጠኚው ጋር አብሮ በመሆን መወያየት ያስፈልጋል፡፡ እነዚህ ሦስት የመረዳት ደረጃዎችም የቃላትና የዓረፍተ-ነገሮቹን ትርጉም መረዳት፣ ፅንሰ-ሐሳቦቹ በእለት ተእለት ሕይወታችን ውስጥ በተግባር እንዴት እንደሚንፀባረቁ መገንዘብና የጽንሰ-ሀሳቦቹን ተዛማጅ ወይንም ድብቅ የሆነ ትርጉማቸውን መረዳት ናቸው፡፡ ስለ እነዚህ ሦስት የመረዳት ደረጃዎችና ተሳታፊዎችም እንዲካኗቸው እንዴት ለመርዳት እንደሚችሉ የበለጠ እንዲብራራልዎ የሚፈልጉ ከሆነ ሩሂ አንደ ውስጥ "ለተባባሪዎች" በሚል ርዕስ የቀረበውን መግቢያ ያንብቡ፡፡

ሁለተኛው ክፍል "የአንደኛ ክፍል የልጆች ትምህርቶች" በሚል ርዕስ የአንደኛ ክፍል የባሃኢ ልጆች አስተማሪዎችን ለማሰልጠን የተዘጋጀ ነው፡፡ ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ አስተማሪዎች ፍሬያማ የልጆች ትምህርት ለማካሄድ የሚያስችሏቸውን ዘዴዎች ያስጨብጣል፡፡ ይህ ክፍል በተጨማሪም 15 የልጆች ክፍለ-ትምህርቶችንም ይዟል፡፡ እያንዳንዱ ክፍለ-ትምህርት አምስት የትምህርት እንቅስቃሴዎች አሉት፡፡ እነዚህም የጸሎቶችና ጥቅሶች የቃል ጥናት፣ መዝሙሮች፣ ታሪኮች፣ ጨዋታዎችና ስዕሎችን መቀባት ናቸው፡፡ ለሕፃናቶቹ በዓመት ውስጥ ሁለት ወይንም ሦስት ጊዜ በመደጋገም ትምህርቶቹን እንዲያስተምሩ ይመከራሉ፡፡ ይህን ካደረጉ በአንድ ዓመት ውስጥ ከ 30-45 የትምህርት ክፍለ-ጊዜዎች ይኖሮታል ማለት ነው፡፡

- የዚህ ስልጠና ተሳታፊዎች ስለትምህርቱ እቅዶችና ትምህርቶቹን ለሕፃናቱ ስለሚያስተላልፉባቸው መንገዶች በቂ እውቀት እንዲጨብጡ አስጠኚው በሚረዳቸው ጊዜ የሚከተሉትን ቁልፍ ነጥቦች መርሳት የለበትም፡-

- የልጆች ትምህርትን ለማካሄድ የሚያስፈልገውን ችሎታ ለማዳበር ከተፈለገ በጣም ብዙ ልምምዶችን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በዚህም ምክንያት ይህ ስልጠና ረዥምና አንዳንድ ጊዜም አስቸጋሪ እንደሚሆን መርዳት ያስፈልጋል፡፡ ትምህርቶቹን ማንበብና ይዘታቸ ውን መረዳት የሕፃናት ትምህርትን ለማካሄድ በቂ አይደለም፡፡ ከስልጠናው በኋላ አስተማሪ የሚሆኑትን ተሳታፊዎች በስልጠናው ጊዜ የሕፃናት ትምህርት የመስጠት ልምምድ እንዲያደርጉ አስጠኚው በቂ ሰዓት መመደብ አለበት፡፡

- አብዛኛዎቹ አስተማሪዎች ልጆች በነበሩ ጊዜ አስተማሪዎቻቸው ባስተማሯቸው መንገድ እነርሱም ልጆችን ለማስተማር ይፈልጋሉ፡፡ ይህንን ለመከላከል አስጠኚውና ተሳታፊዎቹ ጥልቅ አትኩሮቶቻቸውን ሊሰግሷቸው የሚገቡ ዝርዝር ምክሮች በዚህ ክፍል ውስጥ ተካተዋል፡፡

- የልጆች ትምህርቶቹ ልጆች ወደ አምላክ እንዲቀርቡ የሚያደርጋቸው አመለካከቶችንና መንፈሳዊ ባህሪያትን እንዲያዳብሩ የሚረዱ መሳሪያዎች እንዲሆኑ ተስፋችን ነው፡፡ የአንደኛ ክፍል የልጆች ትምህርቶች ያተኮሩት በመንፈሳዊ ባህሪያት ላይ ነው፡፡ ስለእምነቱ አጠቃላይ እውቀት በመስጠት ላይ ትኩረት አልተሰጠም፡፡ ሕፃኑ የመልካም ባሕሪ መሠረት ከጣለ በኋላ አስፈላጊውን የእምነቱ እውቀት በቀጣዮቹ ዓመታት ሊሰጠው ይችላል፡፡

- የልጆች ትምህርቱ የሚካሄድበት ዘዴ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ያካተተ ነው፡፡ ሁሉም እንቅስቃሴዎች ያነጣጠሩት ግን መንፈሳዊ በሕሪያትንና አመለካከትን በማዳበሩ ዋና ዓላማ ላይ ነው፡፡ ዋነኛ አትኩሮታቸውም መንፈሳዊ መነቃቃትን በሕጻናቱ ውስጥ ለመፍጠር በሚችለው ብቸኛ ኃይል በሆነው በአምላክ ለዋጭ ቃል ዙሪያ ነው፡፡ ስለዚህም ለዋጩን የአምላክ ቃል በቃል መያዝ ላይ ጥብቅ ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡ በቃል የሚያዘውን በሚገባ መረዳት ከተቻለ የቃል ጥናት እጅግ የበለጠ ፍሬ ያሳያል፡፡ ለዚህም ሲባል እያንዳንዱ ትምህርት ሕጻናት የጥቅሱን ትር ጉም ለመረዳት እንዲችሉ የሚያግዙ አስረጂ ምሳሌዎችን ይዟል፡፡ በቃል እንዲያዙ የተመረጡ ጥቅሶች ውስጥ የሚገኙ ሐሳቦችን የሚያጠናክሩ መዝሙሮች፣ ጨዋታዎችና ታሪኮች ግን በብዛት አላዘጋጀንም፡፡ ይሁንና ወደፊት እንደዚህ ዓይነት መርጃዎች በብዛት እንደሚዘጋጁና ተሰባስበውም ለባሃኢ ልጆች ማስተማሪያ እንደሚውሉ ተስፋ እናደርጋለን፡፡

- አብዱል-ባሃ የባሃኢ ህይወት አርአያ በመሆኑ በትምህርቶቹ ውስጥ የተካተቱት የእርሱ ታሪኮች በጣም ትልቅ ጠቀሜታ አላቸው፡፡ ምክንያቱም ህፃናት ለሚማሯቸው መንፈሳዊ ባህሪያት ተጨባጭ ምሳሌዎች ናቸው፡፡ልጆች ረቂቅ ስለሆኑ ነገሮች ሲማሩ ተጨባጭ የሆኑ ምሳሌዎች ቢቀርብላቸው በቀላሉ ሊረዱ እንደሚችሉ የታወቀ ነው፡፡ ልጆችን በሚስብ መንገድ ታሪኮችን መናገር የሚቸገሩ ተሳታፊዎች ይኖሩ ይሆናል፡፡ የልጆችን ስሜት የሚይዝ ክፍሎችን ማስታወስና ታሪኩን እንዲጥም አድርጎ መናገር ለመቻል ከተፈለገ ዘወትር ልምምድ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

- በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ለተካተቱት የልጆች ትምህርቶች ከአቅም በላይ የሆኑ የማስተማሪያ መሳሪያዎች አያስፈልጉም፡፡ መምህሩ ከጥናቱ ከገበየው እውቀት በተጨማሪ የሚያስፈልገው በክፍለ- ትምህርቱ ውስጥ የተካተቱትን ስዕሎች መቀቢያ የቀለም እርሳስ ነው፡፡ ስዕሎቹን በተማሪዎቹ ብዛት ልክ ለማባዛት ከተፈለገ ነጭ ወረቀት በመጠቀም በእርሳስ በመረሰስ ኮፒ ሊያደርግ ይችላል፡፡

- በስልጠናው ጊዜ ተሳታፊዎች ያገኙዋቸውን አዳዲስ ችሎታዎች (ክህሎቶቸ) በተግባር ላይ ማዋል ቢጀምሩ መልካም ነው፡፡ ይህም እራሳቸውን ችለው ሕፃናትን በሚያስ ተምሩበት ጊዜ ስለሚያዘጋጃቸው ይጠቅማቸዋል፡፡ አዲስ አስተማሪዎች ለመጀመሪያ ጊዜ በርካታ ሕፃናት ፊት ሲቆሙ ይደናገጡ ይሆናል፡፡ ስለዚህ አዲስ አስተማሪዎች በቅድሚያ ልምድ ካላቸው አስተ ማሪዎች ጋር በመሆን አልያም ቁጥራቸው ትንሽ የሆኑ ህፃናትን በማስተማር እንዲጀምሩ ይመከራል፡፡

- በትምህርቶቹ ውስጥ የተጠቀምንባቸውን መዝሙሮች የያዘ ካሴት ከዚህ መጽሐፍ ጋር ይገኛል፡፡ አስተማሪዎች እራሳቸውን ለትምህርቱ ለማዘጋጀትም ሆነ መዝሙሮቹን ለሕፃናቱ ለማስተማር እንዲችሉ ካሴቱን መጠቀም ይፈልጉ ይሆናል፡፡

የሩሂ ተቋም የልጆች አስተማሪዎችን ለማሰልጠን ያደረጋቸው የመጀመሪያዎቹ ጥረቶች ሲገመገሙ የልጆችን ትምህርት እንዴት ማቀናጀትና መምራት እንደሚቻል የሚያስተዋውቅ ኮርስ እንደሚያስፈልግ ግልጽ ሆነ፡፡ ይህ ኮርስ በተለይ የልጆች ትምህርትን እንደልዩ እምነቱን የማገልገል መስክ አድርገው ለመረጡ አማኞች አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ “የልጆች ትምህርትን በብቃት መምራት” በሚል ርዕስ የታቀፈው የመጨረሻው ክፍል ይህንን ፍላጎት ለማሟላት የተዘጋጀ ነው፡፡ እንደ ሌሎቹ ክፍሎች ተሳታፊዎች በትንንሽ ቡድኖች በመሆን ይህንን ክፍል ማጥናት አለባቸው፡፡ እያንዳንዱን ምዕራፍ አንድ ወይም ሁለት ጊዜ ጮክ ተብሎ ከተነበበ በኋላ በዚያው ላይ ተሳታፊዎቹ ይወያዩባቸው፡፡ ዋነኛው የሆነ የዚህ ክፍል ዓላማ በአንድ በኩል በደስታና በፍቅር የተሞላ፣ በሌላ በኩል ጨዋነትን በእጅጉ የተላበሰ የትምህርት ክፍለ-ጊዜን ለማስፈን የሚያስፈልገውን የመጠነኛነት (ጥብቅነትንና ቸልተኝነትን ያስወገደ) ግንዛቤ ለተሳታፊዎቹ ማስጨበጥ ነው፡፡ ልጆች ቅጣትን ከመፍራት የተነሳ በተጽዕኖ ሥርዓትን ሊጠብቁ ይችላሉ፡፡ መንፈሳዊ ጨዋነት ግን በተፅዕኖና በፍራቻ ሳይሆን ከአምላክ ፍቅርና በእርሱም ከመተማመን የሚመነጭ መሆን ይገባዋል፡፡ ሩሂ ሦስትን ሲያጠኑ የልጆች አስተማሪዎችም በተማሪዎቻቸው ውስጥ ይህንን ፍቅርና አመኔታ የማሳደር ችሎታ ሊያዳብሩ ይገባል፡፡

## ስለትምህርት ጽንሰ - ሃሳብ ጥቂት የባሃኢ መመሪያዎች

### ዓላማ

ስለልጆች ትምህርት መሠረታዊ መመሪያዎች ከባሃኢ ቅዱሳን ጽሑፎች መረዳት

## ምዕራፍ 1

የባሃኢ የልጆች ትምህርት ይዘት ማንኛውም ፍላጎት ያለው ሰው በአንድ ማኅበረሰብ የሚገኙ ጥቂት ሕፃናትን ሰብስቦ በየሳምንቱ የሚሰጧቸው ትምህርቶች ናቸው። በትምህርቱ ክፍለ ጊዜዎች ሕፃናት ፀሎቶችንና ከቅዱሳን ጽሑፎች የተገኙ ጥቅሶችን በቃላቸው ይይዛሉ። ታሪኮችንና ስለትምህርቶቹ ቀላል ማብራሪያዎችን ያዳምጣሉ፣ይዘምራሉ ይጫወታሉ።

የዚህ ክፍል ዓላማ እርስዎ የልጆች አስተማሪ ለመሆን የሚያስችሎዎትን አቅም እንዲያዳብሩ ለመርዳት ነው። እርስዎ የባሃኢ ልጆች አስተማሪ በመሆን ሥራዎን ለመጀመር በጣም እየጓጉ እንደሆነ ጥርጥር የለውም። ስለዚህ ይህንን ክፍል በጥንቃቄ ማጥናትና ይዘቶቹም ላይ ማሰላሰል ይኖርብዎታል።

ከዚህ በታች የተሰጡትን የባሃኡላህና የአብዱል-ባሃን ጥቅሶች በማጥናት የልጆች አስተማሪነት ግልጋሎት ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ ይገነዘባሉ። እነዚህን ቃላት በቃል ቢይዟቸውና ልጆችን በሚያስተምሩም ጊዜ ቢያስታውሷቸው ይጠቅምዎታል።

> "...ያ ሕፃናትን ለማስተማር የሚነሳ አስተማሪ የተባረከ ነው።" [1]

> " ኃያሉ አምላክ በሰው ሲሰጡ ከሚችሉት እጅግ በጣም ታላላቅ አገልግሎቶች ሁሉ መካከል አንዱ የልጆች ትምህርትና ሥልጠና ነው" [2]

" በግልጹ መለኮታዊ ጽሑፍ መሰረት፤ ልጆችን ማስተማር ማስቀረት የማይቻልና ግዴታም ነው። ልክ ከስግደት ጋር አንድ የሆነውን ፤ ይህንን ግዳጅ ለማከናወን ስለተነሱ፣ አስተማሪዎች የጌታ የአምላክ አገልጋዮች ናቸው ማለት ነው። ስለዚህ መንፈሳዊ ልጆችህን በማስተማር ላይ ስለሆንክ በተነፈስክ ቁጥር ምስጋና ማቅረብ አለብህ።" [3]

### 1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልሱ:-

ሀ. ሰው ለኃያሉ አምላክ ሊያበረክታቸው ከሚችላቸው ታላቅ ግልጋሎቶች አንዱ ምንድን ነው?

____________________________________________________

ለ. ሕፃናትን ማስተማር አስመልክቶ የባሃኢ ጽሑፎች ምን ይላሉ? ____________________

____________________________________________________

____________________________________________________

ሐ. ሕፃናትን ለማስተማር ከመነሳት ጋር አንድ የሆነው ምንድን ነው? ________________

____________________________________________________

____________________________________________________

### 2. የሚከተሉት አረፍተ-ነገሮች እውነት ወይም ሐሰት መሆናቸውን ይለዩ:-

ሀ. በባሃኢ እምነት ልጆችን ማስተማር ግዴታ ነው። እ ☐ ሐ ☐

ለ. ልጆችን ስናስተምር አምላክን እያመለክን ነው። እ ☐ ሐ ☐

ሐ. አብዛኞቹ ልጆች ትምህርት ቤት ሄደው የሚማሩ በመሆናቸው እኛ ባሃኢዎች ሕፃናትን ለማስተማር የግድ ማሰብ የለብንም::  እ ☐  ሐ ☐

መ. ልጆችን ስታስተምር መንፈሳዊ ልጆችህን እያፈራህና እያሳደግክ ነው  እ ☐  ሐ ☐

ሠ. አስተማሪዎች የጌታ እግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸው::  እ ☐  ሐ ☐

# ምዕራፍ 2

የባሃኢ እምነት ጽሑፎችን በምናጠናበት ጊዜ ጥራትና ብቃት ያለው ትምህርት እንዴት ልንሰጥ እንደምንችል የሚጠቁሙንን ምክሮችንና መመሪያዎችን እናገኛለን:: ከእነዚህ ትምህርቶች አንዱ አስተማሪዎች ለተማሪዎቻቸው ሁሉ ሊያሳዩ ከሚገባቸው የፍቅርና ተማሪዎቻቸውን የመረዳት አመለካከት ጋር የተያያዘ ነው:: ተማሪዎችም እንዲያስተምሯቸው ብቻ የተሰበሰቡ እንደማንኛውም ሰው ሳይሆኑ በእርስዎ ዘንድ በጣም ልዩ ቦታ ያላቸው ሊሆኑ ይገባል:: እያንዳንዱ ተማሪ የራሱ በሆነ ተሰጥኦና ችሎታ የተሞላ ልዩ የአምላክ ፍጡር ነው:: በሌሎች ምዕራፎች እነዚህ ተሰጥኦዎች ምን እንደሆኑ እንነጋገርባቸዋለን:: ለአሁኑ ግን ሁሉም ሰው የአምላክን ክስተቶች የማወቅ፣ ሕግጋቶችንም የመታዘዝ በመንፈስ የማደግ ችሎታ እንዳለው መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው:: ሁሉም ልጆች ጥሩ ሲሆኑ መንፈሳዊ ባሕሪያትንም ሊያዳብሩ ይችላሉ::

የሰው ልጆች ሁሉ ክቡር ሆነው መፈጠራቸው በልብዎ የተረጋገጠ ይሁን:: በትምህርት ክፍለ ጊዜዎችም ተማሪዎችዎ ይህንን ክቡርነት እንዲያንጸባርቁ ሊረዷቸው ይችላሉ::

**1. ከላይ ባጠናነው ምንባብ ላይ የተመሰረቱ ጥቂት ሐረጎች ከዚህ በታች ተሰጥተዋል:: ይሁንና አንዳንድ አስፈላጊ ቃላትና ሐረጎች ተዘለዋል:: እነዚህን የተዘለሉ ቃላትና ሐረጎች በባዶ ቦታው ውስጥ ይሙሉ::**

- አስተማሪዎች ለ ______________________ ሁሉ ሊያሳዩዋቸው የሚገቡ የፍቅርና ተማሪዎቻቸውን የ____________________ አመለካከት በጣም አስፈላጊ ነው::

- አስተማሪዎች ለተማሪዎቻቸው ሊያሳዩ የሚገባቸው የ______________እና ተማሪዎቻቸውን የመረዳት አመለካከት በጣም ____________________ነው::

- እያንዳንዱ ተማሪ የራሱ በሆነ___________________ እና የተሞላ ልዩ የአምላክ ፍጡር ነው:: ሆኖም ____________________የአምላክን የማወቅ፤ _______________ የመታዘዝና በ_____________ የማደግ ችሎታ አለው::

- ______________________ የአምላክን ______________________ ሕግጋቶችቸውንም____________ በመንፈስም____________ችሎታ አለው::

- ተማሪዎችዎ እንዲያስተምሯቸው ብቻ የተሰበሰቡ እንደ ____________ ሳይሆኑ በእርስዎ ዘንድ በጣም____________________ያላቸው ሊሆኑ ይገባል::

- አስተማሪዎች ለ ____________ሊያሳዩ የሚገባቸው የ ______________እና ____________________አመለካከት በጣም አስፈላጊ ነው::

- ተማሪዎችዎ በእርስዎ ዘንድ በጣም ____________________ያላቸው ሊሆኑ ይገባል::

- እያንዳንዱ ተማሪ የራሱ በሆነ________________እና __________የተሞላ ልዩ የአምላክ______________________________ ነው::

- ሁሉም ሰው የአምላክን ክስተቶች የ____________________፤ ሕጋቶቻቸውንም የ ____________እና በመንፈስም የ________________ ችሎታ አለው::

- ሁሉም ሕፃናት ______________________ ሊሆኑ፤ _____________ ________ሊያዳብሩ ይችላሉ ::

- የሰው ልጆች ሁሉ________________መፈጠራቸው ______________ ይሁን:: በትምህርት ክፍል ጊዜዎችም ተማሪዎችዎ ይህንን ክቡርነት ____________ ይችላሉ::

2. በዚህ ምእራፍ ካጠናችሁት ውስጥ ዋነኛ ናቸው የሚሏቸውን ሁለት ነጥቦች/ ሃሳቦች ከዚህ በታች ይፃፉ:: ለምን እንደመረጧቸውም ያስረዱ::

______________________________________________________

______________________________________________________

______________________________________________________

______________________________________________________

## ምዕራፍ 3

**አሁን ደግሞ ከዚህ በታች የተሰጠውን የባሃኡላህን ጥቅስ ያንብቡና ቀጥለው የተሰጡትን ባዶ ቦታዎች በተገቢዎቹ ቃላትና ሐረጎች ይሙሉ::**

**"ሰውን ዋጋው ከግምት በላይ የሆኑ ዕንቁዎች እንዳሉበት የማዕድን ሥፍራ ቁጠሩት:: ሃብቱን እንዲገልጽ ሊያደርገው የሚችለው፤ የሰውንም ዘር ከዚያ ስመጠቀም የሚያስ ችለው ትምህርት ብቻ ነው::" [4]**

*ባሃኡላህ የሚያስተምረን፣ ሰውን ዋጋው ___________ የሆኑ___________*

*እንዳሉበት ___________ ቁጠሩት:: ሃብቱን ___________*

*ሊያደርግ የሚችለው ___________ ከዚያ ለመጠቀም የሚያስችለው*

*___________ ብቻ ነው::*

## ምዕራፍ 4

*ከላይ የተሰጠውን የባሃኡላህን ጥቅስ በቃልዎ ይያዙና ከዚህ በታች በተሰጡት ጥያቄዎች ላይ ያሰላስሉ:: የእኛ ከሆኑት ከእነዚህ እንቁዎች መካከል ጥቂቶቹ እነማን ናቸው? በውስጣችን ተደብቀው ያሉ እንደፍቅርና ደግነት፣ ፍትሃዊነት፣ እውነተኛነት፣ ታማኝነት፣ ፅኑነት፤ ሃቀኝነትና ቅንነት የመሰሉ መልካም ባህሪያት ከእነዚህ እንቁዎች ጥቂቶቹ ናቸውን? ስለሰው አእምሮና የቁሳዊውን ዓለም ምስጢራት ለማወቅ፤ ድንቅ የስነ-ጥበብ ስራዎችን ለመፍጠርና ውብና ክቡር ሐሳቦችን ለማመንጨት ስላለው ኃይል ምን ያስባሉ? እውነተኛ ትምህርት ያለመኖር ውጤት ምን ይሆናል? አምላክ የለገሰንን እነዚህን ሁሉ ሐብቶች ለማሳየት እንችል ነበርን?*

***በቡድንዎ ውስጥ ካሉ ተሳታፊዎች ጋር በመሆን በእነዚህ ሐሳቦች ላይ ይወያዩባቸው::***

## ምዕራፍ 5

*አስተማሪዎችን በሁለት ዓይነት ልንከፍላቸው እንችላለን:: አንዳንዶቹ ከላይ በቃልዎ በያዟቸው ቅዱሳን ቃላት የሚያምኑ ሲሆኑ ሌሎቹ ግን እነዚህን ቅዱሳን ቃላት ቀድሞውንም ያልተረዱ ናቸው:: እነዚህን ቃላት ያልተረዳ አስተማሪ ተማሪዎች ምንም እንደማያውቁና ለመማርም በጣም እንደሚቸገሩ ያምናል:: ይባስ ብሎ ደደቦች ናቸው ብሎ ሊያማርር ይችላል:: ተማሪዎቹን ቀስ በቀስ በእውቀት መሙላት እንደሚገባው እንደ ባዶ ብርጭቆዎች ያስባቸዋል:: እርስዎ ግን በአንፃሩ ተማሪዎችዎ በውስጣቸው በተደበቁ እንቁዎች እንደተሞሉ ያምናሉ:: የእርስዎም ድርሻ ተማሪዎችዎ እነዚህን የተደበቁ እንቁዎች እንዲከስቱ መርዳት እንደሆነ ተረድተዋል:: ለዚህም ነው በትምህርት ጊዜ ተማሪዎችዎ ንቁ ተሳትፎ እን ዲያደርጉ የተቻለዎትን ሁሉ ለማድረግ የወሰኑት:: ተማሪዎችዎ በውይይቶች እንዲሳተፉ ለማበረ ታታት፣ አስተሳሰባቸውን በጥሞና ለማድመጥና በባሃኦላህ ትምህርቶች አማካኝነት አምላክ የሰጣቸውን ችሎታዎች እንዲያዳብሩ ለመርዳት ቆርጠው የተነሱት::*

አንድ ሰው ሰላሳ ትልልቅ ገንዳዎችን በማንኪያ እየጨለፉ በውሃ እንዲሞሉ አዘዝዎት እንበል፡፡ ይህ የሚያስደስትዎ ስራ ይሆናልን? እንዲህ ዓይነቱን ስራ ሕይወትዎን ሙሉ እንዲያከናውኑ ቢታዘዙ ደስተኛ ይሆናሉን?

ዋጋቸው ሊተመን የማይችል እንቁዎችን የያዘ የማእድን ስፍራ ተሰጠዎ እንበል፡፡ በየእለቱ አዲስ የተደበቁ እንቁዎችን ከጉድጓዱ ውስጥ ፈልጎ ማውጣት ቢኖርብዎ ገንዳዎቹን በማንኪያ እየጨለፉ ከመሙላት የተሻለ አያስደስትዎትምን?

በዚህ መንገድ የባሃኡላህ ትምህርት በስራችን ላይ የሚኖረውን ተግባራዊነት በማጥናት ሕፃናትን ከመር ዳት በተጨማሪ የማስተማር ስራችንን የበለጠ እንድንወደው ማድረግ እንችላለን፡፡

# ምዕራፍ 6

ሕፃናት እምቅ የሆነ ተሰጥኦዎችና ችሎታዎች እንዳሉአቸው ተገንዝበናል፡፡ እስቲ አሁን "እምቅ" ስለሚለው ዋነኛ ቃል እናሰላስል፡፡ በመጀመሪያ ከቁሳዊ ነገሮች እንነሳ፡፡ ሻማ ብርሃን የመስጠት እምቅ (ወይም ድብቅ ችሎታ) አለው ማለት እንችላለን፡፡ ነገር ግን ይህን ስንል ያለምንም እገዛ እራሱን ችሎ ብርሃን ይሰጣል ማለት ነውን ወይስ ሊያቀጣጥሉት ያስፈልጋል? ብርሃን እንዲሰጥ ከፈለግን ሻማውን ማቀጣጠል እንደሚያስፈልግ ግልጽ ነው፡፡ ሆኖም ከመቀጣጠሉ በፊትም ብርሃን የመሰጠት እምቅ ችሎታ አለው፡፡ ሁሉም ቁሳዊ ነገሮች አንድ ዓይነት እምቅ ተፈጥሮ የላቸውም፡፡ ለምሳሌ ከእርሳስ ብርሃን ልናገኝ አንችልም፡፡ በሌላ በኩል ግን እርሳስም እምቅ የሆነ ግልጋሎት መስጠት የሚችል እምቅ አለው፡፡ ለመፃፍ ልንጠቀምበት እንችላለን፡፡ ሆኖም እርሳስን ካልቀረጽነው ሊጽፍ ይችላልን? ወይስ እርሳስ ያለውን የመፃፍ አቅም ከጥቅም ላይ ለማዋል መቀረጽ ይገባዋል?

አሁን ደግሞ የሕፃናት እምቅ ችሎታ እንመልከት፡፡ ከችሎታዎቻቸው መካከል ጥቂቶቹ ሕፃናት ያሏቸው ልዩ ተሰጥኦዎች ናቸው፡፡ አትሌት ሊሆን ይችላል፤ ሌላው ደግሞ እጅግ ጥዑም የሆነ ድምጽ ስላለው ዘፋኝ(ድምጻዊ) ሊሆን ይችላል፡፡ አንዱ በስነ-ጥበብ ዘርፍ ልዩ ተሰጥኦ ሲኖረው ሌላው ደግሞ በሳይንስ ልዩ ችሎታ እንዳለው የሚጠቁሙ ምልክቶችን ያሳያል፡፡ አንዳንድ ተማሪዎችዎ ከእነዚህ ሌላ ምን ተሰጥኦዎች ሊኖሯቸው ይችላል?

ባሃኢ አስተማሪ እንደመሆንዎ እያንዳንዱ ተማሪዎ ያለውን ተሰጥኦዎች ፈልጎ ማግኘትና እንዲዳብርም መርዳት ይኖርብዎታል፡፡ ሁልጊዜ ስለእያንዳንዱ ተማሪዎ ማሰብ፤ እንቅስቃሴዎቹን መከታተልና ልዩ ችሎታዎቹን ፈልጎ ማግኘት ያስፈልጋል፡፡ አንዳንድ ሕፃናት አስቸጋሪ ሆነው ያገኟቸው ይሆናል፡፡ ይሁንና ሕፃናትን መግራት ከፍተኛ የአገልግሎት ደረጃ እንደሆነ በመረዳ ትዎ ተግባሮዎን በፅናት ይወጣሉ፡፡ በዋነኛነት ከመንፈሳዊ ባህሪያት ጋር ቁርኝት ያላቸው ስጦታ ዎችና ተሰጥኦዎች ከሁሉም በላይ አስፈላጊ እንደሆኑ ያስታውሱ፡፡

## 1. ከላይ የተሰጡትን ሐሳቦች በይበልጥ ለመረዳት በሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ባዶ ቦታዎች በተገቢው ቃላት ወይም ሐረጎች ይሙሉ፡፡

- ሻማ ብርሃን የመስጠት እምቅ ወይም ____________________ አለው ማለት እንችላለን፡፡
- ____________ ብርሃን _________________ የመስጠት ወይም ድብቅ ችሎታ አለው፡፡
- ሻማው ____________________________________ ከፈለግን ___________________

  ያስፈልጋል፡፡ ሆኖም ከመቀጣጠሉ በፊትም ብርሃን የመስጠት ________________ አለው፡፡

- ______________________ ነገሮች አንድ ____________________ የላቸውም::
- እርሳስን _______________ ? ወይስ እርሳስ ያለውን _______________ ላይ ለማዋል መቀረጽ ይገባዋል?

**2. የሕፃናት እምቅ ወይም ድብቅ ችሎታም እንደዚሁ ነው:: ሕፃናት የታደሉትን እንቁ ዎች እንዲያንጸባርቁ ከተፈለገ መማር አለባቸው:: ከዚህ በታች ያሉትን ባዶ ቦታዎች እየሞሉ ስለእነዚህ አቅሞች ወይም ድብቅ ችሎታዎችን ያሰላስሉ ::**

- አሁን ደግሞ የሕፃናትን _______________________ እንመልከት ::ከመካከል ___________________________ ጥቂቶቹ ሕፃናት ያሏቸው ልዩ ተሰጥኦዎች ናቸው:: ለምሳሌ አንዱ _________________________ ሌላው ደግሞ እጅግ ጥኡም___________________________ ይችላል:: ሌላው ደግሞ በ______________________________ ልዩ ችሎታ እንዳለው የሚጠቁሙ ምልክቶችን ያሳያል::

- ባሃኢ አስተማሪ እንደመሆንዎ እያንዳንዱ _________________________ ያለውን ተሰጥኦዎች ________________ እና _________________ መርዳት ይኖርብዎታል::

- ______________________________________ ተማሪዎ ያለውን ተሰጥኦዎች ፈልጎ ማግኘትና እንዲዳብሩም _________ይኖርብዎታል::

- ___________________________ ተማሪዎ__________ ______________ ፣እንቅስቃሴዎች መከታተልና ልዩ_______ ____________________ ፈልጎ______________________ ያስፈልጋል::

- ሁልጊዜ ስለእያንዳንዱ _______________________ ማሰብ ፣ሁኔታቸውን ___________________________ እና ልዩ ችሎታዎቹን _____ __________________ ያስፈልጋል::

- አንዳንድ ሕፃናት አስቸጋሪ ሆነው ያገኟቸው ይሆናል:: ይሁንና ______________ ተግባርዎን በ _______________________ መወጣት ይኖርብዎታል::

## *ምዕራፍ 7*

*የሰው ክቡርነት በባሃኢ ጽሑፎች ውስጥ ዋነኛ የሆነ ጭብጥ እንደሆነ በመጠኑ ከተረዳን አሁን ደግሞ አትኩሮታችንን በጥቂቱም ቢሆን ትምህርትን አስመልክቶ የባሃኢ ቅዱሳን ጽሑፎች ምን እንደሚያስ ገነዘቡን እንመልከት፡፡*

*ለምንድን ነው ሕፃናትን የምናስተምረው? ምን ዓይነት ውጤት ለመቀዳጀት እንፈልጋለን? እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ እንዲችሉ የሚከተለውን የአብዱል-ባሃን ጥቅስ አንብበው ያሰላስሉባቸው፡፡*

> **"የልጆችን ትምህርት ስለሚመለከተው ጥያቄህ ደግሞ፡- ፊታቸውን ወደ እግዚአብሔር ያዞሩ ዘንድ፣ መንገዶቻቸው የመልካም ጠባይ ደንቦችን የተከተሉና ጠባያቸው ከማንም ሰው የማያንስ ይሆን ዘንድ፣ የሰውን ዘር ጸጋዎችና አስመስጋኝ ባህሪያትን ሁሉ የራሳቸው ያደርጉ ዘንድ፣ ከመጀመሪያው የሕይ ወታቸው ጊዜ ጀምሮ መንፈሳዊያን፤ በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ ነዋሪዎች፤ የቅድስና ጣፋጭ እስትንፋስ አፍቃሪዎች እንዲሆኑ፤ ሃይማኖታዊ፤ መንፈሳዊ እና የመንግሥተ ሰማይ ግዛት ትምህርት እንዲቀበሉ፣ልዩ ልዩ የሆኑ የትምህርት ዘርፎችን ዕውቀት ይገበዩ ዘንድ፣ በእግዚአብሔር ፍቅር ጉያ ውስጥ እነርሱን ማሳደግ ይገባሃል፡፡ ወደ መንፈሳዊ ነገሮች ጥረት ማድረጋቸውን እንዲቀጥሉም ማበረታታት አለብህ፡፡ እነሆ፤ በዚህም የሚያስደስት ውጤት ይሰጣቸው ዘንድ አምላክን እጣራለሁ፡፡"[5]**

### *1. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች ከላይ በተሰጠው ጥቅስ ውስጥ በሚገኙ ተገቢ ቃላት ይሙሉ፡፡*

*ሕፃናትን በእግዚአብሔር ____________________ ጉያ ማሳደግ ________*

*____________________ እና ወደ ____________________ነገሮች*

*____________________ ጥረት ማድረጋቸውን እንዲቀጥሉ ________*

*____________________ እንዳለብን አብዱል-ባሃ ይነግረናል፡፡ ሕፃናቱ ወደ ________*

*____________________ ነገሮች ጥረት እንዲያደርጉና ፊቶቻቸውን ወደ ________*

*____________________ ያዞሩ ዘንድ አስተማሪው ____________________ ይገባል፡፡*

*መንገዶቻቸው የመልካም ____________________*

*እንዲሆኑ አስተማሪው ሊረዳቸው ይገባል፡፡ የሰውን ዘር ____________________*

*እና አስመስጋኝ____________________ ሁሉ ____________________ማድረግ*

*አለባቸው፡፡ መንገዶቻቸው የመልካም ____________________ የተከተሉና*

*የሰውን ዘር ____________________ እና ____________________*

*ባህሪያት በሙሉ የእራሳቸውን እንዲያደርጉ አስተማሪው ሊረዳቸው ይገባል፡፡*

*ሕፃናት ከ ____________________ ጊዜ ____________________ጀምሮ*

*____________________ ውስጥ ነዋሪዎች፣የ ____________________*

*ጣፋጭ እስትንፋስ አፍቃሪዎች እንደሆኑ አስተማሪው ሊረዳቸውይገባል፡፡*

_______________________________፤ _______________________________

እና ______________________________ ግዛት ትምህርት እንዲቀበሉ ይገባል። ሕፃናት

ከ ____________________ የህይወታቸው ጊዜ ጀምሮ____________________ ፣ የ

_____________________________ ው______________________________ ፣የቅድስና

ጣፋጭ __________________________ መሆን ይገባቸዋል።____________________

፣______________________________ እና ____________________________

ግዛት ትምህርት እንዲቀበሉ ይገባል።

______________________________ በእግዚአብሔር ___________________________

ማሳደግ፤ ወደ ____________________ነገሮች ጥረት ማድረግ እንዲችሉ ____________

መንገዶቻቸው የመልካም ______________________ ደንቦችን ___________________

እና የሰው ዘርን _________________________________ እና __________________

ባህሪያት ሁሉ የራሳቸውን እንዲያደርጉ መርዳት እንዳለብን ማስታወስ ያስፈልጋል።

ከ ________________________________ ጊዜ ጀምሮ ________________________

፣የ _______________________ውስጥ ነዋሪዎች፤ የ ___________________________

ዘርፎችን ______________________________ መገብየትና____________________

መንፈሳዊና _____________________________ ግዛት ትምህርት እንዲቀበሉ ይገባል።

**2. ከላይ የተሰጠውን የአብዱል-ባሃን ጥቅስ ካጠኑ በኋላ የሕፃናት ትምህርት ዓላማው ምንድን ነው ብለው ተገነዘቡ? የሚያስተምሯቸው ሕፃናት ምን እንዲሆኑ ይፈልጋሉ? ተማሪዎች ምን መንፈሳዊ ባሕሪያ በውስጣቸው እንዲያዳብሩ መርዳት ዋናው ዓላማም እንደሆነ አው ቀዋል፡ ከጨቅላነት ዕድሜአቸው ጀምሮ መንፈሳዊ ትምህርት ማግኘትና ንፁህ፤ ሐቀኛና የተቀደሱ ተግባሮችን ለማከናወን መፈለግ አለባቸው፡**

## 3. አሁን ደግሞ በምሳሌ በተሰጠው መሠረት የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች ይሙሉ።

ለምሳሌ፡- <u>እውነተኛ እንዲሆኑ ሕፃናትን መርዳት</u> አለብኝ።

<u>ፍትሃዊ እንዲሆኑ ሕፃናትን መርዳት</u> አለብኝ ።

______________________________ አለብኝ።

______________________________ አለብኝ።

______________________________ አለብኝ።

______________________________ አለብኝ።

______________________________ አለብኝ።

______________________________ አለብኝ።

# ምዕራፍ 8

*እርስዎ እራስዎ በሕይወትዎ መንፈሳዊ ባሕሪያትን ለማንጸባረቅ የዕለት ተዕለት ጥረት በማድረግ ሂደት ውስጥ ሳይሆኑ ሕፃናትን መንፈሳዊ ባሕሪያት እንዲያዳብሩ መርዳት ይችላሉን? እስቲ በዚህ ጥያቄ ላይ ለጥቂት ደቂቃዎች ያሰላስሉ። ከዚያም የሚከተለውን የባሃኦላህን ምክር ያንብቡና በቃልዎ ይያዙት።*

> **" ከመካከላችሁ የጌታውን እምነት ለማስተማር የሚነሣ ማንም ሰዉ ንግግሩ የእነዚያን እርሱን የሚሰሙትን ሰዎች ልቦች እንዲስብ ከሁሉም በፊት ራሱን ያስተምር።" [11]**

*መልካም ባሕሪያትን በሕፃናት ፊት ብቻ ማንጸባረቁ በቂ ነው ብለው ያስባሉ? አንድ አስተማሪ ተማሪ ዎቹ በሌሉበት ሐሰት ተናገረ እንበል። ይህ በሚያካሂደው የሕፃናት ትምህርት ላይ ተፅዕኖ ይኖረዋልን? ስለ እውነተኛነት በሚያስተምር ጊዜ ቃላቱ ኃይል ይኖራቸዋልን?*

# ምዕራፍ 9

*መንፈሳዊ ባህሪያትን በተሳካ ሁኔታ ለሕፃናት ለማስተማር የአምላክን ፍቅርና የፈሪሃ-እግዚአብ ሔርን ፍሬ በሕፃናት ልብ ንጹህ አፈር ውስጥ መዝራት አለብን። አምላክ ለፍጡሮቹ ካለው ወሰን የሌ ለው ፍቅር ምክንያት እንደተፈጠርንና ያለማቋረጥ የሚመግበንና የሚጠብቀንም ይኸው ፍቅር እንደሆነ ማወቅ አለባቸው። ባሃኡላህን የማወቅን ፀጋ፣ በእርሱም ፍቅር የማደግን ደስታና በእለት ተዕለት ሕይ ወታችን የሚለገሰንን በረከቶች ጨምሮ ስለታደሉን የአምላክን በረከቶች እንዲገነዘቡ ሊያስተምሯቸው ይችላሉ።ሕፃናት ለባሃኦላህ ባላቸው ፍቅር ምክንያት ሕግጋቱንም መታዘዝ እንደሚገባቸው ሊያስተ ምሯቸው ይገባል።*

## *አሁን ደግሞ ቀጥሎ የተሰጡትን የባሃኦላህ ጥቅሶች ያንብቡና ያሰላስሉባቸው:-*

> **"...የኃይሌ አንደበት ምንም ከማይሳነው ክብሬ ሰማይ:- 'ለውበቴ ፍቅር ስትሉ ትእዛዞቼን አክብሩ፣' የሚሉትን ቃላት ለፍጥረቴ ተናግሯል። ምንም አንደበት ሊገልጸው የማይችለውን የፀጋ ሽቶ ከተመሉት ከእነዚህ ቃላት የእጅግ በጣም ተወዳጁን መለኮ ታዊ መዓዛ ያሸተተ አፍቃሪ ደስተኛ ነው። " [7]**

> **"የአምላክ ፍቅር ነበልባል በብሩህ ልቦቻችሁ ውስጥ በድምቀት ይንደድ። በመለኮታዊ መርሖ ዘይት መግቡት? በጽኑነታችሁም መጠጊያ ውስጥ ከልሉት። የእነዚያ ከአምላክ የራቁት ሰዎች አደገኛ ሹክሹክታ ብርሃኑን እንዳያጠፋ በመተማመንና ከአምላክ በቀር ከሁሉም ነገር በመላቀቅ ሉል ውስጥ ጠብቁት።"[8]**

> **" የሕያው ልጅ ሆይ!**
> **ፍቅሬ ምሽጌ ነው፤ ወደዚያ የሚገባ ደህንነትና ዋስትና አለው፤ ፊቱን ከዚያ የሚያዞር ግን በእርግጥ ተንከራትቶ ይጠፋል። " [9]**

**1. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች ከላይ በተሰጡ ጥቅሶች ውስጥ በምታገኟቸው ቃላት ይሙሉ::**

የአምላክን ሕግጋት ለእርሱ ____________________ ስንል ማክበር አለብን:: የአምላክን ሕግጋት ለእርሱ ____________________ ስንል ____________________ አለብን:: የአምላክ ፍቅር ነበልባል በ____________________ ልቦቻችን ውስጥ መንደድ አለበት:: የአምላክ ፍቅር ____________________ በ __________ ____________________ ልቦቻችንውስጥ ____________________አለበት::

የአምላክ____________________ በብሩህ ____________________ ውስጥ በድምቀት መንደድ አለበት:: የአምላክን ____________________ ለእርሱ ____________________ ስንል ማክበር አለብን:: የአምላክን __________ ____________________ ነበልባል በ____________________ መርሆ ዘይት____________________ አለብን:: የአምላክ ____________________ነበልባል በ ____________________ መርሆ ዘይት____________________ አለብን::

____________________ መጠጊያ ውስጥ መከለል አለብን:: በ __________ ____________________ መጠጊያ ውስጥ____________________ አለብን:: የ ____________________ ፍቅርን ነበልባል በጽኑነታችን____________________ ውስጥ መከለል አለብን:: በ____________________ መጠጊያ ውስጥ __________ ____________________ አለብን:: በ____________________ እና ከአምላክ በስተቀር ከሁሉም ነገር በ____________________ ሉል ውስጥ መጠበቅ አለብን::

በ____________________ እና ከአምላክ በስተቀር ከሁሉም ነገር በ ____________________ ውስጥ መጠበቅ አለብን:: የአምላክ __________ነበልባል ____________________ በ____________________ ውስጥ በ ____________________ መንደድ አለበት::

በ____________________መጠጊያ ውስጥ መከለል አለብን:: በ____________________ እና ከአምላክ በስተቀር ከሁሉም ነገር በ____________________ ሉል ውስጥ መጠበቅ አለብን:: የአምላክን ፍቅር ነበልባልን ከአምላክ የራቁ ሰዎች እርኩስ ሹክሹክታ ____________________ እንዳያጠፉ ልንጠብቀውና ልንከባከበው ይገባል::

የአምላክ________________________ ምሽግ ውስጥ የሚገባ ሁሉ ደህንነትና ________________ አለው:: የአምላክ ____________________ውስጥ የሚገባ ሁሉ________________________ እና ________________ አለው:: የአምላክ ________________ ውስጥ የሚገባ ሁሉ____________ እና ______________________ አለው::

## ምዕራፍ 10

*መንፈሳዊ ባህሪያትን በልጆች ውስጥ ለማስረጽ እንዲችሉ የአምላክን ፍቅርና የፈሪሃ-እግዚአብሔርን ዘር በልቦቻቸው ውስጥ መዝራት እንደሚኖርብዎ ተመልክተናል:: የፈሪሃ-እግዚአብሔር ጽንሰ ሐሳብ በጣም ጥልቅና አስፈላጊ ነው:: እዚህ በጥቂቱ ብቻ ለመዳሰስ እንሞክራለን:: አንድን ሰው በጣም በምናፈቅረው ጊዜ እርሱም እንዲያፈቅረን በጣም እንመኛለን:: ይሁንና የእርሱ ፍቅር ሳይደርሰን ቢቀር ልባችን በጣም ያዝናል:: የአምላክም ፍቅር እንደዚሁ የሕልውናችን ምክንያት እንደሆነ እናውቃለን:: የእርሱ ፀጋ ለአንዲት ቅጽበት እንኳን ቢነፈገን ጥልቅ ወደ ሆነ ውርደት እንወድቃለን:: መልካም ያልሆኑ ሥራዎች ችንና ለባሃኦላህ ሕግጋት አለመታዘዛችን ከመንፈሳዊ ዓለም የሚጋርደን መጋረጃና የዚያ ዓለም ፀጋዎች እንዳይደርሱን የሚያግዱ ግርዶሾች ናቸው:: አምላክን ካልታዘዝን የእርሱ ችሮታዎች ሊደርሱን አይችሉም ብለን ስንፈራ ፈሪሃ እግዚአብሔር ይሰማናል:: ፈሪሃ-እግዚአብሔር በቀጥተኛው መንገድ ላይ እንድንቆይ የሚያደርገንና ከእኔነት፣ ከክፉ ስሜቶቻችንና አምላክን ከሚያሳዝኑ ድርጊቶች የሚጥብ ቀን መሣሪያ ነው::*

ስለዚህ አስተማሪው አምላክን የሚያሳዝኑ ድርጊቶች የትኞቹ እንደሆኑ በየጊዜው ለተማሪዎቹ ማሳወቅ ይኖርቦታል:: አንድ ልጅ የተመሰገነ ተግባር በሚያደርግ ጊዜ ደግሞ ያ ተግባር አምላክን በደስታ እንደ ሚሞላው ለልጁ በመንገር ማበረታታት ይገባል::

### 1. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ከላይ በተጠቀሰው ምንባብ ውስጥ በሚገኙ ቃላት በመ ውሰድ ያሟሉ::

- መንፈሳዊ ባህሪያትን በልጆች ውስጥ ለማስረጽ እንዲችሉ የአምላክን __________ ________________ የ ________________________ እግዚአብሔርን ____________________ ዘሮች በልቦቻቸው ውስጥ መዝራት ያስ ፈልጋል::

- መንፈሳዊ ________________ በልጆች ውስጥ ለማስረጽ ______________ የአምላክ________________________ የ____________________ እግዚአብሔርን ____________________ ዘሮች በልቦቻቸው ውስጥ መዝራት ያስፈልጋል::

- አንድን ሰው በጣም________________________ ጊዜ ________________ እርሱም እንዲያፈቅረን በጣም እንመኛለን:: ይሁንና የእርሱ____________________ ሳይደርሰን ቢቀር ልባችን በጣም_______________ ::

- አንድን ________________________ በጣም___________________ ጊዜ እርሱም እንዲያፈቅረን በጣም እንመኛለን:: ይሁንና_____________________ ፍቅር ሳይደርሰን ቢቀር ልባችን በጣም ___________________________ ::

- አንድን ሰው በጣም ____________________ ጊዜ እርሱም ___________በጣም እንመኛለን:: ይሁንና ____________________________ የእርሱ ፍቅር ሳይደርሰን ቢቀር ልባችን በጣም ____________________________ ::

- የ _____________________ ፍቅር የ _______________________ ምክንያት ነው::

- ክፉ ስራዎቻችንና ለባሃኡላህ ህግጋት ____________________________ ዓለም _____________________ እና የዚህም ዓለም ____________________ እንዳይደርሱን የሚያግዱ ግርዶሾች ናቸው::

- _____________________ እና ባሃኡላህ ህግጋት___________________ የሚጋርዱን_____________________________ ግርዶሾች ናቸው::

- አምላክን ካልታዘዝን የእርሱ ችሮታዎች ሊደርሱን አይችሉም ብለን ስንፈራ___________ ይሰማናል::

- አምላክን ___________________ የእርሱ ________________________ ሊደርሱን አይችሉም ብለን ስንፈራ ___________________________ ይሰማናል::

- በቀጥተኛው ____________________________ ላይ እንድንቆይ የሚያደርገንና ከ_________________________ እና _________________________ ከሚያሳዝነ_________________________ የሚጠብቀን ______________ ነው::

## 2. የሚከተለውን የባሃኦላህ ምክር በቃልዎ ይያዙ::

"ሰዎች ሆይ. የምትፈሩት አምላክን ይሁን፤ ከእነዚያም የጽድቅን መንገድ ከሚከተሉት ሁኑ::"[10]

# ምዕራፍ 11

ልጆችን በእግዚአብሔር__________________ ጉያ ውስጥ መመገብና ወደ__ __________________ነገሮች ጥረት ማድረጋቸውን እንዲቀጥሉ ማበረታታት ግዴታችን እንደሆነ አብዱል-ባሃ እንደነገረን በዚህ ሥልጠና ተምረናል።

መንገዶቻቸውን ከመልካም__________________ ደንቦችን እንዲከተሉና የሰው ዘርን __________________ ና__________________ ባሕሪያት ሁሉ የራሳቸው እንዲያደርጉ ሕፃናትን መርዳት አለብን።

ሕፃናት ከ __________________ ጊዜ ጀምሮ__________________ ውስጥ ነዋሪዎች የቅድስና ጣፋጭ እስትንፋስ አፍቃሪዎች መሆን ይገባቸዋል። __________________ እና __________________ ግዛት ትምህርት ሊቀበሉ ይገባል።

መንፈሳዊ ባህሪያትን በሕፃናት ውስጥ ለማስረጽ እንድንችል የ__________________ እግዚአብሔርንና የአምላክን__________________ ዘሮች በንፁህ ልቦቻቸው ውስጥ መዝራት ያስፈልጋል።

አምላክ ለፍጡሮቹ ካለው ወሰን የሌለው ፍቅር ምክንያት እንደተፈጠርንና የባሃኡላህን ህግጋት የምንታ ዘዘውም ለእርሱ ካለን ፍቅር ምክንያት መሆኑን ሊማሩ ይገባል። የአምላክ ህግጋት ለእርሱ__________________ ስንል ማክበር አለብን። የአምላክ__________ __________________ ነበልባል በብሩህ __________________ ውስጥ በድምቀት መንደድ አለበት። ነበልባሉንም በመለኮታዊ ዘይት መመገብ እና በ________ __________________ መጠጊያ ውስጥ መከለል አለብን።

የእነዚህ ከአምላክ የራቁት ሰዎች እርኩስ__________________ ብርሃኑን __________________ በ __________________ እና ከአምላክ በቀር ከሁሉም ነገር ውስጥ__________________ መጠበቅ አለብን።

በተጨማሪም ሕፃናት መንፈሳዊ ባህሪያትን እንዲያዳብሩ ከፈለግን እኛ እራሳችን እነዚህን ባህሪያት በዕለት እንቅስቃሴያችን ማሳየት እንዳለብን ተምረናል።

## የሚከተለውን የባሃኡላህ ምክር መታዘዝ አለብን

"ከመካከላችሁ የጌታውን እምነት ለማስተማር የሚነሣ ማንም ሰዉ፣ ንግግሩ የእነዚያን እርሱን የሚሰሙትን ሰዎች ልቦች እንዲስብ፣ ከሁሉም በፊት ራሱን ያስተምር።"[7]

## ምዕራፍ 12

*በልጅነታችን የምናዳብራቸው ልማዶችና ባሕሪዎች የቀሪው ህይወታችን የእለት ተዕለት ድርጊቶቻችን አካል ይሆናሉ:: ተማሪዎችዎም እንደልማድ እንዲያዳብሯቸው የሚረዷቸውን መንፈሳዊ ባህሪያት ጠቀሜታና ተዛማጅነት ያስተውሉ:: እያንዳንዳችን በሺህ የሚቆጠሩ ልማዶች አሉን:: ከሁሉም በላይ መስራት የምንወዳቸው ስራዎች በተለይ መመገብ የምንመርጣቸው የምግብ ዓይነቶች፣ የሚያዝ ናኑን ነገሮች፣ የሚያስከፉን ነገሮች እና ሌሎችም በሺህ የሚቆጠሩ ጥሩም ይሁን መጥፎ ልማዶች የሚገነቡት በልጅነታችን ወቅት ነው:: በልጅነት ጊዜ የገነባናቸውን ልማዶች ከጎለበትን በኋላ ለመቀየር በጣም አዳጋች ነው:: ስለዚህ ልጆችዎ ከባሃኢ ሕይወት ጋር ተስማሚ የሆኑ ልማዶችንና ባሕሪዎች እንዲያዳብሩ መከታተል ይኖርብዎታል:: ከእነዚህ ልማዶች መካከል ጧትና ማታ መፀለይ፣ የአስራ ዘጠነኛ ቀን በዓል መካፈልና ንጽሕናን መጠበቅ ይገኙ ብታል:: በቀጣዮቹ ጥቂት ወራት ስለእራስዎ ልማዶች ያሰላስሉ:: በሚገባ ከመረመሯቸው በኋላ አንዳንድ መለወጥ የሚገባዎ ልማዶች እንዳሉ ይወስኑ:: ስለእራስዎ ልማዶች እያሰላሰሉ እግረ-መንገድዎን ለሕፃናቱ ሊያስተምሯቸው የሚገቡ መንፈ ሳዊ ልማዶችን ይዘርዝሩ::*

## ምዕራፍ 13

*የሚከተሉት ሁኔታዎች ሕፃናትን በሚያስተምሩ ጊዜ ሊከሰቱ ይችላሉ:: እስካሁን የተማሯቸ ውን መመሪያዎች በመጠቀም ችግሮቹን መፍታት ይችላሉን?*

*ሀ. ጆርጅ በጣም ተንኮለኛ ልጅ ነው:: ሁልጊዜ ሌሎቹን ሕፃናት ከማስቸገሩም በላይ በትምህርት ጊዜ ያወራል ጥያቄ በጠየቁት ጊዜ ግን መልሱን ተሳስቶ አያውቅም:: ምን ቢያደርጉት ይሻ ላል?*

1. *ሁሉንም ልጆች ስለሚያስቸግርና እንዳይማሩ ስለሚበጠብጥ ከክፍል ያስወጡታል::*
2. *አእምሮውን እንዲጠቀም፤ በስራ እንዲጠመድና ሌሎቹን እንዳያስቸግር ከበድ ያለ መልመጃ ይሰ ጡታል::*
3. *ማንንም እንዳያስቸግርና እርስዎም በቀላሉ ይረሱት ዘንድ ከሌሎቹ ተማሪዎች ራቅ ባለ የክፍሉ ጥግ እንዲቀመጥ ያደርጉታል::*

*ለ. ጊታ አታስቸግርም:: ከክፍል ቀርታ አታውቅም:: በጥሞናም ታዳምጣለች:: ይሁንና አንድም ጥያቄ መልሳ አታውቅም:: አንድ ነገር ሲያስተምሯት ትንሽ ቆይታ ትረሳዋለች:: በምን መንገድ ቢረዷት ይሻላል?*

1. *አንድም የቀሰመችው ትምህርት ያለ ስለማይመስል ከክፍል ብትባረር ይሻላል::*
2. *እንዲገባት የሚያስችሉ ሌሎች ማስተማሪያ መንገዶች ካሉ በትእግስት ይሞክራሉ::*

3. ደደብ እንደሆነችና ሌሎች ተማሪዎች ከሄዱ በኋላ ለእርሷ ብቻ የጥናት ጊዜ ቢያዘጋጁላት እንደሚሻል ይገልጹላታል?

4. ሌላ አማራጭ ይስጡ:-

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

ሐ. አቡያ ከሊሎቹ ልጆች በ በእድሜ በጣም ያንሳል:: ሰዎች ጥያቄ ካልጠየቁት በስተቀር አያወራም ፤ አይስቅም:: በጣም ይጥራል:: ነገር ግን ትክክለኛ መልስ መስጠት ሲቸግረው ሌሎች ልጆች ይስቁበታል:: አቡያን በምን መንገድ ብትረዱት ይሻላል?

1. እድሜው ገና ስለሆን ወደቤት እንዲመለስ ያደርጉታል::
2. መልሶች ትክክል ባይሆኑም መሳቅ እንደሌለባቸው ለልጆችዎ ያስተምሯቸዋል:: ምክንያቱም ማንኛውም ሰው ልጆችም ቢሆኑም መከበር ይገባቸዋልና::
3. ወላጁን አስጠርተው አቡያን ትንሽ እስኪያድግ ድረስ እንዳያመጡት ይነግሯቸዋል::
4. ሌላ አማራጭ ይስጡ:-

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

መ. ኩማር ከሌሎቹ ሕፃናት በእድሜ በጣም ይበልጣል:: ጠንክሮ የሚያጠና ሲሆን ብዙ ነገርም ያውቃል:: ይሁንና ሌሎቹ ልጆች እኩዮቼ አይደሉም ብሎ ስለሚያስብ የሕፃናት ትምህርት ክፍለ ጊዜ ላይ ተገኝቶ አያውቅም:: ኩማርን በምን መንገድ ብትረዱት ይሻላል?

1. በእድሜ ክፍ ያለ ስለሆነ ከትምህርቱ መሰረዝ?

2. ለየት ያሉ ስራዎችን ከእርሱ ጋር ማከናወን:: ለምሳሌ በዕድሜ አነስ ያሉ ሕፃናትን እንዴት መርዳት እንደሚቻል ያስተምሩትና እንደአስፈላጊነቱ በትምህርት ክፍለ-ጊዜ ሕፃናትን እንዲያስ ጠና ያደርጉታል:: በዚያው ከተማ ሌላ የሕፃናት ትምህርት ያካሂዱ ከሆነ ተጨማሪ ልምድ እንዲያገኝ እዚያም ይወስዱታል?

3. በሕፃናት ትምህርት ለመታቀፍ ከሚገባው እድሜ እንዳለፈና ከፈለገ የሞያ ትምህርት(እደ-ጥበብ) ሊያስተምሩት እንደሚችሉ ይገልጹለታል፡

4. ሌላ አማራጭ ይስጡ:-

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

ሠ. ሊዊስ ሁልጊዜ እጁን ቢያወጣም አንድም ጊዜ በትክክል መልሶ አያውቅም:: ስለሚያስቸግሩና በክፍል ውስጥ ስለሚያወሩ ሕፃናት ሁልጊዜ የነቀፌታ ሂስ እንደሰነዘረ ነው:: ሊዊስን ምን ማድረግ ይሻላል?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

ሸ. በአንድ ክፍል ውስጥ ከሌሎቹ ይበልጥ በጣም በፍጥነት የመረዳት ችሎታ ያላቸው ልጆች አሉ:: የሚጠይቁት ጥያቄዎች ደግሞ ከደረጃቸው በላይ የሆኑ ናቸው:: አስተማሪው እነዚህን ልጆች እንዴት ማድረግ ይገባዋል ይላሉ?

1. ከሌሎቹ የበለጠ ለማወቅ መሞከራቸው አግባብ ስላልሆነ ሊቆጧቸው ይገባል::

2. ከእነርሱ ጋር መራመድ እንዲችሉ የተቀሩትን ተማሪዎች መገፋፋት፤

3. ሁሉም ተማሪዎች በሚገባቸው መንገድ የፈጣኖቹን ተማሪዎች ጥያቄዎች መመለስ፤ ለፈጣኖቹ ተማሪዎች ከበድ ያሉ መልመጃዎችን መስጠት ነገር ግን አንዱ ከሌላው ዝቅተኛ ወይም የተሻለ ሆኖ እንዳይሰማው ይህንን ልዩነት መደበቅ ወይም እንዳይታወቅ ማድረግ::

4. ፈጣኖቹን ተማሪዎች ከሌሎቹ በመለየት ለሌሎቹ ምሳሌ እንደሆኑ መናገር::

ቀ. አስተማሪው ከተማሪዎቹ አንዱን ለመማሪያ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን እንዲገዛ ሱቅ ይል ከዋል:: ተማሪው ሲመለስ መመለስ ከሚገባው ገንዘብ ግማሹን ለአስተማሪው ይመልሳል:: ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ተማሪው ከረሜላ ሲበላ አስተማሪው ያይና ቀሪውን መልስ ከረሜላ ገዝቶበት ነው ሲል ያስባል:: ይህን ጊዜ አስተማሪው ምን ማድረግ አለበት?

1. አንተ ሌባ ነህ፤ የአንተ ባልሆነ ገንዘብ ከረሜላ መግዛት አልነበረብህም ብሎ ተማሪውን መቆጣት አለበት::

2. ትምህርቱ ካለቀ በኋላ ልጁ እቃውን ወደ ገዛበት ሱቅ በመሄድ የተገዙት ቁሳቁሶች ምን ያክል እንዳወጡ ማጣራት:: ሕፃኑ ተማሪ ዋሽቶ ከሆነ በሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ ለብቻው ጠርቶ ባሃሉላህ እንዳንሰርቅና ውሸት እንዳንናገር የከለከለን መሆኑ አበክሮ ፍቅር በተሞላበት መንገድ መምከር::

3. ወዲያውኑ ወደሱቅ በመሄድ ቁሳቁሱ ስንት እንዳወጣ መጠየቅና ልጁ ዋሽቶ ከሆነ በተማሪዎቹ ፊት "በክፍላችን ውስጥ ሊታመን የማይቻል ልጅ አለ::" ብሎ የሆነውን ሁሉ አንድ በአንድ መዘርዘር::

4. "ወደሱቅ ሄዶ የተገዙት ቁሳቁሶች ይህን ያክል ገንዘብ ማውጣት አለማውጣታቸውን የሚያጣራ ማን አለ" ብሎ ተማሪዎቹን መጠየቅ::

5. ነገሩን ምንም ሳያደርጉ በዝምታ ማለፍ::

በ. በፀጥታ እንዲያዳምጡ መምህርቷ ቢጠይቁም አንዳንድ ልጆች እርሷን ከማዳመጥ ይልቅ በክፍሉ ውስጥ ይጫወታሉ:: መምህርቷ ምን ማድረግ አለባት?

1. ስርዓት የማይዙት ለምን እንደሆነ መመርመር:: መማር ስለደከማቸው ከሆነ የትምህርቱን አሰጣጥ መንገድ መቀየር:: ችግር ፈጣሪው አንድ ልጅ ብቻ ከሆነ እርሱን ከሌሎቹ መለየት::

2. በተደጋጋሚ ስርዓት ባለማክበራቸው ልትቀጣቸው እንደሆነ መምህርቷ ክፍል ውስጥ ለሚጫወቱት ልጆች መንገር፡፡

3. ከዚያ በላይ መታገስ ስለማትችል ልጆችን ከክፍል ማባረር፡፡

4. ወላጆቻቸውን ጠርቶ ስለልጆቻቸው አስቸጋሪነት መንገርና ልጆቹን ስርዓት እንዲጠብቁ አድርገው ባለማሳደጋቸው መቆጣት፡፡

ተ. ተማሪዎችዎ የሰጧቸውን የቤት ስራ ሰርተው አቀረቡልዎ፡፡ አንዳንዶቹ ልጆች በጣም በጥ ንቃቄ ሰርተዋል ሌሎቹ ግን በጥንቃቄ አልሰሩም፡፡ ልጆቹ ለስሯቸው ደረጃ እንዲሰጧ ቸው ቢጠብቁብዎና እርስዎ ግን ጥሩ ያልሰሩ ተማሪዎችን ስሜት ለመጉዳት ባይፈልጉ ማድረግ የሚገባዎ ጥሩ ነገር ምን ድን ነው?

1. የቤት ሥራዎቹ በደንብ ያልተሰሩ በመሆናቸው የበለጠ ተጠንቅቀው እንዲሰሯቸው መንገር፡፡

2. በደንብ ከተሰሩት የቤት ስራዎች መካከል አንዱን ለልጆቹ በማሳየት "እንደዚህ ነው የቤት ሥራው መሰራት ያለበት፡፡ ግልጽና ጥሩ በሆነ የእጅ ጽሑፍ መጻፍ ይገባዋል" ማለት፡፡

3. የቤት ሥራቸውን በጥንቃቄ ያልሰሩትን ልጆች መቅጣትና በሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ በደንብ ሰርተው ካልመጡ ክፍል ውስጥ እንደማያስገቧቸው ማስፈራራት፡፡

4. የቤት ሥራዎቻቸውን በጥንቃቄ የሰሩትን ልጆች በግልፅ ጠርቶ ማበረታታትና በጥንቃቄ ያልሰሩ ትንም በግል በመጥራት «የቤት ሥራህን ጥሩ አድርገህ ሰርተሃል፡፡ የበለጠ ግልጽና ንጹህ አድር ገህ ልትሰራው ትችል ነበር፡፡ የነገውን የቤት ሥራ የተሻለ አድርገህ እንደምትሰራ እርግጠኛ ነኝ፤ ማለት፡፡

ቸ. መምህሩ ለሕፃናቱ ለማሳየት ስዕል ይዞ መጥቶ ነበር፡፡ ከእረፍት በኋላ ሲመለስ በስዕሉ ላይ ተጽፎበት አገኘ፡፡ ሁለት ሕፃናትም "የፃፈው እርሱ ነው" እየተባባሉ እርስ በእርሳቸው ተካሰሱ፡፡ ማን እንዳጠፋ አስተማሪው እንዴት ማወቅ ይችላል?

1. ስዕሉ ላይ የጻፈው የቱ ልጅ እንደሆነ ማወቅ ስለማይቻል ሁለቱንም መቅጣት አለበት፡፡

2. ስዕሉ ላይ የጻፈው የቱ ልጅ እንደሆነ ማወቅ ስለማይቻል ማንንም መቅጣት የለበትም፡፡

3. በመጀመሪያ በክፍል ውስጥ ያሉትን ልጆች ለየብቻ ይጠይቃል፡፡ ከዚያም የክፍሉን ተማሪዎች ሁሉ በአንድ ላይ ይጠይቃል፡፡ በዚህ መንገድ ተገቢ የሆነ ብያኔ ሊሰጥና መቀጣት የሚገባው ልጅ የቱ እንደሆነ ሊያውቅ ይችላል፡፡

4. ጥፋተኛ የሆነውን ተማሪ ለመቅጣት እንዲችል አስተማሪው የሚወደውን ልጅ ጠርቶ የተፈ ጠረውን ነገር ሁሉ አጣርቶ እንዲነግረው ማድረግ ይችላል፡፡

5. ሌላ አማራጭ ይስጡ፡-

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

ነ. አንዲት ትንሽ ልጅ ከልጆች ጋር አብራ መማር አትፈልግም፡፡ ጥግ ላይ ለብቻዋ ተቀምጣ መጫወት እንጂ ትኩረቷን ወደ ትምህርቱ አታደርግም፡፡ ልጅቷ የሚሰጠውን ትምህርት

እንደሌሎቹ መረዳት አለመቻልዋን አስተማሪዋ ያስተውላል:: አስተማሪው ምን ማድረግ ይችላል?

1. ወደ ልጆቹ በመቀላቀል ትኩረቷን የበለጠ ትምህርቱ ላይ ብትሳርፍ ሊገባት እንደሚችል መንገር::

2. አስቸጋሪ በመሆኗ መቅጣት::

3. ትምህርቱን ለመማር የሚፈልጉ 20 ተማሪዎች ስላሉ ከአንዲት ዘገምተኛ ተማሪ ጋር የሚያጠ ፋው ጊዜ ስለሌለው ልጅቷን ከክፍል ማስወጣት::

4. ክፍሉን የማትበጠብጥ ከሆነ የፈለገችውን እንድትሰራ መፍቀድና ሌሎቹ ተማሪዎች የግል የክፍል ሥራ ሲሰሩ ልጅቷን ማስጠናት::

ኘ. አንዲት ልጅ ከሌሎቹ የበለጠ ብዙ ፀሎቶችን በቃሏ ይዛለች:: አጋጣሚውን ባገኘች ጊዜ ፀሎቶቹን በጥኡም ድምጿና በታላቅ ተመስጦ ትደግማቸዋለች:: ከሌሎቹ ሕፃናት ስተለሻለች ሁልጊዜ ፀሎት እንድታደርግ ሊፈቅድላት ይገባልን?

ኀ. አንድ ሕፃን ሁልጊዜ ቆሽሽ ብሎ ወደ ክፍል ስለሚመጣ ማንም ከእርሱ አጠገብ መቀመጥ አይፈልግም:: ልጁም የተጠላ ስለመሰለው ይከፋል:: ጽዳቱን ጠብቆ እንዲመጣ ምን ማድረግ አለብዎ? ወደቤቱ መመለስ? እቤት ውስጥ ስላለ ችግር ለብቻው ለይቶ ማነጋገር? የሚኖረው ከወላጆቹ ጋር ነውን? እናቱ በጧት ተነስተው ወደሥራ ስለሚሄዱ እርሱን ለመከታተል ጊዜ ስለ ሌላቸው ነውን? ከቤተሰቡ መካከል እንዴት ንጽህናውን መጠበቅ እንደሚችል ያስተማረው ሰው አለን?

1 ወደቤቱ መመለስ

2 እቤት ውስጥ ስላለ ችግር ለብቻው ለይቶ ማነጋገር

3 የሚኖረው ከወላጆቹ ጋር ይሁን አይሁን ማረጋገጥ

4 እናቱ በጠዋት ተነስተው ወደሥራ ስለሚሄዱ እርሱን ለመከታተል ጊዜ ስለሌላቸው ነው::

5 ከቤተሰቡ መካከል እንዴት ንጽህናውን መጠበቅ እንደሚችል ያስተማረው ሰው ስለሌለው ነው::

አ. የአንድርው ፀባይ ምንም ሊገባዎ አልቻለም:: የክፍል ጓደኞቹ ስዕል መሥራት ሲጀምሩ መጫወት ይፈልጋል:: ሲጫወቱ ደግሞ ስዕል መሥራት ይጀምራል:: በአጠቃላይ አንድርው ነገሮችን የሚያደርገው ያለጊዜያቸው ነው:: ምን ሊመክሩት ይችላሉ?

ከ. ሳሽኮ በንቃት ትምህርቷን የምትከታተልና ጠንክራ የምታጠና ልጅ ናት:: በሁሉም ነገር አንደኛ መው ጣት እንዳለባት ቤተሰቦቿ ያበርታቷታል:: ከሌሎች ልጆች ሁሉ የበለጠ እንደምታውቅ ዘወትር ይነ ግሯቷል:: ተማሪዎችን ጥያቄ በጠየቁ ቁጥር ምንም እንኳን በትክክል ባትመልስም ለመመለስ እጇን በማውጣት የምትሽቀዳደመው ለዚሁ ነው:: የክፍል ሥራ በሰጡ ቁጥርም ከሁሉም ቀድማ ትጨ ርስና “እኔ ከሌሎቹ የተሻለ አልሰራሁምን?” ብላ ትጠይቃለች:: ይህንን የሳሽኮ ፀባይን ለመቀየር የሚችሉት እንዴት ነው? እርሷ ማዳበር የሚገባት ምን ዓይነት መንፈሳዊ ባህሪያት ነው?

# የአንደኛ ክፍል የልጆች ትምህርቶች (ይዘት)

## ዓላማ

ፀሎቶችንና ቅዱሳን ጽሑፎችን በቃል መያዝን፣መዝሙሮችን፣ ታሪኮችን፣ ጨዋታዎ ችንና ስዕሎችን ቀለም መቀባትን ያካተተ ቀለል ያለ የልጆች ትምህርትን ማካሄድን መማር።

# ምዕራፍ 1

አብዱል-ባሃ እንዲህ ይላል:-

> *"...የአምላክ ተወዳጆችና ሴት አገልጋዮች ልጆቻቸውን በሕይወትና ከልብ ማሰልጠን፣ በመልካም ምግባርና በፍጹምነት ትምህርት ቤት እነሱን ማስተማር አለባቸው፡፡ እነርሱ በዚህ ጉዳይ መስነፍ የለባቸውም፣ ውጤታማነት የጎደላቸው መሆን የለባቸውም፡፡"*[1]

ይህንን የአብዱል-ባሃ ፍላጎት የምናሟላበት አንዱ መንገድ በየባሃኢ ማህበረሰባችን (ውስጥ) የልጆችን ትምህርትን በማካሄድ ነው፡፡ ይህን ለማድረግ ደግሞ ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን ልጆችን ለማስተማር የሚሰጡ ሰዎች ቁጥር መበራከት አለበት፡፡ አንድ ሰው ልጆችን ለማስተማር ሲነሳ (የልጆች) ትምህርትን አስመልክቶ ስለተጻፉ መጻሕፍት በብዛት ማወቅ የግድ አስፈላጊው አይደለም፡፡ ትልቁ አስፈላጊ ነገር ልጆችን የማስተማር ፍላጎቱና ለአገልግሎቱም ራስን መስጠቱ ላይ ነው፡፡ ማስተማር በጥናትና በልምድ ቀስ በቀስ ሊዳብር የሚችል ሳይንስና ጥበብ ነውና፡፡

## ጥያቄዎች:-

1. ከላይ በተሰጠው ጥቅስ ውስጥ የልጆችን ትምህርት አስመልክቶ አብዱል-ባሃ ምን ይላል?

________________________________________

________________________________________

________________________________________

2. የአብዱል-ባሃ ትእዛዝ ተፈፃሚነት እንዲያገኝ እርስዎ እንዴት ሊተባበሩ ይችላሉ?

________________________________________

________________________________________

3. ቀለል ያለ የልጆች ትምህርት ክፍለ-ጊዜ መጀመር እንዲችሉ የልጆች ትምህርትን አስመልክቶ ምን ያህል ማወቅ ያስፈልግዎታል?

________________________________________

________________________________________

4. የልጆች ትምህርትን አስመልክቶ ሊኖርዎ ከሚገባ እውቀት የበለጠ አስፈላጊው ነገር ምንድን ነው?

________________________________________

________________________________________

5. የማስተማርን ሳይንስና ጥበብ እንዴት እማራለሁ ብለው ያስባሉ?

________________________________________

________________________________________

## ምዕራፍ 2

ልጆችን ለማስተማር የሚያካሄዷቸው የመጀመሪያዎቹ ተከታታይ ክፍለ ጊዜዎች ጥቂት የማስተማሪያ ስልቶችን ብቻ ያቀፉ ይሆናሉ፡፡ ከእያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ አስቀድመው እነዚህን ስልቶች መከለስና ትምህርቱንም በጥንቃቄ ማዘጋጀት ይኖርብዎታል፡፡ አንዱ ስልት ከቅዱሳን ጽሑፎች ወይንም ከአንድ ፀሎት የተወሰደን ጥቅስ በቃል ማስጠናት ይሆናል፡፡ ስለዚህ ስለቃል-ጥናት ምንነት ማሰላሰል ይገባናል፡፡ ቅዱሳን ጽሑፎችን በቃል ማጥናት አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት ምንድን ነው ብለው ያስባሉ?

በእግዚአብሔር መልእክተኞች አማካኝነት የሚገለጸው የአምላክ ቃል በሕፃናት ልብ ላይ መለካም ተጽእና ያሳድራል፡፡ ሁሉም ነገር የተፈጠረው **"ሁን"** በሚለው የአምላክ ቃል አማክኝነት እንደሆነ ያስታውሱ፡፡ የአምላክ ቃላት ከተጎናፀፉት ኃይል ጋር በሕፃናት ልብ ላይ በሚቀረጹ ጊዜ የሚያደርሱት ተፅዕኖ የቱን ያክል ሊሆን እንደሚችል ያስቡት፡፡

ልጆች ቅዱሳን ጽሑፎችን ወይንም ፀሎቶችን በቃላቸው ለመያዝ እንዲችሉ ለመርዳት በመጀመሪያ የቅዱሳን ጽሑፎቹን ወይንም የፀሎቱን መሪ ቃል ወይንም ሐረግ ትርጉም ማብራራት ይገባዎታል፡፡ ስለዚህ እንደ ሕፃናት አስተማሪነትዎ ማዳበር ከሚገባዎ የመጀመሪያዎቹ ችሎታዎች አንዱ የጸሎቶችን ወይንም የቅዱሳን ጽሑፎችን ዋና ዋና ቃላቶችና ሐረጎች በግልጽ የማብራራት ችሎታ ነው፡፡ ከዚህ በታች አንድ ልምድ ያላቸው አስተማሪ ቀጥሎ የተሰጠውን ፀሎት ትርጉም ለሕፃናት ለማብራራት የተጠቀሙበት ስልት ተጠቅሷል፡፡ ይህንን ስልት በጥንቃቄ በማጥናት ይጀምሩ፡፡

> **"አምላክ ሆይ፤ ምራኝ፤ ጠብቀኝ ብሩህ መብራትና አንጸባራቂ ኮከብ አድርገኝ፡፡ አንተ ኃያሉና ኃይል የተመላህ ነህ፡፡"**

### ምራኝ

1. ሲሳይ መንገድ ጠፋው፤ እቤቱ የሚያደርሰውን መንገድ ማግኘት አልቻለም፡፡ ብዙ ሳይቆይ አንድ ጓደኛውን ያገኘውና ወደ ቤቱ የሚወስደውን መንገድ አየሳው፡፡ ጓደኛው ሲሳይን ወደቤቱ የሚወ ስደውን መንገድ "መራው"፡፡

2. ሰናይት ከማጥናትና ከመጫወት የቱ እንደሚሻላት ማወቅ ስላልቻለች ግራ ገብቷታል፡፡ ስለዚህ የወላጆቿን አስተያየት ጠየቀች፡፡ ጥሩ ምክርም ሰጧት፡፡ የሰናይት ወላጆች ሰናይትን "መሯት"፡፡

አምላካችን ከሁሉ የበለጠ ጓደኛችን ነው፡፡ በፀሎታችንም "አምላክ ሆይ ምራኝ?" የምንለው ለዚሁ ነው፡፡ አምላክ የሚመራን ወዴት ነው?

### ጠብቀኝ

1. ሜዳ ላይ እያለን ኃይለኛ ዝናብ መዝነብ ጀመረ፡፡ ስለዚህ እሮጠን ከመጠለያ ስር እንቆማለን፡፡ መጠለያውም ከዝናብ "ይጠብቀናል"፡፡

2. ኃይለኛ ውሻ ማርታን ሊነክሳት ሲል ወደእናቷ ሮጠች፡፡ እናቷም ከውሻው "ጠበቋት"፡፡

3. ወላጆቻችን ከክፉ ነገሮች "ይጠብቁናል"፡፡

አምላክ እውነተኛ ጠባቂያችን ነው፡፡ "አምላክ ሆይ....ጠብቀኝ፡፡" ብለን የምንፀልየውም ለዚህ ነው፡፡

## አንጸባራቂ ኮከብ

> 1. ብርሃን በሌለበት ቦታ ሁሉ ጨለማ አለ፡፡ ሲጨልም ደግሞ ማየት ስለማንችል ያለንበት ቦታ አናውቅም፡፡ እንጠፋለን፡፡ ሻማ ብርሃን ሊሰጠን ይችላል፡፡ ይሁንና አንድ ሰው ሊያቀጣጥለው ይገባል፡፡ ልባችን መንፈሳዊ ብርሃን ሊሰጥ የሚችል ሻማ ነው፡፡ ይሁንና አምላክ ሊያቀጣጥለው ይገባል፡፡ ስለዚህም **"ብሩህ መብራት አድርገኝ"** ብለን አምላክን በፀሎታችን እንለምናለን፡፡ በመጨረሻም አምላክ ኃያልና ኃይል የተመላ እንደሆነ እንመሰክራለን፡፡

ባሃኡላህ፤ መላው ዓለም እንዲገነዘብ የሚሻው በእርሱ የእግዚአብሔር መልዕክተኛነት የሚያምኑ ሁሉ ጨዋ፣ደግ፣ብልህና ደስተኛ መሆን እንዳለባቸው ነው፡፡ የዓለም ሕዝብን የምንመራ መሪ ኮከቦች እንድንሆንም ይፈልጋል፡፡ ስለሆነም ነው አምላክን **"...አንጸባራቂ ኮከብ አድርገኝ፡፡"** ብለን የምንለም ነው፡፡

# ምዕራፍ 3

የቅዱሳን ጽሑፎችን ጥቅስ ትርጉም ለሕፃናቱ ካብራሩላቸው በኋላ በመቀጠል በቃላቸው እንዲይዙት መርዳት ይኖርብዎታል፡፡ ሕፃናቱ ጥቅሱን በቃላቸው እንዲይዙ እንዴት መርዳት ይችላሉ? መቼም እስከ ዛሬ ብዙ ጥቅሶችንና ግጥሞችን በቃልዎ ሳይዙ አይቀሩም፡፡ የጥቅሱን ትርጉም ከተረዱ በኋላ በቃል መያዝ ቀላል ይሆናል፡፡ ጥቅሱን በቃል ለመያዝ እንዲረዳዎ በመጀመሪያ ጥቅሱን ወደብዙ ሐረጎች ይከፋፍሉት፡፡ ከዚያም የመጀመሪያውን ሐረግ በቃልዎ ይያዙ፡፡ ቀጥለው ሁለተኛውን ሐረግ ይያዙ፡፡ ከዚያም ሁለቱን አንድ ላይ በቃልዎ ይድገሙት፡፡ ጥቅሱን በሙሉ በቃልዎ እስኪይዙ ድረስ በዚህ መንገድ ይቀጥሉ፡፡ ለምሳሌ በምእራፍ ሁለት ውስጥ ያለውን ፀሎት በቃል ለማስያዝ "አምላኬ ሆይ፣ ምራኝ..." በሚለው ሐረግ ይጀምሩና ሕጻናቱ በግልና በቡድን ከእርስዎ በኋላ እንዲደግሙ ያድርጓቸው፡፡ ከዚያም "አምላኬ ሆይ፣ ምራኝ .... " የሚለውን ሐረግ ከ "ጠብቀኝ..." ጋር አያይዘው ሕፃናቱ ከእርስዎ ቀጥሎ እንዲደግሙ ያድርጓቸው፡፡ እነዚህን ሁለት ሐረጎች እራሳቸውን ችለው መድገም ሲችሉ "...የልቤን ብርሃን አብራልኝ... " የሚለውን ሐረግ ይጨምሩላቸው፡፡ በዚህ መንገድ ሐረጎችን እየጨመሩ ጸሎቱን በሙሉ በቃላቸው እስኪይዙ ድረስ ይቀጥሉ፡፡ ሁሉም ሕፃናት በአንድ ላይ ፀሎቱን መድገም ከቻሉ በኋላ እያንዳንዱ ሕፃን ፀሎቱን በቃሉ መያዙን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

ሐላፊነት የሚሰማው አስተማሪ እንደመሆንዎ አዲሱን ሃላፊነትዎን እራስዎን በማስተማር ለመጀመር እንደሚፈልጉ አይጠረጠርም፡፡ ስለዚህ በዚህ ርእሰ ምእራፍ ውስጥ የተካተቱትን ለሕፃናት የተዘጋጁ 15 ትምህርቶችን ከማስተማርዎ በፊት የጥቅሶቹን ትርጉም ለማጥናት፤ ትርጉሞቹን ለህፃናት ለማስረዳት የሚጠቅሙ ምሳሌዎችን ለማሰብና ጥቅሶቹን በቃልዎ ለመያዝ እንዲችሉ በቂ ጊዜ ይመድባል፡፡

# ምዕራፍ 4

ልጆችን ለማስተማር የምንጠቀምበት ሌላው ስልት መዝሙር ነው፡፡ ልጆች መንፈሳዊ መዝ ሙሮችን ሲዘምሩ ልባቸው በደስታ ይሞላል፡፡

አብዱል-ባሃ እንዲህ ይላል፡-

> **"የሙዚቃ ጥበብ መለኮታዊና ውጤታማ ነው፡፡ የነፍስና የመንፈስ ምግብ ነው፡፡ በሙዚቃ ኃይልና መስህብ የሰው ነፍስ ይነቃቃል፡፡ ልቦቸው ንጹሕ ስለሆነና ጥዑመ ዜማም ታላቅ የመስወጥ ኃይል ስላለው በሕፃናት ልቦች ላይ ድንቅ የመስወጥ ኃይልና ውጤት አለው፡፡ ሕፃናት የተሰጡአቸው ድብቅ ተሰጦዎች በሙዚቃ አማካይነት ይገለጻሉ፡፡"** [3]

ከአብዱል-ባሃ ጽሑፎች የተወሰደው ይህ ጥቅስ ሙዚቃ በሕይወታችን ሊኖረው የሚገባውን ቦታ ይጠቁመናል። ልጆች ገና በጨቅላ እድሜያቸው ጀምሮ ጥዑም መንፈሳዊ መዝሙሮችን የመዘመርን አስፈላጊነትን ያስቡት።

ልጆች መዘመር ስለሚወዱ በልጆች ትምህርት ክፍለ-ጊዜ ውስጥ ማድረግ ከሚቀሉ እንቅስቃሴዎች አንዱ እነርሱን መዝሙር ማስተማር ነው። ልጆችን መዝሙር ማስተማር እንዲሳካልን አሁንም ቁልፉ ልምምድ ነው። እርስዎ እራስዎ መዝሙሮቹን ከሚያውቅ ሰው ጋር በመሆን መዝሙርን መለማመድ አለብዎ። ሲለማመዱ ለሙዚቃው ህብርና ቅላፄ(የግጥም ምትና ጥዑመ ዜማ) ልዩ አትኩሮት ይስጡ። መዝሙሮቹን በቴፕ ማዳመጥ ቢችሉ በቶሎ ለመማር ይረዳዎታል። ከዛም ሕፃናቱ መዝሙሩን በሚገባ እስኪችሉ ድረስ ከእነርሱ ጋር በመሆን ደጋግመው መዘመር ይኖርቦታል። መዝሙሩን በቃል ለመያዝ ቅዱሳን ጽሑፎችን በቃል ለመያዝ ከምንጠቀምበት በምዕራፍ ሦስት ከተማርነው ዘዴ ጋር ተመሳሳይ ነው። ልዩነቱ አሁን ሐረጎቹን በምንደጋግምበት ጊዜ ከሙዚቃው ጋር በማጣመር መሆኑ ላይ ነው።

በዚህ ምእራፍ ውስጥ በሚገኙ 15 የልጆች ትምህርቶች ውስጥ የተካተቱትን መዝሙሮች ለልጆች በብቃት ማስተማር እንዲችሉ በቅድሚያ በአስጠኚዎ በመታገዝም ሆነ በካሴት የተቀረጹ መዝሙሮቹን በማዳመጥ በሚገባ እንዲያጠኗቸው ይመከራሉ።

# ምዕራፍ 5

በልጆች ትምህርት ክፍለ-ጊዜ ሊካተት የሚችል ሌላው ስልት ትረካ ነው። ትረካዎች ለልጆች ትምህርት ያላቸው ጠቀሜታ ምንድን ነው? አብዛኛዎቹ ተረቶችና ትረካዎች ስለመንፈሳዊ ባህሪዎችና መመሪያዎች እንዲሁም በእለት ሕይወታችን እንዴት ተግባራዊ ልናደርጋቸው እንደምንችል በምሳሌ ያስተምሩናል። ሌሎች ትረካዎች ደግሞ ለመልካም ሥራዎች የሚገቡ ሽልማቶችንና ክፉ ጠባዮች የሚያስከትሉ ውጤቶችን በግልጽ ያሳያሉ። ልጆች ትረካው ውስጥ ከሚገኙ ሐሳቦች ብዙ ሊጠቀሙና በእነርሱም አማካኝነት ሰፊ ልምድ ስለሚቀስሙ ለጸባያቸውና ለስብዕናቸው ግንባታ ጠቀሜታ ይኖራቸ ዋል።

ባሃኡላህ አብዱል-ባሃን የባሃኢ ትምህርቶች ፍፁም የሆነ አርአያ አድርጎ እንደሰየመው እናው ቃለን። የአብዱል-ባሃ ሕይወት ታሪኮች የባሃኢ ትምህርቶችን በሕይወታችን ውስጥ እንዴት ማንጸባረቅ እንደምንችል ለመረዳት እንድንችል ይረዱናል። ልጆች የአብዱል-ባሃን አርአያነት ዘወትር በአእምሯቸው እንዲቀርጽ ከእርሱ ሕይወት የተወሰዱ ብዙ ታሪኮችን መማር አለባቸው።

## ጥያቄዎች

1. ለልጆች ትምህርት ክፍለ-ጊዜ ትረካዎች አስፈላጊ የሚሆኑት ለምንድን ነው?

______________________________________________

2. አብዱል-ባሃ ማን ነው?______________________________

3. ከአብዱል-ባሃ ሕይወት የተወሰዱ ታሪኮችን መማር አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው?

______________________________________________

______________________________________________

# ምዕራፍ 6

*ታሪክ መተረክ ኪነ-ጥበብ ነው። የመተረክ ብቃት እንዲኖረን ስለጥበቡ መሰረታዊ መመሪያዎችን ማወቅና ጊዜ ወስደን በደንብ መለማመድ ይኖርብናል። ለመተረክ በመጀመሪያ የምንተርከውን ታሪክ በሚገባ ማወቅ ያስፈልጋል። አንድ አስተማሪ ለልጆች ታሪክ መተረክ የሚችልበትን መንገድ ለማየት እንድንችል ከዚህ ቀጥሎ አብዱል-ባሃ በልጅነቱ ያደረገውን መልካም ድርጊት ታሪክ በጥልቀት እናጠ ናለን።*

> በባሃኦላህና በቤተሰቡ ላይ የደረሱትን ችግሮችና መከራዎች ከመጀመራቸው በፊት ባሃኦላህ ሰፊ መሬትና በጣም ብዙ በጎች ነበሩት። እነዚህንም በጎች ተከፋፍለው የሚጠብቁ እረኞችንም አሰማርቶ ነበር። አንድ ቀን እነዚህ እረኞች ሥራቸውን በሚገባ እያከናወኑ እንደሆነ እዲጎበኝ ልጁን አብዱል-ባሃን ይልከዋል። በዚያን ጊዜ አብዱል-ባሃ ገና ትንሽ ልጅ ነበር። አብዱል-ባሃም ጉብኝቱን ጨርሶ ወደ ቤቱ ሲመለስ ሲዘጋጅ አብሮት ሲዘዋወር የነበረው ሰው "*አባትህ በሚመጡ ጊዜ ለእያንዳንዱ እረኛ ስጦታ የመስጠት ልማድ አላቸው።*" አለው። አብዱል-ባሃ የሚያበረክተው ስጦታ ስላልያዘ ለጊዜው ዝም አለ። ይሁንና እረኞቹ ስጦታ እየተጠባበቁ እንደሆነ ሰውየው አጥብቆ ነገረው። ይህን ጊዜ አብዱል-ባሃ አንድ ሃሳብ ብልጭ አለለትና በጣም ተደሰተ። ለእረኞቹ የሚጠብቋቸውን በጎች በስጦታ አበረክትላቸዋለሁ ሲል አሰበ። አብዱል-ባሃ ለእረኞቹ ስላደረገው ችሮታ ባሃኦላህ በሰማ ጊዜ በጣም ተደሰተ። ሁሉም ሰው አብዱል-ባሃን በደንብ መንከባከብ አለበት ምክንያቱም ወደፊት እራሱን ጭምር ለሁሉም ይሰጣልና በማለት ባሃኦላህ በቀልድ መልክ ተናገረ። በእርግጥም አብዱል-ባሃ ሕይወቱን ሙሉ ያደረገው ይህንኑ ነበር። አንድነት በመካከላችን እንዲሰፍንና እውነተኛ ደስታ እንድናገኝ ያለውን ሁሉ እያንዳንዷን የህይወቱን ደቂቃ ሳይቀር ሰጠ።

*አንድን ታሪክ ስናጠና መጀመሪያ መመርመር የሚገባን የታሪኩን ዋና ጭብጥ ነው። ከላይ የተሰጠው ታሪክ ዋና ጭብጥ የአብዱል-ባሃ ለጋስነት ነው ማለት እንችላለን። ከዚህ በኋላ ከጭብጡ ጋር በቀጥታ ግንኙነትያላቸውን የታሪኩን ክፍሎች መለየት አለብን። እነዚህ ክፍሎች የትኞቹ ናቸው? አብዱል-ባሃ በጎቹን ለእረኞቹ ለመስጠት ማሰቡና ባሃኦላህ ስለዚህ የልግስና መንፈስ በሰማ ጊዜ ያሳየው መደሰት እነዚህ ክንዋኔዎች ከዋና ጭብጡ ጋር በቀጥታ የሚገናኙ የታሪኩ ክፍሎች ናቸው። ስለሆነም ታሪኩን ለልጆች ይህን በሚተርኩ ጊዜ እነዚህን ክፍሎች አጉልተው መንገሩ በጣም አስፈላጊ ነው። የታሪኩን የመጨረሻ ክፍል ረስተው ሳይናገሩ ቢቀሩ ወይም "*እረኞቹ የሚጠብቋቸውን በጎች በስጦታ አበረክትላቸዋለሁ!*" ብሎ አብዱል-ባሃ እንዳሰበ ሲናገሩ ለጋስነቱን በሚገልጽ የድምጽ ግነት ሳይተርኩ ቢቀሩ ምን ይሆናል? ጭብጥ ጋር በቀጥታ የሚገኛ ኙ ሁለት በታሪኩ ውስጥ የተጠቀሱ ክንዋኔዎች ይውሰዱና አስፈላጊውን የትረካ ጥበብ በመጠቀም ታሪኩን ጮክ ብለው ያንብቡ። ይህንን ልምምድ አብሮዎት ካሉ ተሳታፊዎች ጋር በመሆን ይደጋግሙት።*

*ምንም እንኳን አሁን የታሪኩን ዋና ዋና ክፍሎች ብንለይም ሌሎቹን የታሪኩን ክፍሎች መርሳት አለብን ማለት አይደለም። ሕፃናቱ በንቃትና በፍላጎት እንዲያዳምጡና ዋና መልእክቱንም እንዲማሩ በማራኪ መንገድ መተረክ አለብን። ያለምንም የትረካ ጥበብ በልጅነቱ አብዱል-ባሃ የአባቱን በጎች ሁሉ ለሚጠብቋቸው እረኞች ሰጠ ባሃኦላህም በዚህ ተግባር ውስጥ የልጁን ለጋስነት ተመለከተ ብለው ብቻ ቢናገሩ ታሪክ ተረኩ ማለት ይቻላልን? አንድ ትረካ ሊያስተላልፈው የሚገባ ዋና መልእክት ቢኖርም ትረካው ድምቀትና ልዩ ስሜት የሚሰጡት ግን አብረው ያሉት ዝርዝሮችና የአተራረክ ጥበብ ነው።*

**ከዚህ በታች የታሪኩ አንዳንድ ክንዋኔዎች ተዘርዝረዋል፤ ዋና ጭብጥ የሆነውና የዋና ጭብጡ አጋዥ ክንዋኔ የሆነውን ይለዩ።**

- *ታሪኩ በተፈጸመ ጊዜ አብዱል-ባሃ ትንሽ ልጅ ነበር።*
- *አብዱል-ባሃ ሥራውን ጨርሶ ሊመለስ ሲዘጋጅ አብሮት ሲዘዋወር የነበረው ሰው ባሃኦላህ ለእረኞቹ ስጦታ የማበርከት ልማድ እንዳለው ነገረው።*

- አብዱል-ባሃ የሚሰጠው ነገር ስላልያዘ ዝም አለ።
- በመጨረሻም በመጣለት ሐሳብ ከፍተኛ ደስታ ተሰማው።

**እነዚህን ነጥቦች ከተረዱ በኋላ ታሪኩን አብሮዎት ላሉት ተሳታፊዎች ይተርኩላቸው። እራስዎን ለሕፃናት አስተማሪነት በሚገባ ለማዘጋጀት፤ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በተካተቱት 15 የሕፃናት ትምህርት ቶች ውስጥ የሚገኙትን ታሪኮች ለማጥናትና ለመተረክ እንዲችሉ ለመለ ማመድ በቂ ጊዜ ይመድቡ። ታሪኮቹን ለሕፃናት ከመተረኮ በፊት ሊመልሷቸው የሚገቡ ሶስት ዋና ዋና ጥያቄዎች እንዳሉ ያስታ ውሱ። እነዚህም፡-**

*1. የታሪኩ ዋና ጭብጥ ምንድን ነው?*
*2. ከዋናው ጭብጥ ጋር በቀጥታ የሚገናኙ የታሪኩ ክፍሎች የትኞቹ ናቸው?*
*3. ታሪኩ እንዲያምርና እንዲስብ የሚያደርጉት ዝርዝር የታሪኩ ክፍሎች የትኞቹ ናቸው?*

# ምዕራፍ 7

*የሚተርኳቸውን ታሪኮች በሚገባ ካጠኗቸው በኋላ የአተራረክ ጥበብን ማዳበር ያስፈልጎታል። ስለዚህም ታሪኮቹን ደጋግመው መተረክ፤ የድምጽን ቅላጼ ከሚተርኩት ታሪክ ሁኔታ ጋር ማጣጣምና የታሪኩን ድርጊት የሚገልጽ የአካል እንቅስቃሴ መለማመድ ይገባዎታል። ይሁንና የመተረኩ ዓላማ መልካም ባሕሪዎችንና ድርጊቶችን ለሕፃናት ለማስተማር እንጂ እንደቲያትር ተዋናይ ለማስመሰል እንዳልሆነ ማስታወስ አለብዎ። ስለዚህ ታሪኮቹን በደስታና ስሜት በተሞላበት መንገድ መተረክ ቢኖርብዎም ስሜትዎ እውነተኛ እንጂ የማስመሰል መሆን የለበትም። ሕፃናት ቅንነት የሌለበትን ነገር በቀላሉ መለየት እንደሚችሉ ማወቅ አለብዎት።*

*ታሪክ በሚተርኩ ጊዜ ለልጆቹ ታላቅ ፍቅር ሊሰማዎ ይገባል። በዚህም በእርስዎና በልጆቹ መካከል ልዩ የመቀራረብ ድባብ ይሰፍናል። ይህ ፍቅር የተሞላው ቅርርብ ለትረካዎ ልብ መስቀልና በድራማ ባህሪ ሙላት ጠቀሜታ ይኖረዋል። የድምጽዎ ከፍና ዝቅ ማለትና ቅላጼ ከታሪኩ ድርጊት ጋር አብሮ መቀያየር ይኖርበታል። የእጅዎ፣ የፊትዎ እና የሌሎች የሰውነትዎ አካሎች እንቅስቃሴ ከታሪኩ የተለያዩ ክንዋኔዎች ጋር መጣጣም ይገባቸዋል። ልጆች አሰልቺ የሆነ አንድ እንደሐውልት የቆመ ሰው የሚናገረው ትረካ አይስባቸውም። እንደ ደስታ፤ ሐዘን፤ ፍርሃትና ድፍረት የመሰሉ ስሜቶችን ድምጽን በመለዋወጥና በሰውነት እንቅስቃሴ ለልጆች ማስተላለፍ እንዲችሉ በደንብ ልምምድ ማድረግ አለብዎ።*

*የአተራረኮን ቅላጼያዊነትና (የድምጽ አወጣጥ) ፍጥነት አስቀድመው ማሰብ አለብዎ። በጣም ቀስ ብለው ቢተርኩ ሕፃናቱ ሊሰለቹ ይችላሉ። በጣም በፍጥነት ቢተርኩ ደግሞ ታሪኩን ማዳመጥ ሳይችሉ ይቀራሉ።*

*ለማጠቃለል፤ በጥሩ መንገድ ታሪክን ለመተረክ እንድንችል አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ብዙ ነገሮች አሉ። በዚህ ጥበብ ለመካን ከሁሉም በላይ ልምምድ ያስፈልጎታል። ስለዚህ በሚገባ ያጠኗቸውን ታሪኮች መተረክ ከሚገኙ ተሳታፊዎች ጋር በመሆን በተደጋጋሚ በመተረክ ይለማመዱ። ለትረካዎ ማማር አስተ ዋጽኦ ስለሚያደርጉ እንደ ድምጽዎ፤ የአካል እንቅስቃሴዎና ስሜቶችዎ ያሰላስሉ። ለትረካ ጥበብ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ተጨማሪ ነገሮችን ይዘርዙሩና ያብራሩ።*

________________________________________________________________

________________________________________________________________

# ምዕራፍ 8

አንዳንድ ሰዎች ስለጨዋታ የተሳሳተ ግንዛቤ አላቸው። በእውነቱ ጨዋታዎች ሕፃናት ብዙ ችሎታዎችን እንዲያዳብሩና ግንዛቤያቸው እንዲሰፋ ይረዳቸዋል። ለምሳሌ በጨዋታዎች አማካኝነት ልጆች መተባበርን፣ማተኮርንና እንቅስቃሴዎቻቸውን ማቀናጀትንና ሕግጋትን መታዘዝን ይማራሉ። ጨዋታዎች ሕፃናትን የማስተማሪያ ሌላው ስልት የሆነው ለዚህ ነው። ለማስተማሪያ የሚመረጡት አብዛኛዎቹ ጨዋታዎች የትብብር ጨዋታዎች መሆን አለባቸው።

በቤተሰብ ወይም በማኅበረሰብ አንድነትን ለማስፈን መተባበርና መረዳዳትን ማዳበር ይገባናል። በማህበረሰባችን ውስጥ ትብብር የለም እያልን ብዙ ጊዜ እናማርራለን። የትብብር ማነስ መንስኤው ሰዎች እንዴት መተባበር እንዳለባቸው አለመማራቸው ነው።

እንድንተባበር ከተፈለገ በመጀመሪያ የጋራ ግብ ሊኖረን ያስፈልጋል። ሁላችንም በሙሉ አንድ አይነት ውጤት ላይ ለመድረስ መሻት አለብን። ይሁንና ተመሳሳይ ግብ እንዲኖር ማድረግ ብቻ ለመልካም ውጤት አይበቃም። ከግቡ ለመድረስ እያንዳንዱ ተሳታፊ ለእቅዱ መሳካት የግሉን አስተዋፅኦ ማድረግ አለበት።

እያንዳንዱ ሰው የሚያደርገው አስተዋጽኦ ለጋራ ግብ መሳካት አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ አለበት።:: እጅግ አስፈላጊ ነው ሲባል ይጠቅማል ማለት ብቻ ሳይሆን የግድ ነው ማለትም ጭምር ነው። ስለዚህ የእያንዳንዱ ሰው አስተዋጽኦ ጠቃሚ ብቻ ሳይሆን የግድ አስፈላጊ ነው። እያንዳንዱ ሰው የድርሻውን ካላበረከተ ከግቡ ለመድረስ ላይቻል ይችላልና።

ትብብር ልናጤነው የሚገባ ሦስተኛ ጎን አለው። በሁሉም ተሳታፊዎች ዘንድ የጋራ ግብ መኖሩና መተባበራቸው በቂ አይደለም። እያንዳንዱ ተሳታፊ የሚያደርገው አስተዋጽኦ መቀናጀት አለበት። ለምሳሌ አንድ የሸቦ አጥር ለመስራት ሁለት ሰዎች መተባበር አለባቸው እንበል። ሁለቱም አጥሩን ለመስራትና ለመተባበር ፍላጎት አላቸው። ሆኖም አጥሩን ለምሥራት አንዱ ቅዳሜ ሲመጣ ሌላው ደግሞ እሁድ ይመጣል። አጥሩን ለመስራት ሁለቱም በአንድ ቀን መገኘት ስላለባቸው ግባቸውን መምታት አልቻሉም።

መረዳዳትን ለማዳበር መቀናጀት አስፈላጊ እንደሆነ ለመረዳት አንዳንድ ጊዜ ይከብዳል። አንድን ነገር ከብዙ ሰዎች ጋር በመተባበር ለመሥራት ሞክረው ሳያውቁ አይቀሩም። መቼም ከመካከላችሁ ለሥራው ሳይመጡ የሚቀሩ ሰዎች ይኖራሉ። በዚህ ምክንያት የመጡት ሰዎች ተስፋ ይቆርጡና ሥራውን ሳይጨርሱ ምናልባትም ሳይጀምሩ ይበተናሉ። ወይም አንዳንዶቹ አርፍደው ይመጣሉ። ቀድመው የመጡትም ያልመጡትን በመጠበቅ ይሰለቹና ይሄዳሉ ወይንም የሥራ ስሜታቸውና ንቃታቸው ይደክማል።

የትብብር ጨዋታዎች ሕፃናት የመረዳዳትን አስፈላጊነት እንዲያዳብሩ ይረዳቸዋል።

1. የጨዋታው ዓላማ የጋራ ግብ እንዲኖር ያደርጋል

2. ግባቸው ላይ ለመድረስ ሲጥሩ ሕፃናቱ መተባበርንና፣ ጥረቶቻቸውን ማቀናጀት ይማራሉ።

ገና በመጀመሪያው ጨዋታ ሕፃናቱን መረዳዳት የሚችሉባቸውን መንገድ ማስተማር አይቻልም። ሕፃናቱ የመረዳዳትን አስፈላጊነት እስኪገነዘቡ ድረስ ጨዋታዎቹን መደጋገም ያስፈልጋል።

## ጥያቄዎች

1. ስለ ትብብር ጨዋታዎች ጥቅም ሃሳቦን ይግለጹ?

______________________________________________

______________________________________________

*2. የትብብር ጨዋታዎች ከሌሎች ጨዋታዎች እንዴት ይለያሉ?*

________________________________________________

________________________________________________

*3. ስለፉክክር ጨዋታዎች ምን ሃሳብ አሎት?*

________________________________________________

________________________________________________

*6.  ጨዋታዎች በሕፃናት ላይ ምን ለውጥ እንዲያመጡ ይፈልጋሉ?*

________________________________________________

________________________________________________

## *ምዕራፍ 9*

*ጨዋታዎቹን ለህፃናት በደንብ ለማስተማር እንዲችሉ እርስዎ እራስዎ የጨዋታዎቹን አጨዋወትና ዓላማ በሚገባ ማወቅ ይኖርብዎታል። ይህም ለማድረግ ጨዋታዎቹን ደጋግሞ በመጫወት መለማመድ ያስፈልጋል። ስለዚህ በዚህ ክፍል-ምዕራፍ ውስጥ በ15 የሕፃናት ትምህርቶች ውስጥ የተካተቱትን ጨዋታዎች አብረዎት ካሉት ተሳታፊዎች ጋር በመሆን በመጫወት ቢለማመዱት ይረዳ ዎታል።*

## *ምዕራፍ 10*

***አንድን ጨዋታ ለልጆች ለማስተማር አስተማሪው ከዚህ በታች ያሉትን ሦስት ነገሮች በሚገባ ማከናወን አለበት፡-***

1. *የጨዋታውን ዓላማ በግልጽ ማስረዳት*
2. *ጨዋታውን እንዴት መጫወት እንደሚቻል ህፃናቱ መረዳታቸውን ማረጋገጥ*
3. *ጨዋታውን ሲጨርሱ የስኬታማነት ስሜት እንዲሰማቸው ማድረግ።*

*አስተማሪው የጨዋታውን ዓላማ የሚያስረዳበት መንገድ የልጆቹን ስሜት ለማነሳሳት ወሳኝ ነው። ልጆቹ ለመጫወት እንዲጓጉ አስተማሪው የደስታና የማሸነፍ ፍላጎት በውስጣቸው ማሳደር አለበት። ሕፃናቱን ከማነሳሳት በተጨማሪ ስለጨዋታው ዓላማ በሚገባ ካስረዳቸው በሚፈለገው ሁኔታ ጨዋታውን ለመጫወት ይገፋፋሉ። ለምሳሌ በ5ኛው ትምህርት ውስጥ በሚገኘው "ሕሙማንን መርዳት" በተሰኘው ጨዋታ "የታመመን ሰውን" ወደ "ጤና ጣቢያ" ለመውሰድ መሸከሚያ የሚሆን መቀመጫ ለመስራት ሁለት ልጆች እጅ ለእጅ ይያያዛሉ። በቂ ማብራሪያ ካልተደረገላቸው "የታመመው" ጓደኛቸውን መጣል ተሸክሞ ከማድረሱ ይበልጥ የሚያዝናና ነው ብለው ሊያስቡ ይችላሉ። ይህ እንዳይሆን አስተማሪው፡- "ልጆች ዛሬ ሕሙማንን መርዳት የተሰኘ መልካም ተግባርን የሚያሳይ ጨዋታ እንጫወታለን። በጨዋታው የታመመ ሰውን ወደ ጤና ጣቢያ ለመውሰድ መተባበር ይኖርብናል። የታመመውን ሰው መንገድ ላይ ከጣልነው ስለሚጎዳ መጠንቀቅ አለብን። ጤና ጣቢያ ያለምንም ችግር ቶሎ ካደረስነው ግን  እንዲድን ስለረዳነው በጣም እንደሰታለን በስራችንም እንረካለን።" ብሎ ማብራራት አለበ።*

*መልመጃዎች*

1. አስተማሪው አዲስ ጨዋታ ለሕፃናቱ ሲያስተዋውቅ በሚገባ ማድረግ የሚገባውን ሁለት ነገሮች ይጥቀሱ::

ሀ. ______________________________________________________________

______________________________________________________________

ለ. ______________________________________________________________

______________________________________________________________

2. የሚያውቁትን ሦስት ጨዋታዎችን አብረዎት ለሚያጠኑ ጓደኞችዎ ማስተዋወቅን ይለማመዱ

3. ምንም እንኳን ጨዋታውን ከዚህ በፊት የሚያውቁት ቢሆንም፤ ህፃናቱ እንዲጫወቱ ማነሳሳት የጨዋታውንም ዓላማ ማብራራት የግድ አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው?

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

## ምዕራፍ 11

ልጆቹ የጨዋታውን ዓላማ ከተረዱና ለመጫወትም ከተነሳሱ በኋላ ጨዋታውን እንዴት መጫወት እንደሚችሉ በግልጽ ማስረዳት አስፈላጊ ከሆነም በመጫወት ማሳየት ይኖርብዎ ይሆናል:: ለምሳሌ በ4ኛው ትምህርት ውስጥ ያለውን “ድልድይ” የተሰኘውን ጨዋታ ለማጫወት ለልጆቹ ለማስ ረዳት ረጋ ባለ ሁኔታ የአጨዋወቱን ቅድመ-ተከተል ሊያሳዩአቸው ይችላሉ:: አንዳንድ ጊዜ በዕድሜ አነስ ያሉ ሕፃናትን በማጫወት ከፍ ያሉት ደግሞ በመቀጠል ማስከተል ይቻላል:: ሁሉንም ሕፃናት በአንድ ጊዜ “ድልድይ” ጨዋታን ከመጫወታቸው በፊት የተወሰኑ ሕፃናትን ሁለት ሁለት በማድረግ ማለማ መድ ይበጃል:: አጨዋወቱን በዚህ መንገድ ለሕፃናቱ ካሳዩ በኋላ “ድልድይ” ላይ የሚወጡትን ሕፃናት ቁጥር ሁሉም ሕፃናት እስኪሳተፉ ድረስ ቀስ በቀስ መጨመር ይቻላል:: አጨዋወቱን ለሕፃናቱ በሚ ያስረዱ ጊዜ በተግባር ማሳየትና ከእነርሱ ጋር መጫወትም ያስፈልጋል::

## ምዕራፍ 12

ልጆቹ ሲጫወቱ የስኬታማነት ስሜት እንዲሰማቸው ማድረግ አስፈላጊ ነው:: በዚህ ረገድ አስተማሪው ከፍተኛ ሚና ሊጫወት ይገባል:: በጨዋታ ጊዜ ማበረታታት፣ ጨዋታውን በትክክል ሲያካሄዱ ሊያጨበጭብላቸውና በአጠቃላይ ለተገቢው ስራቸው የሚሰማውን ደስታ በግልጽ ማሳየት አለበት::

ልጆች የስኬታማነት ስሜት በውስጣቸው ሲያድር በስነ-ልቦና ያድጋሉ:: በችሎታቸው መተማመን ይጀምራሉ፣ አዲስ እና አስቸጋሪ ነገሮችን ለመሞከር ድፍረት ያዳብራሉ:: ከሌሎች

ጋር በወዳጅነት የመቀላቀል አመለካከት ያዳብራሉ:: ለጨዋታ ሕጎች የመታዘዝ ፍላጎታቸው ይጠነክራል:: ይህንንም ፍላጎት ቤተሰብን እና አምላክን ወደ መታዘዝ እንዲያድግ ማድረግ ይቻላል:: የስኬታማነት ስሜት እምቅ ችሎታዎቻቸውን ሁሉ በተቻለ መጠን ተጠቅመው ውጤት የመቀዳጀትን ፍላጎት ያጠነ ክራል::

## ለውይይት የቀረቡ ጥያቄዎች

1. የልጆቹ የስኬታማነት መንፈስ እንዲዳብር አስተማሪው ምን አስተዋጽኦ ማድረግ ይችላል?
2. ልጆቹ ያለመቻል ወይም ያለመሳካት ስሜት እንዲያድርባቸው አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የአስተማሪው ምግባራት ወይም ባህሪያትን ይግለጹ
3. ልጆቹ የስኬታማነት መንፈስ እንዲያዳብሩ ጨዋታውን በሚገባ መጫወት አለባቸው ማለት መሳሳት የለባቸውም ማለት ነው?
4. የልጆቹ የስኬታማነት መንፈስ እንዲዳብር አስተዋጽኦ ለማድረግ አስተማሪው ከተጠቀመባቸው ሊጠቀመባቸው ከሚገባ አነጋገሮችና ባሕሪዎች መካከል ጥቂቶቹን ይግለጹ::

# ምዕራፍ 13

ለልጆች ትምህርት የምንጠቀምበት ሌላው ስልት ስዕሎችን ቀለም እንዲቀቡ መርዳት ነው:: ለነገሩ ይህ ከሁሉም የበለጠ ሕፃናት የሚወዱትና የሚናፍቁት ክፍል-ጊዜ ነው:: ስዕሎችን ቀለም መቀባት የሕፃናቱን ትኩረት ሊስብ የቻለበት ምክንያት የስነ-ጥበብ ችሎታዎቻቸውን ለመፈተንና የውበት ግንዛቤዎቻቸውን ለማዳበር ዕድል ስለሚያገኙ ይሆናል:: የስነ-ጥበብ መዳበር በሕጻናት ትምህርት ውስጥ እጅግ አስፈላጊ ነው:: የትምህርቱ ደረጃ እየጨመረ ሲሄድ የሕፃናቱን የሥነ-ጥበብ ችሎታ ሊያዳብሩ የሚችሉ የበለጠ ሰፋ ያሉ እንቅስቃሴዎችን ማከናወን ይኖርብዎታል:: ለአሁኑ የተሰጡትን ስዕሎች በነፃነት ቀለም እንዲቀቡ ሕፃናቱን መተው ይበቃል::

ለእያንዳንዱ የትምህርት ክፍለ ጊዜ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ካሉት ስዕሎች ተስማሚውን በመምረጥ፤ በሕፃናቱ ቁጥር ልክ ማባዛት ያስፈልጋል:: ስዕሎቹን መቀቢያ ቀለም ሕፃናቶቹ ከቤታቸው ይዘው ይመጡ ይሆናል:: አለበለዚያ ለሁሉም ሕፃናት የሚያስፈልገውን ቀለም መግዣ የሚሆን ገንዘብ ቤተሰቦች ሊያዋጡ ይችላሉ:: በዚህ ጊዜ ቤተሰቦቹ መዋጮ እንዲያደርጉ በመጠየቅ መንፈሳዊ ጉባዔዎ ያለ ጥርጥር ትብብር ያደርግልዎታል:: በተጨማሪም እንደያካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ አስፈላጊውን ቁሳቁስ መጠቀም ይችላሉ::

## ስለስዕል መቀባት ክፍለ-ጊዜ የበለጠ እንዲገነዘቡ የሚከተሉትን ዓረፍተ-ነገሮች እውነት ወይም ሐሰት መሆናቸውን ይለዩ::

1. ሕፃናት ያላቸውን ስዕል መቀቢያ ቀለም መዋዋስ አለባቸው:: እ □ ሐ □
2. ሕፃናቱ ጥርት አድርገው ስዕሎቹን መቀባት እስኪችሉ ድረስ በመጀመሪያ አካባቢ ከመስመር ውጭ ቢቀቡ ምንም አይደለም እ □ ሐ □
3. አንድ ሕፃን ጥሩ አድርጎ መቀባት ካልቻለ ስዕሉን ከእርሱ ነጥቆ ለሌላ ሕፃን መስጠት አለበት እ □ ሐ □
4. ሕፃናቱ ስዕል በሚቀቡ ጊዜ አስተማሪው እረፍት ሊወስድ ይችላል:: እ □ ሐ □
5. ሕፃናቱ ስዕል በሚቀቡ ጊዜ አተማሪው እየተዘዋወሩ ሊረዷቸውና

ሊያበረታቷቸው ይገባል። እ □ ሐ □

6. ሕፃናቱ ስዕል በሚቀቡ ጊዜ ፀጥታ ማክበር አለባቸው። እ □ ሐ □

7. ስዕሉን ለሕፃናቱ ከማደል በፊት አስተማሪው የስዕሉን መልእክት ማስተዋወቅ አለበት። እ □ ሐ □

8. አስተማሪው አንድ መልካም ነገር ለማስተማር የሚረዳ በስዕሉ ላይ የተሞረከዘ ታሪክ ፈጥሮ ቢተርኩላቸው ጥሩ ነው። እ □ ሐ □

# አሥራ አምስት የልጆች ትምህርት ክፍለ-ጊዜዎች

## *ትምህርት 1*

*መለኮታዊ ቡራኬን ለመሳብና መንፈሳዊ ድባብ ለማስፈን የትምህርት ክፍለ-ጊዜውን በፀሎት ይጀምሩ:: ከዚህ ቀጥሎ የተሰጠውን ፀሎት ለትምህርቱ መክፈቻ እንዲያደርጉት ይመከራሉ::*

> **"አምላክ ሆይ! እነዚህን ህፃናት አስተምራቸው፤ እነዚህ ህፃናት የአትክልት ሥፍራህ ተክሎች፤ የመስክህ አበባዎች፤ የአትክልት ቦታህ ጽጌረዳዎች ናቸው:: ዝናብህ እንዲዘንብላቸው፤ የእውነት ፀሐይ ከፍቅርህ ጋር እንዲበራላቸው አድርግ:: ይሠስጥ፤ ያድጉና ይዳብሩ፤ በከፍተኛ ውበትም ይታዩ ዘንድ የአንተ ልዝብ ነፋስ እንዲያድሳቸው ፈቃድህ ይሁን:: አንተ ሰጪው ነህ? አንተ ሩኅ ሩኅህ ነህ::" [4]**

*ከፀሎቱ በኋላ ልጆቹ በቃላቸው የሚያውቁት ፀሎት እንዳለ ይጠይቋቸው:: ቀጥለውም የሚከተለውን ፀሎት በምእራፍ 2 እና 3 በተወያየነው ዘዴ መሰረት በቃላቸው እንዲይዙ ይርዷቸው::*

> **"አምላኬ ሆይ፣ ምራኝ፣ ጠብቀኝ፣ ብሩህ መብራትና አንጸባራቂ ኮከብ አድርገኝ:: አንተ ኃያሉና ኃይል የተመላው ነህና ::"[2]**

*በዚህ ክፍለ ጊዜ ውስጥ ልጆቹ ፀሎቱን ሙሉውን አለበለዚያም የተወሰነውን የፀሎቱን ክፍል በቃላቸው ይይዛሉ ተብሎ ተስፋ ይደረጋል:: ልጆቹ በቃላቸው መያዝ ከተለማመዱ በኋላ ወደ ሚቀጥለው ትምህርት ማለፍ ይቻላል:: የሚቀጥለውም አንድን መዝሙር መዘመርን መማር ነው::*

*<u>የውቅያኖስ ጠብታዎች</u>*

*ሁላችንም የአንድ ውቅያኖስ ጠብታዎች*
*ሁላችንም የአንድ ዛፍ ቅርንጫፎች ነንና*
*የአምላክ ልጆች እኛ ለአንድነት ስንጥር*
*እናንተም ተነሱ በትብብር*
*ይህ የሕይወት ዓላማ ነው የመኖር::*
*አንድ ሃገር ናት ምድር*
*አንድ ነው የሰው ዘር*
*እኛ ለአንድነት ስንጥር*
*እናንተም ተነሱ በትብብር*
*ይህ የሕይወት ዓላማ ነው የመኖር*

*ከመዝሙሩ ትምህርት በመቀጠልም ከባሃኢ ቅዱሳን ጽሑፎች የተወሰደን አንድ ጥቅስ በቃል እንዲይዙ ይርዷቸው:: የሚከተለውን ማብራሪያ በሚገባና በሚስብ መንገድ ለሕፃናቱ ማስረዳት ይችላሉ::*

*የባሃኢ እምነት ዋና አላማ የሰው ልጆች አንድነት ማስፈን ነው:: በአንድነት ለመኖር ስንጥር ሁሉንም ሰው እንደወንድምና እህታችን እንመለከታለን:: በተለይ በምንኖርበት ማኅበረሰብ ውስጥ እንደዚህ ማድረግ በጣም አስፈላጊ ነው:: ባሃኢዎች ክርክርና ፀብ ውስጥ አይገቡም:: በአንድነት ለመኖር እንዲረዳን የሚከተለውን የባሃኡላህን ጥቅስ በቃል እንያዝ::*

> **"የአንድነት ብርሃን በጣም ኃይል የተመላ ስለሆነ መላውን ምድርን ለማብራት ይችላል::"[5]**

ልጆቹ በመጀመሪያ ጥቅሱን ቢረዱት በቀላሉ በቃላቸው ሊይዙት ይችላሉ፡፡ የጥቅሱን ትርጉም የተረዱትን ያክል እንዲናገሩ ቢያበረታቷቸው በጣም ይረዳቸዋል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ምናልባት ለእነርሱ አዲስ ሊሆኑ የሚችሉ ቃላት ተዘርዝረዋል፡፡ የእነዚህንም ቃላት ትርጉም ለመረዳት የሚያስችላቸውን አረፍተ ነገሮች አብረው ተሰጥተዋል፡፡

## በኃይል የተሞላ

- ኩማር ያነበበው ግጥም ልብን የሚነካ ከመሆኑ የተነሳ አስለቀሰን፡፡ ጥቅሱ "ታላቅ ኃይል" ነበረው፡፡
- የፀሐይ ጨረሮች ለምድር ሙቀት የሚሰጡና የሁሉም ነገሮች ህይወት መሰረት ናቸው፡፡ የፀሐይ ጨረሮች "በኃይል የተሞሉ" ናቸው፡፡

## ማብራት

- መብራቱን ከማብራታችን በፊት ክፍሉ ጨልሞ ነበር፡፡ "መብራቱ" ክፍሉን አበራው፡፡
- ፀሐይ በማለዳ ትወጣና ብርሃኗን በምድርና በባህር ላይ ትፈነጥቃለች፡፡ ፀሐይ ምድርንና ባህርን በብርሃን "ማብራት" ትችላለች፡፡

ሕፃናቱ ጥቅሱን በቃላቸው ከያዙና ስለአንድነት አስፈላጊነት እንዲገነዘቡ ከረዷቸው በኋላ አብዱል-ባሃ ለአንድነት ምን ያህል ቦታ እንደሚሰጥ የሚገልጽ ታሪክ ሊተርኩላቸው ይችላሉ፡፡ በምእራፍ 5፣6 እና7 እንደተብራራው የታሪኩን ጭብጥ፤ ከጭብጡ ጋር በቀጥታ ግንኙነት ያላቸውን የታሪኩን ክፍ ሎችና በማጠቃለያው ላይ ትኩረት በመስጠት ሕፃናቱ ታሪኩን እንዲረዱት ያድርጉ፡፡ የታሪኩ ጭብጥ ምንድን ነው? ከታሪኩ ውስጥ የትኛው ክፍል ነው ከጭብጡ ጋር በቀጥታ የሚገናኘው? ታሪኩን ማራኪ የሚያደርጉት ዝርዝር ክንዋኔዎች የትኞቹ ናቸው? የተሰኙ ጥያቄዎችን ታሪኩን ከመናገርዎ በፊት መክ ለስ በጣም ይጠቅሞታል፡፡

## የእለቱ ትረካ

ባሃኦላህና አብዱል-ባሃ በሕይወት በነበሩበት ጊዜ አብዛኛው የአቆር ሕዝብ ስለባሃኢዎች የተሳሳተ አመለካከት ነበራቸው፡፡ ስለዚህም ባሃኢዎችን እጅግ በጣም ይቃወሟቸው ነበር፡፡ ይሁንና አብዱል-ባሃ በታላቁ ፍቅሩና ጥበቡ የብዙ የአቆር ሕዝቦችን ልቦች ለውጧል፡፡ ለሁሉም ሃይማኖቶች ተከታዮች ደግነትን አሳይቷል፤ አንድነትን እንዲያዳብሩ ረድቷቸዋል፡፡

እንደመሰል የሐገሩ ሕዝብ ባሃኢዎችን የማይወድ አንድ ክርስቲያን ነጋዴ ነበር፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ይህ ነጋዴ ባለቤትነቱ የባሃኢዎች የሆነ ከሰል ግመል ላይ ተጭኖ ያያል፡፡ የግመሉንም ነጂ ያቆምና "ይህ እኔ ላገኝ ከምችለው ከሰል የተሻለ ነው፡፡" በማለት የባሃኢዎቹን ከሰል ይዘርፋል፡፡

አብዱል-ባሃ ይህንን በሰማ ጊዜ ከሰሉን እንዲመልስ ለመጠየቅ ወደ ነጋዴው ሱቅ ሄደ፡፡ ሱቁም በደረሰ ጊዜ ነጋዴው አብዱል-ባሃን ሊያነጋግረው አልፈለገም፡፡ አብዱል-ባሃ በትእግስት ጠበቀው፡፡ ከሦስት ሰዓታት በኃላ ነጋዴው ወደአብዱል-ባሃ ፊቱን አዙሮ በግዴለሽነት "ከእስረኞቹ መካከል አንዱ ነህ? ለመሆኑ ምን አድርገህ ነው የታሰርከው?" ሲል ጠየቀው፡፡ አብዱል-ባሃም እርሱ የፈጸመው ወንጀል ክርስቶስ ከፈጸመው ወንጀል ጋር አንድ አይነት እንደሆነ ነገረው፡፡ ነጋዴውም ተደነቀ፡፡ "ለመሆኑ ስለክርስቶስ ምን ታውቃለህ?" ሲልም ጠየቀው ከዚያም አብዱል-ባሃ በእርጋታና በፍቅር ስለ ክርስቶስ ታላቅነትና ትምህርት ሲናገር የነጋዴው ልብ ራራ፡፡ ኩራቱና ጀብደኝነቱም ጠፋ፡፡ በመጨረሻም "ከሰሉን ሸጬዋለሁ፡፡ ይሁንና ዋጋውን በደስታ እከፍላለሁ፡፡" ሲል ነጋዴው ለአብዱል-ባሃ ነገረው፡፡ ከዛም አብዱል-ባሃ ነጋዴውን ሊሰናበተው ተነሳ፡፡ ነጋዴውም በታላቅ አክብሮትም እስከ ዋናው መንገድ ድረስ ሸኘው፡፡

### ቀጣዩ ክፍለ ጊዜ የጨዋታ ነው፡፡ የዚህ ክፍለ-ጊዜ ጨዋታ መጠሪያ "ግዙፎቹ" የተሰኘ ነው፡፡

ሁለት ልጆች ጎን ለጎን ይቆማሉ፡፡ የአንዱ ልጅ የግራ እግር ከሌላው ልጅ የቀኝ እግር ጋር ይታሰር፡፡ ከዚያም ከአንድ የተወሰነ ቦታ ወደ ሌላ ይራመዱ፡፡

ጨዋታውን በሚከተሉት መንገዶች መጫወት ይቻላል::

- ሦስት፣ አራት ወይም ከዚያም በላይ የሆኑ ልጆች እግራቸው ከላይ በተጠቀሰው መልኩ ይታሰርና በአንድ ላይ ለመራመድ ይሞክሩ::
- ጉዳት እንዳይደርስባቸው በመጠንቀቅ መሰናክል ሊሆኑ የሚችሉ አነስ ያለ እንጨትና ድንጋይ በመንገዳቸው ላይ ይደቀኑባቸው::
- አንዳንድ ጊዜም ከመራመድ ይልቅ በአንድነት እንደ እንቁራሪት ይዝለሉ::
- የጨዋታው ዓላማ አንድነትን የማያስተምር መሆኑን ያብራሩ::

***የዕለቱ ትምህርት ከማብቃቱ በፊት ለእያንዳንዱ ልጅ አንድ ስዕል ይሰጠውና ቀለም ይቀባ::***

# *ትምህርት 2*

***የዕለቱን ትምህርት የሚከተለውን ፀሎት በመድገም እንዲጀምሩ ይመከራሉ::***

> **"አምላክ ሆይ! ይህን ጨቅላ ሕፃን በፍቅርህ ጉያ ተንከባከበዉ ከመለኮታዊ ጠባቂነትህም ጡት ወተት ስግሰው:: ይህን ስጋ ቡቃያ በፍቅርህ የጽጌረዳ አትክልት ሥፍራ ውስጥ ኮትኩተህ አሳድገዉ ከጸጋህም በሚወርደው ዝናብ እንዲያድግ እርዳው:: የመንግሥተ ሰማይ ልጅ አድርገዉ ወደ መንግሥተ ሰማያዊው ዓለምህም ምራው:: አንተ ኃይል የተመላህና ደግ ነህ? አንተ ሰጪዉ ቸሩ የተትረፈረፈ በረከት ባለቤት ነህና::"[6]**

*ሕፃናቱ በቃላቸው ያድርጉ የሚያውቁትን አንድ ፀሎት እንዲፀልዩ ያድርጉ:: ቀጥሎም ባለፈው ትምህርት በቃላቸው ማጥናት የጀመሩትን ፀሎት እንዲከልሱ ይርዷቸው::*

***ከዚህ የሚቀጥለው ሁለት መዝሙሮችን መዘመር ነው:: አንዱ ባለፈው ትምህርት የተማሩት ሲሆን ሌላው ግን አዲስ ነው::***

*<u>የመጀመሪያው ምክሩ</u>*

*የሚጣራ ድምፁን ስማ<br>ልብን በሚያስደስት ዜማ፣<br>የመጀመሪያ ምክሩ<br>ልብ ይኑርህ ንጹህ<br>አንጸባራቂና ሩህሩህ፣<br>የሃብት መዝገብ ነው ልብ<br>ከልብ ያለፈ ስጦታ<br>ቸርነቱ የጌታ፣<br>ጠበቀው ከጥፋት<br>ከሚያጠፋ ዓለማዊ እሾት፣<br>በነፃም ወደ ጌታ ይምጠቅ<br>በመንፈሳዊ ህልውናህ ይሳቅ::*

*ከመዝሙሮቹ በኋላ ሕፃናቱ ከባሃኦላህ ጽሑፍ የተወሰደውን ጥቅስ በቃላቸው እንዲይዙ ይርዷቸው:: በቅድሚያ ግን ጥቅሱን በሚከተለው መንገድ ሊያብራሩላቸው ይችላሉ::*

*ልባችን እንደመስታወት ነው:: ሁልጊዜ ንጽሕናውን ልንጠብቅ ይገባል:: ጥላቻ፣ ቅናትና መጥፎ ሐሳቦች ልባችን እንዳያንጸባርቅ የሚያግዱ አቧራዎች ናቸው:: ልቦቻችን ንጹህ በሚሆኑ ጊዜ የአምላክን ብርሃን ያንፀባርቃሉ:: ስለሆነም ሌሎችን ሰዎች ማስደሰት እንችላለን:: ልባችን ንጹሕ ሆነው እንዲቆዩ እንዲረዳን የሚከተለውን የባሃኦላህ ጥቅስን በቃላችን እንያዝ::*

**"የመንፈስ ልጅ ሆይ! የመጀመሪያ ምክሬ ይህ ነው፣... ንጹህ ሩህሩህና አንጸባራቂ ልብ ይኑርህ::"[7]**

## ምክር

- አንድ ቀን ጄራርድና ሜሪ ስዕሎችን ቀለም እየቀቡ ነበር፡፡ ጄራርድ ቢጫ ቀለም ፈልጎ ሜሪን ቢጠይቅ ልትሰጠው አልፈለገችም፡፡ ሜሪ ቢጫውን ቀለም ጄራርድ እንዲጠቀምበት እንድትሰጠው መምህሯ ነገሯት፡፡ መምህሯ ለሜሪ መልካም ምክር ለገሷት፡፡
- ፓትሪሻ በገንዘቧ ዳቦ ትግዛ፣ ወይስ መጽሐፍ፣ ልትወስን አልቻለችም፡፡ ቤተሰቦቿ መጽሐፍ እንድትገዛ መከሯት፡፡ የፓትርሻ ቤተሰቦች ለፓትርሻ መልካም ምክር ለገሷት፡፡

## ይኑራችሁ

- ጤናዬ ከመተኛቷ በፊት ፀሎት ማድረግ ትወዳለች፡፡ ፀሎቶቹን የምታነበው ከአንዲት ትንሽ የፀሎት መጽሐፍ ነው፡፡ ጤናዬ አንዲት ትንሽ የፀሎት መጽሐፍ አላት፡፡ ሁላችንም የፀሎት መጽሐፍ እንዲኖረን ያስፈልጋል፡፡
- ጎርፍ መጣና ሰዎች ያላቸውን ንብረት በሞላ ጠራርጎ ወሰደባቸው፡፡ ይሁንና ጓደኞቸው በቶሎ ደርሰው የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ረዷቸው፡፡

## ንፁህ ልብ

- ካቲ በጣም ተናዳ ፋናን ተቆጣቻት፡፡ ሱዛን ብታዝንባትም ወዲያውኑ ካቲን ይቅር አለቻት፤ ካቲ ንፁህ ልብ አላት፡፡

- ጆርጅ ዳቦውን ከጓደኞቹ ጋር መካፈል ያስደስተዋል፡፡ ድንጋይ ለሚወረውርበት ጉስታቮ እንኳን ሳይቀር ዳቦውን ያካፍላል፡፡ ጆርጅ ንጹህ ልብ አለው፡፡

## ሩህሩህ ልብ

- የተቸገሩ ሰዎች ስታገኝ (ሲያጋጥሟት) ሚንግ ሊንግ ትንከባከባቸዋለች(ትረዳለች)፡፡ ሚንግ ሊንግ ሩህሩህ ልብ አላት፡፡
- አቶ ሮበርትሰን ሽማግሌ ናቸው፡፡ እርሳቸው ለሽያጭ ያዘጋጁትን በቀሎ ጂሚ ተሸክሞ ገበያ ያደርስላቸዋል፡፡ ጂሚ ሩህሩህ ልብ አለው፡፡

## አንፀባራቂ ልብ

- እናቴ ስከፋ ሁልጊዜ ታጽናናኝና ደስተኛ እንድሆን ታደርገኛለች፡፡ እናቴ አንፀባራቂ ልብ አላት፡፡
- ኦቡያ በጠና ስለታመመ አልጋ ላይ ተኝቶ ነው የሚውለው፡፡ ይሁንና ፀሎቱን ለመፀለይ ከተኛበት በመነሳቱ፤ ሳይከፋና ደስተኛ እንደሆነ ይፀልያል፡፡ ኦቡያ አንጸባራቂ ልብ አለው፡፡

ሕፃናቱ ፀሎቱን በቃላቸው ካጠኑ በኋላ አንድ ታሪክ ሊተርኩላቸው ይችላሉ፡፡ እንደተለመደው የተለያዩ የታሪኩን ክንዋኔዎች በአእምሮ ግልጽ ከሆነልዎ በኋላ ታሪኩን በደስታና በቅንነት ለሕፃናቱ ቢተርኩላቸው ታሪኩን በተሻለ መንገድ ይረዱታል፡፡

# የእለቱ ትረካ

ሰዎች በልባቸው ምን እንደሚያስቡ አብዱል-ባሃ በቀላሉ ያውቅ ነበር፡፡ ንጹህና ብሩህ ልብ ያላቸውን ሰዎች በጣም ይወዳል፡፡ በአብዱል-ባሃ እራት የመጋበዝን ክብር ያገኘች አንዲት ሴት ነበረች፡፡ በእራት ግብዣው ላይ ከእነርሱ አንደበት የሚፈልቀውን የጥበብ ቃል እያዳመጠች ቁጭ ብላ ሳለ በውሃ የተሞላ ብርጭቆን ተመልክታ "አብዱል-ባሃ ከልቤ አስማዊ ፍላጎቶችን አውጥቶ በምትኩ እንደዚህች ብርጭቆ ልቤን በመለኮታዊ ፍቅርና መረዳት ቢሞላልኝ ኖሮ!" ስትል ተመኘች፡፡

ይህ ሐሳብ በአእምሮዋ የቆየው ለአጭር ጊዜ ነበር፡፡ ሐሳቧንም ለማንም አላካፈለችም፡፡ ጥቂት ቆይቶ ግን ስለምን ታስብ እንደነበር አብዱል-ባሃ እንዳወቀ የሚያመለክት ነገር ተፈጠረ፡፡ በንግግሩ መሐል አንድ አገልጋዩን ጠራው፡፡ ከዚያም በፋርስኛ አዘዘው፡፡ አገልጋዩም ሴትዮዋ

ወደተቀመጠችበት ሄዶ ለእርሷ በቀረበው ብርጭቆ ውስጥ ያለውን ውሃ አፍስሶ ባዶውን ብርጭቆ መልሶ ከፊቷ አስቀመጠው::

ጥቂት ቆይቶ አብዱል-ባሃ በንግግሩና በጨዋታው መሐል በጠረጴዛው ላይ ያለ የውሃ ማንቆርቆሪያ አንስቶ የሌሎችን አትኩሮት በማይስብ መንገድ የሴትዮዋን ባዶ ብርጭቆ በዝግታ ሞላው:: ምን እንደተፈጠረ ማንም ያወቀ አልነበረም:: ይሁንና አብዱል-ባሃ የልቧን ምኞት እያሟላ እንደሆነ ሴትዮዋ ተገነዘበች:: በደስታም ተሞላች በዚህም ልብና አእምሮ እንደተከፈተ መጽሐፍ ለአብዱል-ባሃ ግልጽ እንደሆኑና በታላቅ ፍቅርና ደግነት እንደሚያነባቸው አወቀች::

**የሚቀጥለው እንቅስቃሴ "የውኃ ጥም" የተባለ ጨዋታ ነው::**

እጆቻቸውን እንዳያጥፉ የልጆቹ ክርን በእንጨት ይታሰር:: ከዚያም ህፃናቱ በበረሃ ውስጥ እንደሚጓዙና በጣም በጣም ውሃ እንደተጠሙ ያስመስሉ:: ከዚያም ውሃ በኩባያ የሚሰጣቸው ሰው አገኙ:: እጃቸውን ማጠፍ ስለማይችሉ ውሃውን አንስተው ለመጠጣት የሚችሉበትን ዘዴ መፈለግ አለባቸው:: (በመጨረሻም ያላቸው አማራጭ አንዱ ሌላውን ማጠጣት እንደሆነ ይደረሱበታል:: አንዱ ሌላውን ሲያጠጣ እንዳያፈስ መጠንቀቅ ይኖርበታል::)

**የእለቱን የትምህርት ክፍለ ጊዜ ለማጠቃለል ለእያንዳንዱ ልጅ ስዕል ቁጥር 2 ይሰጠውና ቀለም ይቀባ::**

# ትምህርት 3

እያንዳንዱን ክፍለ ጊዜ በፀሎት የመጀመርንና ሕፃናቱ በቃላቸው የሚያውቋቸውን ፀሎቶች እንዲፀልዩ የመጠየቅን ጠቀሜታ ሳይገነዘቡ አይቀሩም:: ይህንን ማድረጋቸው ማንኛውንም ተግባር ከመጀመራቸው በፊት የአምላክን እርዳታ የመለመንን ባህል (ልምድ) ቀስ በቀስ እንዲያዳብሩ ይረዳቸ ዋል:: የእለቱን ትምህርት ለመጀመር የሚከተለውን ፀሎት ይጸልዩ:-

**"አቤቱ ጌታዬ ሆይ! ውበትህ ሕብስቴ፣ የአንተ ቅርበት ብርሃንም ጽዋዬ፣ የአንተም ፍሳጎት ተስፋዬ፣ አንተን ማወደስም ሥራዬ፣ አንተን ማስታወስም ባልደረባዬ፣ የአንተ ሉዓላዊነትም እርዳታዬ፣ የአንተ መኖሪያ ሥፍራም መኖሪያ ቦታዬ፣ ልክ በግርዶሽ እንደተከለሉ ከአንተ ከተዘጉት ሰዎች ገደቦች በላይ ከፍ ያደረግከው መኖሪያ ሥፍራም መኖሪያ ቤቴ እንዲሆንልኝ ፈቃድህ ይሁን::**

**በእውነቱ፣ አንተ የሥልጣን፣የብርታትና የክብር አምላክ ነህና::"**[8]

ቀጥሎም ሕፃናቱ ከዚህ በፊት ከሚያውቋቸው ፀሎቶች መካከል እንዲፀልዩ ከተደረገ በኋላ ባለፉት ሁለት ክፍለ-ጊዜዎች በቃል ያጠኗቸውን ሁለት ፀሎቶች ይከልሱ:: የዚህን ጊዜ ሁሉም ሕፃናቶች ፀሎቶቹን በቃላቸው መያዛቸውን ማረጋገጥ አለብዎ::

ቀጥለው ሕፃናቱ ባለፉት ሁለት ክፍለ ጊዜዎች ያጠኗቸውን መዝሙሮች እንዲዘምሩ ያድርጉ:: እነዚህን መዝሙሮች በሚገባ ማጥናታቸውን ካረጋገጡ በኋላ የእለቱን መዝሙር ያስጠኗቸው::

_መንገዱ ፍትህ ነው_

ፍትህ
እንደሰት ዘንድ በየእለቱ
ፍትሕ ነው መብራቱ፣

ሰዎች ሲባዝኑ መንገዳቸው ጠፍቶ
ከመልካም ምግባር በጥረት ተሰርቶ
ፍትህ ብርሃን ነው የሚያሳይ አጉልቶ፣
አብዱል-ባሃ የኛ መምህር
ስለሱ ስንሰማ ዘወትር፣
ያለውን ሁሉ ያካፍላል
ባለው የሚረካ በትንሽ ነገር የሚደሰት
የሚያስብ ስለሌሎች ሕይወት፣
ፍትሕ ትርጉም አለው የላቀ
ከመልካምነት የረቀቀ፣
ፍትኸኛ ለመሆን
የምታፈቅረውን፣
በሁሉም ቦታ
አጋራ የመኖርን ደስታ።

ሕፃናቱ በቃላቸው እንዲይዙ የሚፈልገውን ጥቅስ ከማብራራቶ በፊት ከሕፃናቱ መካከል በቀደሙት ክፍለ ጊዜዎች ያጠኗቸውን ሁለት ጥቅሶች የቻሉትን ያህል በቃላቸው እንዲወጧቸው ይጠይቁ። ከዚያም የእለቱን ጥቅስ በሚከተለው መንገድ ያብራሩ።

አምላክ ፍትህን ይወዳል። ሌሎችን በፍትህና በእኩልነት ስንመለከት በእኛ ይደሰታል። የእያንዳንዱን ሰው መብት ማክበር አለብን። ማንንም የሚገባውን መንፈግ የለብንም። ፍትሕዊ ለመሆን እንዲረዳን የሚከተ ለውን የባሃኦላህን ጥቅስ በቃላችን እንያዝ።

ይህን ማብራሪያ ለሕፃናት በሚገባ ቃላት ማስረዳት ቢችሉ መልካም ነው።

**"በፍትሕ መንገድ ተራመድ፤ ይህ በእውነቱ ቀጥተኛው መንገድ ነውና።"[3]**

### ተራመድ

- ከዛፎቹ ላይ ብዙ ቅጠሎች ረግፈው መንገዱን ሸፍነውታል። ፉሚኮ በዛፎቹ መካከል ሄደች። ፉሚኮ በቅጠል በተሸፈነው መንገድ ላይ ተራመደች።
- ፔድሮ ጓደኞቹ ሁሉ በአንድ ላይ እንዲጫወቱ ማድረግ ይወዳል። ፔድሮና ጓደኞቹ አንድነታቸው የጠነከረ ነው። ፔድሮና ጓደኞቹ በአንድነት ይራመዳሉ።

### መንገድ

- ሉዊስ አህያ አለው። ሳር እንድትግጥ ወደሜዳ ከወሰዳት በኋላ እርሱ ወደ ቤቱ ተመለሰ። አህያዋም ወደ ቤት የሚወስዳትን መንገድ ማንም ሳይመራት ትመለሳለች።
- ወደ ትምህርት ቤት የሚያስኬዱ ሁለት መንገዶች አሉ። ሚሊ በአያቷ ቤት በኩል ባለው መንገድ መሄድ ትወዳለች።

### ፍትህ

- ካርሎስ ለተማሪዎች እንዲያከፋፍል ባለቀለም እርሳሶች ተሰጠው። አስር ባለቀለም እርሳሶችና አምስት ተማሪዎች ነበሩ። ካርሎስ ለእያንዳንዱ ተማሪ ሁለት ሁለት እርሳሶችን አደለ። ካርሎስ እርሳሶቹን በፍትህ አከፋፈለ።
- እነአና ቤት ያለው የውኃ ጉድጓድ ሙሉ ነው። አንዳንድ ጊዜ የጎረቤቶቿ የውሃ ጉድጓድ ግን ይደርቃል። አና ጎረቤቶቿ እንዲቸገሩ ስለማትፈልግ ከእርሷ ጉድጓድ መጥተው እንዲቀዱ ትፈቅድላቸዋለች። አና ፍትኸኛ ነች።

ሕፃናቱ ጥቅሱን ካጠኑና ትርጉሙንም ካብራሩላቸው በኋላ ስለ ፍትህ ምንነት ምሳሌ የሚሆን የአብዱል-ባሃን ታሪክ ይተርኩላቸው። ይህን ታሪክ ሲተርኩ የአብዱል-ባሃን የፍትሃዊነት ባህሪ የሚያመለክቱ ተግባሮቹ ላይ አጽንኦት ይስጡ። ከዚያም ሕፃናቱ የአብዱል-ባሃን ምሳሌ እንዴት መከተል እንዲችሉ ይርዷቸው።

### የእለቱ ትረካ

አንድ ቀን አብዱል-ባሃ ከአቆር ወደ ሐይፋ መጓዝ ነበረበትና ብዙ ገንዘብ በማያስከፍል ጋሪ ላይ ተሳፈረ:: የጋሪ ነጂውም ተደነቀ:: አብዱል-ባሃ ገንዘብ ቆጥቦ በዚህ ርካሽ ጋሪ ለመሄድ እንዴት ፈለገ ብሎ ራሱን ሳይጠይቅም አልቀረም:: **"መቼም ክቡርነትዎ የተሻለ ምቾት ባለው ጋሪ መጓዝን ሳይመርጡ አይቀሩም"** ሲል አብዱል--ባሃን ጠየቀ:: "አይ! አልፈልግም!" ሲል አብዱል-ባሃ መልስ ሰጥቶት:: በተጨናነቀው ጋሪ ወደ ሐይፋ መጓዙን ቀጠለ:: ሐይፋ ደርሶ ከጋሪው እንደወረደ የተከፋች ዓሣ አጥማጅ ሴት ወደ እርሱ መጥታ እንዲረዳት ጠየቀችው:: ቀኑን በሙሉ ምንም ዓሣ ልታጠምድ ባለመቻሏ አሁን ወደ ተራቡ ቤተሰቦቿ መመለስ ተገዳለች:: አብዱል-ባሃም በቂ ገንዘብ ከሰጣት በኋላ ወደጋሪ ነጂው ዞወር ብሎ **"ብዙ ሰዎች እየተራቡ እኔ ስምን በምቾት መጓዝ ይኖርብኛል?"** አለው::

### ከዚህ ታሪክ ቀጥሎ "መተሳሰብ" የተሰኘ ጨዋታ ይቀጥላል::

የመኪና ጎማ ወይም ርዝመት የሌለው ሌላ እቃ በመሬት ላይ ይቀመጥ ከዚያም በጎማው ላይ ብዙ ሕፃናት በአንድ ጊዜ ለመቀመጥ ይሞክሩ::

**የዕለቱን ክፍለ--ጊዜ ለማጠናቀቅ ለእያንዳንዱ ልጅ ስዕል ቁጥር 3 ይሰጠውና ቀለም ይቀባ**

# ትምህርት 4

የዕለቱን ትምህርት በሚከተለው ጸሎት ይጀምሩ::

> **"አምላክ ሆይ! መንፈሴን አድስልኜ አስደስትልኝም:: ልቤን አንፃልኝ:: አእምሮዬን አብራልኝ:: ጉዳዮቼን ሁሉ በአንተ ላይ ጥያለሁ:: አንተ መሪዬና መሸሻዬ ነህ:: ከእንግዲህ ወዲያ የተከፋሁና ኃዘንተኛ አልሆንም፣ ደስተኛና በሃሴት የተመላሁ እሆናለሁ:: አምላክ ሆይ ከእንግዲህ ወዲያ በስጋት ውስጥ አልዋኝም፣ ችግርም እንዲያስጨንቀኝ መንገድ አልሰጥም:: ደስ በማያሰኝ የሕይወት ነገር ውስጥ አልኖርም:: አምላክ ሆይ! አንተ ከራሴ ይልቅ ለእኔ ትራታልኛለህ:: ጌታ ሆይ፤ ራሴን ለአንተ አደራ ሰጥቻለሁ::"[10]**

ከልጆችም መካከል ከዚህ በፊት የሚያውቁትን ጸሎት እንዲፀልዩ ካደረጉ በኋላ ባለፉት ሦስት ክፍለ ጊዜዎች በቃላቸው የያዟቸውን ፀሎቶች ይከልሱ:: አዲስ ጸሎት ከማስተማርዎ በፊት በመጀ መሪያዎቹ ክፍለ-ጊዜዎች ያስጠኗቸውን ፀሎቶች በሚገባ መቻላቸውን ያረጋግጡ::

በዚህ ክፍለ-ጊዜ በቃላቸው እንዲይዙ የፀሎቱን ዋና ዋና ጽንሰ-ሃሳብ ሲያብራሩላቸው መሪ ቃላቶችን በግልጽ ማብራራትዎን አይዘንጉ:: ከባድ ቃላት ሲያጋጥምዎ ትርጉማቸውን ሊያብራሩ የሚችሉ ተጨባጭ ምሳሌዎችን መስጠት ይገባል:: ሕፃናቱ ይህንን ፀሎት በቃል ለመያዝ ሰባት ክፍለ ጊዜዎች ሊፈጅባቸው ይችላል:: ስለዚህ ፀሎቱን ለሰባት ከፍሎ በቀን አንዱን ክፍል ማስጠናትና ቀሪዎቹን ሁለት ክፍለ ጊዜዎች ለክለሳ መመደብ ያስፈልጋል::

> **"አቤቱ አንተ ቸር ጌታ ሆይ! እኔ ትንሽ ልጅ ነኝ፤ በመንግሥትህ ውስጥ ተቀብለኝ ከፍ አድርገኝ:: ምድራዊ ነኝ? የመንግስተ ሰማይ ነዋሪ አድርገኝ? እኔ የዝቅተኛው ዓለም ነዋሪ ነኝ? የላይኛው ዓለም ነዋሪ እንድሆን አድርገኝ? የተከፋሁ ነኝ? ደስተኛ እንድሆን አድርገኝ? ቁሳዊ ነኝ? መንፈሳዊ አድርገኝ? ወሰን የሌላቸውን ጸጋዎችህንም እንድከስት ፈቃድህ ይሁን:: አንተ ኃይል የተመላህ? ሁሉን አፍቃሪው ነህና::"[11]**

ከዚህ በመቀጠል ልጆቹ አዲስ መዝሙር ሊማሩና ባለፉት ክፍለ ጊዜዎች የተማሯቸውን መዝሙሮች ሊከልሱ ይችላሉ::

**<u>ፍቅር ፤ ፍቅር ፤ ፍቅር</u>**

ፍቅር ፤ ፍቅር ፤ ፍቅር፤ አፍቅር
መሰልህን ሰው አፍቅር፣
ዓለምም ልትፈጠር
ምክንያቱ ነው ፍቅር፣
ስለወደድኩህ ፈጠርኩህ ይላል አምላክ
እንድትወደውና ሰውንም
እንድትወደው::

**ቀጥለውም ልጆቹ በቃላቸው የሚይዙትን አዲስ ጥቅስ በሚከተለው መንገድ ሊያብራሩላቸው ይችላሉ::**

የአምላክን ፍቅር እንደ ፀሐይ ጨረሮች በሰው ዘር ላይ ያንፀባርቃል:: የፀሐይ ጨረር በበረሃውም ሆነ በመስክ ላይ እኩል ይፈነጥቃሉ:: ፍቅራችንም እንደ ፀሐይ ጨረሮች ሊሆን ይገባል:: የሚያስከፋንን ጨምሮ ሁሉንም ሰው ማፍቀር አለብን:: የሰውን ዘር በሙሉ ለማፍቀር እንድንችል እንዲረዱን የሚከተለውን የባሃኦላህ ጥቅስ በቃላችን እንያዝ::

**"ወዳጅ ሆይ! በልብህ አትክልት ሥፍራ ከፍቅር ጽጌረዳ በስተቀር ሌላ አትትከል..::"**[22]

ከዚህ በኋላ አንድ ታሪክ ይተርኩላቸው:: ሕፃናቱን በታሪኩ ለማስደሰት ከፈለጉ በመጀመሪያ ታሪኩን ለብቻዎ ማንበብ፤ ስለዋናው ጭብጥና የህፃናቱን ትኩረት ስለሚስቡት ዝርዝሮች አስቀድመው ማሰላሰል እንደሚገባዎ አይዘንጉ::

## የዕለቱ ትረካ

አብዱል-ባሃ በአቆር ከተማ ታስሮ ሳለ በዚያ ከተማ ውስጥ አብዱል-ባሃን በጣም የሚያስቸግር አንድ ሰው ነበረ:: ይህ ሰው የነብዩ መሐመድ ተከታይ ነኝ ብሎ ያምን ነበር:: አብዱል-ባሃ መጥፎ ሰው ነው፤ ባሃኢዎቹም ላይ ለሚደረግባቸው ጭቆና አምላክ ግድ የለውም ብሎ ያስብ ነበር:: እንዲያውም ባሃኢዎቹን በመጥላት ለአምላኩ ፍቅሩን ሊያሳይ ይሞክር ነበር:: አብዱል-ባሃንም ከልቡ ጠላው:: ጥላቻው በውስጡ እያደገ ሄደ:: አንዳንድ ጊዜ ጥላቻው በግልጽ ይታይበት ነበር::

ሰዎች ለፀሎት ወደመስጊድ ሲሄዱ ይህ ሰው ድምጹን ክፍ አድርጎ አብዱል-ባሃን ይሳደብና ስለእርሱም መጥፎ ነገሮችን ይናገራል:: ከአብዱል-ባሃ ጋር በመንገድ ሲተላለፉ አብዱል-ባሃን ለማየት ባለመፈለግ ፊቱን በልብሱ ይሸፍናል:: ይሁንና ይህ ሰው የሚበላው በቂ ምግብና ከብርድ የሚከላከል የረባ ልብስ የሌለው በጣም ደሃ ሰው ነበር:: አብዱል-ባሃ ይህንን ሰው ምን ያደረገው ይመስላችኋል? አብዱል-ባሃ ለሰውየው ደግነትን በተግባር አሳየው፤ ምግብና ልብስ ላከለት፤ አስፈላጊውን እንክብካቤ አደረገለት:: ለምሳሌ አንድ ጊዜ ይህ ሰው ታሞ ነበር:፤ አብዱል ባሃ ሃኪም ላከለት፤ መድሃኒትና ምግብ ገዛለት፤ ጥቂት ገንዘብም ጨምሮ ሰጠው:: ሰውየው ስጦታውን ከአብዱል-ባሃ ተቀበለው:: ነገር ግን አላመሰገነውም:: እንዲያውም ክፉ ሰው የደሙን ግፊት እንዲለካ አንዱን እጁን ለሐኪም ሰጥቶ በሌላው እጅ የአብዱል-ባሃን ፊት ላለማየት ፊቱን ሸፈነ:: በዚህ ዓይነት ብዙ ዓመታት አለፉ:: በመጨረሻም አንድ ቀን የሰውየው ልብ ሩህሩህ ሆነ:: አብዱል-ባሃ ቤት ድረስ ሄዶ እግሩ ስር በጣም ባዘነ ልብ ወደቀ:: መጥልቅ እያነባ "**ክቡር ሆይ ይቅር ይበሉኝ! ለሃያ አራት አመታት በእርስዎ ላይ ክፉ ነገር ስፈጽም ኖሬአለሁ:: ለሃያ አራት አመታትም እርስዎ ርህራሄ ብቻ ሲያሳዩኝ ቆይተዋል:: እስከዛሬ የፈጸምኩት ሁሉ ስህተት እንደነበረ አሁን ተረድቻለሁ:: እባክዎ ይቅር ይበሉኝ::**" እያለ ጮኸ:: የአብዱል-ባሃ ታላቅ ፍቅር ጥላቻን አሸነፈ:: ሰውየውንም ከክፉነት ባሕሪ አወጣው::

ቀጥሎ የሚከተለውም "ድልድይ" የተሰኘ ጨዋታን መጫወት ነው::

እንደድልድይ ሊያገለግል የሚችል ረዘም ያለ ትይዩ መሰመሮች ይሰመሩ:: ሕጻናቱ ለሁለት ይከፋፈሉና ከተለያየ አቅጣጫ ድልድዩን ያቋርጡ:: ሲያቋርጡ ግን ማንም ሰው ከድልድዩ እንዳይወድቅ ጥንቃቄ ያድ ርጉ:: ቦታ በመለዋወጥ አንዱ ሌላውን ለማሳለፍ መረዳዳት አለባቸው::

**ይህንን ክፍለ--ጊዜ ለማጠቃለል ለሁሉም ልጆች ስዕል ቁጥር 4 ይታደልና ቀለም ይቀቡ::**

# ትምህርት 5

እስካሁን የየእለቱን ትምህርት ለመጀመር የተጠቀሙባቸውን አራት ፀሎቶች እርሶ በቃልዎ ሳይዙ አልቀሩም:: በቃልዎ ከያዟቸው ከእነዚህ አራት ፀሎቶች መካከል አንዱን በመጠቀም ቀጣዮቹን የትም ህርት ክፍለ-ጊዜዎች ይጀምሩ:: ሕፃናቶቹም ቢያንስ አንድ ፀሎት በቃላቸው ሳይዙ ስለማይቀሩ ከመካከላቸው አንዳንዶቹ ከእርስዎ ቀጥለው ፀሎቱን ይድገሙ:: እያንዳንዱ ልጅ ቢያንስ በሶስት ወይም በአራትክፍለ ጊዜዎች ልዩነት ፀሎት ማድረግ አለበት:: በተጨማሪም በእያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ በትምህርት ቁጥር 4 በቃላቸው መያዝ የጀመሩትን ጸሎት ማጥናት ይቀጥሉ:: ይህንን ፀሎት ማስጠናቱ እስከ ትምህርት ቁጥር 9 እንደሚቀጥል እንዳይረሱ:: ከዚያም ፀሎቱን ሁሉም ህፃናት በቃላቸው ይይዙታል ተብሎ ይጠበቃል::

## ቀሪዎቹ የእለቱ እንቅስቃሴዎች ከዚህ የሚከተሉት ናቸው::

*ሀ. መዝሙሮች* (በቀደሙት ክፍለ ጊዜዎች ከተማሯቸው መዝሙሮች መካከል ጥቂቶቹን ይጨምሩ)

***<u>ተመልከቱኝ</u>***

ተመልከቱኝ
ተመልከቱኝ
እንደኔ ሁኑ
አብዱል-ባሃ አብዱል-ባሃ
አስተምሩ-አስተምሩ-አስተምሩ
ተከተሉኝ እንደኔ ኑሩ
አብዱል-ባሃ - አብዱል-ባሃ
ጌታን አገልግሉ
እኔን ተከተሉ
አብዱል-ባሃ -አብዱል-ባሃ
የሰው ዘርን አፍቅሩ
ወደ እኔ ኑ እንደኔ ሁኑ
አብዱል-ባሃ - አብዱል-ባሃ

## ለ ቅዱሳን ጥቅሶችን በቃል መያዝ

አምላክ ያፈቅረናል:: ሁልጊዜም ወደ እርሱ እንድንቀርብ ይፈልጋል:: ወደ አምላክ ለመቅረብ ዋነኛው መንገድ እርሱን ማገልገል ነው:: የሰውን ዘር በምናገለግልበት ጊዜ የአምላክ አገልጋዮች ሆንን ማለት ነው:: የሰውን ዘር በተለያየ መንገድ ልናገለግል እንችላለን፤ ለምሳሌ የታመሙትን መጠየቅ፤ የተቸገሩን መርዳትና የምናውቀውን ለሌሎች ማስተማር:: ሐብታም ወይም ደሃ፤ ጓደኞቻችንንም ሆነ ሌሎችንም ሰዎች ያለ ልዩነት ሁሉንም ማገልገል አለብን:: የሰው ዘር አገልጋዮች ለመሆን እንዲረዳን የሚከተለውን የባሃኦላህ ጥቅስ በቃላችን እንያዝ::

"ያ ዛሬ ስመሳው የሰው ዘር አገልግሎት ራሱን የሚሰጥ ሰዉ በእውነቱ ሰው ነው::"

## ራስን መስጠት

- ደርቪ በስዕል ትምህርት ክፍለ ጊዜ በፀጥታ ታዳምጣለች፡፡ ከትምህርቱ በፊት ብዙ ጊዜዎን ሰጥታ ትዘጋጃለች፡፡ ደስታ ለስዕል ትምህርት እራሷን ለስዕል ሰጥታለች፡፡
- የሃንግ ዌይ አባት አትክልተኛ ናቸው፡፡ሃንግ ዌይም ሁልጊዜ በጧት ተነስቶ በአትክልቶቹ ውስጥ ያደጉትን አረሞች በመንቀልና አትክልቶቹን ውሃ በማጠጣት አባቱን ይረዳል፡፡ ሃንግ ዌይ አባቱን ለመርዳት ራሱን ሰጥቷል፡፡

## አገልግለት

- ሙምቢ፤ አፒዮና ቶቐ የአያቶቻቸውን ቤት ሲያፀዱ ቆዩ፡፡ ይህንን አገልግሎት በመስጠታቸው በጣም ተደስተው ነበር፡፡
- ሕፃናት በማስተማር አገልግሎት መሰጠት ስለምትፈልግ ሳሽኮ የምታስተምራቸው ህፃናት ያሉበት ቦታ ለመድረስ ብዙ ኪሎ ሜትር በእግሯ ትጓዛለች፡፡

## የሰው ዘር

- ትምህርት ቤት በተለያዩ ሐገሮች የሚኖሩ የነጭ፤ የቀይና የጥቁር ህዝቦችን ምስል ተለጥፎ አየሁ፡፡ እነዚህ ሁሉ ሰዎች የሰው ዘር ክፍሎች ናቸው፡፡
- አስተማሪው ኬንጂን በሌሎች አካባቢዎች የሚኖሩ ሰዎችን እንደራሱ መንደር ሰዎች ይወድ እንደሆነ ጠየቁት፡፡ እርሱም ሁሉም የሰው ዘር ክፍሎች ስለሆኑ ሁሉንም እወዳለሁ ሲል መለሰ፡፡

## ሐ. የዕለቱ ትረካ

ሉዋ ጌትሲንገር ከቀድሞ የአሜሪካ ባሃኢዎች መካከል አንዷ ነች፡፡ አብዱል-ባሃን ለመጎብኘት በግምብ የታጠረች ከተማ ወደሆነችው አቆር ሄዳ የገጠማትን እንዲህ ስትል ተናግራለች፡፡

አንድ ቀን አብዱል-ባሃ በጣም ስራ ስለበዛበት አንድ ድሃና የታመመ ጓደኛውን ለመጠየቅ ጊዜ እንዳጣ ይነግራታል፡፡ እንደ እርሱ ሆና ብትጠይቅለትም እንደሚደሰት ይገልጽላታል፡፡ ጥሩ ምግብ ለበሽተኛው እንድትወስድና እርሱ ያደርግ የነበረውንም በማድረግ እንድትንከባከበው ያዛታል፡፡

ሉዋም የሰውየውን አድራሻ ተቀብላ ወዲያውኑ አብዱል-ባሃ ያዘዘውን ለመፈጸም ትሄዳለች፡፡ አብዱል-ባሃ የእራሱ የሆነን ስራ እንድታከናውንለት አደራ ስለሰጣት ኩራት ተሰማት፡፡ ነገር ግን ብዙም ሳትቆይ ደንግጣ ተመለሰች፡፡ አብዱል-በሃን "ጌታዬ" ብላ በመጥራት እንዲህ አለች፡-«በጣም አስቸጋሪ ወደሆነ ቦታ ነው የላክኸኝ፡፡ በክፍሉ ውስጥ በነበረው መጥፎ ሽታና ቆሻሻ በአሳዛኙ የሰውየውና የቤቱ ሁኔታ የተነሳ እራሴን ስቼ ልወድቅ ነበር፡፡» በማለት ስለተሰማት ሁኔታ ለአብዱል ባሃ ተናገረች፡፡

አብዱል ባሃ አዝኖ በትኩረት ተመለከታት፡፡ እምላክን የምታፈቅር ከሆነ የሰው ዘርን ሁሉ ማገልገል እንዳለባት ነገራት፡፡ ምክንያቱም በሁሉም ሰው ውስጥ የአምላክን አምሳልና ምሳሌ ማየት መቻል አለባትና፡፡ ከዚያም በድጋሚ ወደሰውየው ቤት እንድትሄድ ነገራት፡፡ ቤቱ ቆሻሻ ከሆነ ልታፀዳው ይገባል፡፡ ሰውየው ቆሽሾ ከሆነ ልታጥበው ይገባል፡፡ የተራበ ከሆነ ልትመግበው ይገባል፡፡ ይህንን ሁሉ ካላደረገች እንዳትመለስ ነገራት፡፡ አብዱል-ባሃ ይህንን ሁሉ ለሰውየው በተደጋጋሚ አድርጎለታል፡፡ እርሷም ለአንድ ቀን ቢሆንም እንኳ ሰውየውን መንከባከብ እንዳለባት ነገራት፡፡ ሉዋ መሰል የሰው ዘር እንድታገለግል አብዱል-ባሃ የመከራት በዚህ መንገድ ነበር፡፡

### መ. ጨዋታ፡- "ሕሙማንን መርዳት"

አንድ ሕፃን የታመመ ይምሰል፡፡ ሌሎች ሁለት ልጆች ደግሞ ወንበር ለመስራት እጅ ለእጅ ይያያዙ (ግራ እጅ በግራ እጅ፤ ቀኝ እጅ በቀኝ እጅ)፡፡ የታመመው ህፃን በወንበሩ ላይ ይቀመጥና ሌሎቹ አጅበውት ወደጤና ጣቢያ ይውሰዱት፡፡ (እንደ ጤና ጣቢያ ሊያገለግል የሚችል ቦታ አስተማሪው ይምረጡ፡፡)

**ጨዋታውን በተለየ መንገድ ለማጫወት:-**

ጥቂት ልጆች ግራና ቀኝ በመቆም እጅ ለእጅ ይያያዙና ቃሬዛ ይስሩ:: የታመመው ልጅ ቃሬዛው ላይ ይተኛ:: ከዚያም እንዳይወድቅ በመጠንቀቅ ወደ ጤና ጣቢያ ይወስዱት::

**ሰ. ስዕል ቁጥር 5ትን ቀለም መቀባት::**

# ትምህርት 6

እንደቀደሙት ክፍለ ጊዜዎች የዛሬውንም በቃልዎ ካጠኗቸው ፀሎቶች መካከል በአንዱ ይጀምሩና ከህፃናቱ መካከል ጥቂቶቹ እንዲጸልዩ ይጠይቁ:: ፀሎት ከተደረገ በኋላ በትምህርት 4 ውስጥ የተሰጠውን ፀሎት በቃል ማስጠናትን ይቀጥሉ:: የእለቱ ትምህርት ቀጣይ ተግባሮች የሚከተሉት ናቸው::

**ሀ. መዝሙር** (በቀድሞው ክፍለ ጊዜ ያስጠኗቸውን መዝሙሮች ይጨምሩ)

<u>እውነትን ተናገሩ</u>

እውነትን ተናገሩ
ብትናገር እውነት
ይጣልብሃል እምነት
ሁልጊዜም እውነት መናገር
ግዴታ ነው የማይሻር
እውነት መናገር አያሳፍርም
ይደሰትብሃል እግዚአብሔርም
ውሸት መናገር ያስወቅሳል
ጓደኛን ያሳጣል

## ለ. የቃል ጥናት

በጣም አስፈላጊ ከሆኑት መንፈሳዊ ባህሪያት መካከል እውነተኛነት አንዱ ነው:: ባሃኢዎች ትንሽም ብትሆን እንኳን መዋሸት የለባቸውም:: ሰዎች የሚዋሹት ለምንድነው? ሰዎች አንዳንድ ጊዜ የሚዋሹት እውነትን መናገር ስለሚፈሩ ነው:: ይሁንና አምላክ የምናደርጋቸውን ነገሮች ሁሉ ስለሚያውቅ ምንም ነገር ከእርሱ ልንደብቅ አንችልም:: እውነተኞች ካልሆንን ሌሎች መልካም ተግባራትን ለማዳበር በጣም እንቸገራለን:: ወደ አምላክም ለመቅረብ አንችልም:: እስቲ የሚከተለውን የባሃኡላህን ጥቅስ በቃላችን እንያዝ::

**"እውነተኛነት የሰው የመልካም ምግባራት ሁሉ መሠረት ነው::"**

## እውነተኛነት

- ሳንጃይ ብርጭቆ ከእኛ ላይ ወድቆ ተሰበረባት:: እናቷ ምን እንደተፈጠረ ሲጠይቋት ከመዋሸት ይልቅ እውነቱን ተናገረች:: ሰናይት የእውነተኛነትን ባህሪ አሳየች::
- የጊታ ጓደኛ ከጊታ ጋር ለመጫወት ወደእርሱ ቤት ሄደ:: ይሁንና ጊታ የቤት ሥራ ስለነበረው ለጨዋታ ከቤቱ መውጣት አልቻለም:: ጊታ ቤት የለም ብዬ ልንገርልህ? ሲል የ ጊታን ወንድም ጊታን ጠየቀው:: ጊታ ግን እኔ እራሴ እውነቱን እነግረዋለው ብሎ ሊጫወት እንደማይችል ለጓደኛው ነገረው::

*መሠረት*

- *የአሎክ አባት ቤት እየሰሩ ነው ግድግዳውን ከመገንባታቸው በፊት ግድግዳው የሚቆምበት መሠረት በድንጋይ ገነቡ። የድንጋዩ ግንብ የቤቱ መሠረት ሆነ።*
- *መጻፍና ማንበብ ከመማርህ በፊት ፊደል መቁጠር መማር መጻፍና ማንበብን ለመማር መሰረት ነው።*

*መልካም ምግባራት*

- *አውሮራ ደግ፣ ሩህሩህና ደስተኛ ነው። አውሮራ ብዙ መልካም ምግባራት አሉት።*
- *ወይዘሮ ፓቴል ህፃናቱን ስለፍትህ፣ ለጋስነት፣ ትህትና እና ታማኝነት ያስተምራሉ። ወይዘሮ ፓቴል ህፃናቱን ብዙ መልካም ምግባራትን ያስተምራሉ፡፤*
- *ተጨማሪ የመልካም ምግባራትን አስፈላጊነት የሚገልጹ ምሳሌዎችን መጥቀስ ይችላሉ።*

*ሐ.* **የዕለቱ ትረካ**

*በድሮ ጊዜ በሩቅ አገር የሚኖር አንድ እረኛ ልጅ ነበር። የዚህ ልጅ የእለት ተግባር በመንደሩ የሚገኙ በጎችን ሰብስቦ ሲያግድ (ሲጠብቅ) መዋል ነበር።*

*ከእለታት አንድ ቀን በስራው ላይ እያለ ስልችት አለውና የመንደሩ ሰዎች ላይ ሊቀልድባቸው ፈለገ፡፤*

**"ተኩላ! ተኩላ! እረ! በጎቹን በላ!"** *እያለ በድንገት መጮህ ጀመረ። የዚህን ጊዜ የመንደሩ ሰዎች ዱላ ይዘው እየሮጡ ደረሱ፡፤ በሰዎቹ ፊት ላይም ከፍተኛ ድንጋጤ ይነበብ ነበር። እቦታው ሲደርሱ ግን ምንም ቀበሮ አልነበረም። እረኛውም ባደረሰባቸው ድንጋጤ ተደስቶ ይስቅ ነበር። ይህ ልጅ መልካም ተግባር አልፈጸመም እያሉ መንደርተኞቹ ወደ ሥራቸው ተመለሱ።*

*በሚቀጥለው ቀንም ልጁ ተመሳሳይ ተግባር ፈጸመ።* **"ተኩላ! ተኩላ! እርዱኝ!"** *እያለ ጮኸ። አሁንም ከመንደሩ ሰዎች መካከል ጥቂቶቹ ለእርዳታ እየሮጡ ደረሱ። ይሁንና አሁንም ያስሮጣቸው በውሸት በመሆኑ ቁጭ ብሎ ሲስቅባቸው አገኙት። በሶስተኛው ቀን* **"ቀበሮ! ቀበሮ! በጎቹን ጨረሳቸው እባካችሁ ድረሱልኝ"** *እያለ ሲጮህ በሰሙ ጊዜ ለሶስተኛ ጊዜ እየዋሸ ነው ብለው ስላሰቡ ለእርዳታ አልወጡም። ነገር ግን በዚያን ቀን እውነትም "ተኩላ" መጥቶ ነበርና በጎቹን በላቸው። እረኛውም ልጅ በጣም አዘነ። ነገር ግን አንድ ትልቅ ትምህርት ተማረ። ውሸት የምንናገር ከሆነ ወላጆቻችን፣ ወንድሞቻችን፣ እህቶቻችንና ጓደኞቻችንም ሁሉ የምንናገረው ነገር እውነት ቢሆንም እንኳን እንዳያምኑን ተረዳ።*

*መ.* ***ጨዋታ፡-*** የስልክ ጥሪ

*ብዙ ልጆች ወደአንድ አቅጣጫ ፊታቸውን አዙረው ይሰለፉ። ካስፈለገ ከአንድ በላይ ሰልፍ ሊደረግ ይቻላል። በመጀመሪያው ልጅ ጀርባ ላይ አስተማሪው ምንም መጻፊያ ሳይጠቀሙ በጣታቸው በቀላሉ ሊታወቅ የሚችል ነገር ይሳሉ። ጀርባው ላይ የተሳለበትን ለመገመት እንዲችል ጀርባውን ጫን በማለት መዳሰስ አለበት። ይህም ልጅ አስተማሪው በጀርባው ላይ የሳሉት ስዕል ከእርሱ ቀጥሎ ባለው ልጅ ጀርባ ላይ ይሳል። በዚህ መሰረት ይቀጥልና የመጨረሻው ልጅ ከእርሱ በስተኋላ ያለው ልጅ በጀርባው ላይ የኋላውን ስዕል ከፊቱ በተሰቀለው ነጭ ወረቀት ወይም ጥቁር ሰሌዳ ላይ ይሳል። ከዚያም አስተማሪው በመጀመሪያው ልጅ ላይ በዳሰሳ የሳሉትን የመጨረሻውን ልጅ ከሳለው አጠገብ ይሳሉና ለሕፃናቱ ያሳዩ። ስዕሎቹ በጣም ቀላልና ሁሉም ህፃናት ሊስሏቸው የሚችሏቸው ዓይነት መሆን አለባቸው።*

*ሠ. ስዕል ቁጥር 6ን ቀለም መቀባት*

# ትምህርት 7

እርስዎና ልጆቹ ፀሎት ካደረጋችሁና ባለፉት ክፍለ--ጊዜዎች በቃል መያዝ ከጀመራችሁት ፀሎት ካስተማሯቸው በኋላ ወደቀጣዮቹ የእለቱ ክፍለ ጊዜ እንቅስቃሴዎች መሸጋገር ትችላላችሁ።

*ሀ. መዝሙሮች* (ቀድሞ ያጠኗቸውን መዝሙሮችም ይጨምሩ)

<u>እኛ የባሃ ሕዝቦች ነን</u>

እኛ የባሃ ሕዝቦች ነን
እኛ የባሃ ሕዝቦች ነን
እኛ የባሃ ሕዝብ(2)
ያ ባሃኦላህ አብሃ(2)
እኛ የባሃ ሕዝቦች(2)
እኛ የባሃ ሕዝቦች ነን
በፅናት የእግዚአብሔርን መንገድ
እንጓዛለን(2)

## ለ. ቅዱሳን ጥቅሶችን በቃል መያዝ

አምላክን ከልቡ የሚያፈቅር ሰው ሊኖሩት ከሚገባ እጅግ አስፈላጊ ባህሪያት መካከል አንዱ ጽናት ነው። እኛ ባሃኢዎች ባሃኦላህን የተቀበልንና፣ እርሱም የዚህ ዘመን የአምላክ ክስተት(መልእክተኛ) እንደሆነ እርግጠኞች የሆንን ነን። ስለዚህ በማንኛውም አስቸጋሪ ሁኔታ በእምነታችን ጸንተን ለመኖር ሁልጊዜ እርሱን ልናፈቅር፣ ሕግጋቱንና ምክሮቹን ልንታዘዝ ይገባል። ይህንን ለማስታወስ እንድንችል የሚከተለውን የባሃኦላህ ጥቅስ በቃላችን እንያዝ።

"በጌታህ እምነት ጽኑ ሆነህ ከቆየህ፣ ደረጃህ እጅግ በጣም የላቀ ይሆናል።"[15]

### ጽኑ መሆን

- ከዋክብት በሰማይ ላይ የተቀመጡ ነጫጭ ነጥቦች ናቸው ሲል አንድ ሰው ለሮዝሜሪ ነገራት። ይሁንና እያንዳንዱ ኮከብ በርቀት የሚገኝ ፀሐይ እንደሆነ በትምህርት ቤት ተምራለች። ሮዝሜሪ በትምህርት ቤት የተማረችውን አስተሳሰብ አለወጠችም። ሮዝሜሪ በተማረችው ትምህርት ጸናች።
- በየቀኑ መጸለይ አስፈላጊ ነው አይደለም ብሎ አንድ ሰው ለሞና ነገራት። ይሁንና በየቀኑ መጸለይ የአምላክ ህግ መሆኑን ስለምታውቅ ሞና መፀለይ አላቆመችም። ሞናም የፀሎትን ህግ በማክበር ጽኑ ሆና ቆየች።

### የላቀ ደረጃ

- ማርታ በትምህርቷ ጎበዝ ስለነበረች በአስተማሪዋ የተሰጣት ነጥብ የላቀ ደረጃ ላይ ስላደረሳት ቤተሰቦቿ ተደሰቱ።
- ኩማር በባሕሪው የላቀ ደረጃ ላይ የደረሰው ቤተሰቦቹን ስለሚታዘዝ ነው።

## ሐ. የዕለቱ ትረካ

በባብና በባሃኦላህ ጊዜ ሕይወታቸውን በአምላክ መንገድ ስለሰውት የባሃኢ እምነት ጀግኖች ወደፊት ብዙ ትማራላችሁ። አሁን የምነግራችሁ በአብዱል-ባሃ ጊዜ ይኖር ስለነበረ ድንቅ ጀግና ሰው ነው። ስሙ ሩህላህ ቫርቃ ይባላል። በሚወደው በባሃኦላህ መንገድ ሕይወቱን ሲሰዋ ገና የ13 ዓመት ልጅ ነበር። ሩህላህ የ12 ዓመት ልጅ እያለ አብዱል-ባሃን ለማየት ከአባቱ ጋር በመሆን ወደ

አቆር ተጓዘ:: ከዚያ በፊት ስለአብዱል-ባሃ ታላቅ ፍቅርና ደግነት በብዛት ሰምቶ ስለነበር አቆር እስከሚደርስ ድረስ በመጓጓት እንቅልፍ አልወስድህ አለው:: በመጨረሻም ከአብዱል-ባሃ ጋር ሲገናኝ ልቡ በከፍተኛ ፍንደቃና ደስታ ተሞላ::

አብዱል-ባሃ፣ ሩህላህን በጣም ወደደው:: ሩህአላህ በሚያምር ድምጽ በቃሉ የሚያውቀውን ፀሎት ሲደግም መስማቱ በተለይ ያስደስተው ነበር:: ሩህላህ ለተወሰነ ጊዜ ከአብዱል-በሃ ጋር በመኖሩ መንግስተ ሰማይ የመግባትን ያህል ደስታን ተቀዳጀ:: ለእምነቱ ያለው ፍቅርና ጽናትም በእያንዳንዱ ቀን እያደገ፤ እያደገ ሄደ:: በመጨረሻም ከአብዱል-ባሃ ጋር የሚቆይበትን ጊዜ አብቅቶ አቆርን ለቆ ከአባቱ ጋር ወደ ፋርስ ተመለሰ:: አገራቸው ከተመለሱም በኋላ የባሃኦላህን ድንቅ መልእክት ለማስተማርና ለማሰራጨት ሕይወታቸውን ለአገልግሎት ሰጡ:: ሩህላህ ሲያስተምር ቃላቶቹ በከፍተኛ ሁኔታ አድማጩን ይስቡ ነበር፡፡ አባቱ በጣም ይወዱት ነበር፤ ሁሉም ሰው በፀባዩና በመንፈሳዊነቱ ያደንቀው ነበር:: ሩህላህ እውነተኛ፤ ታማኝ፤ ሩህሩህና ሰዎችን አክባሪ ነበር:: ፀሎቶችን በጥዑም ድምጹ ያዜማቸው ነበር:: አብዛኞቹንም በቃሉ ያውቃቸው ነበር:: በየቀኑ ጧት ተነስቶ መጸለይን ያዘወትራል::

አንድ ቀን የእምነቱ ጠላቶች ሩህላህንና አባላቱን ያዟቸው:: ቴህራን ውስጥ በሚገኝ አንድ እስር ቤት ውስጥም አስገቧቸው:: የእስር ቤቱ ኑሮ በጣም አስቸጋሪ ነበር:: የታሰሩበትን ከባድ የብረት ሰንሰለት ተሸክመው እንቅልፍ ሊወስዳቸው አልቻለም:: ይሁንና በዚህ ሁሉ ስቃይ መካከል ሩህላህ በጣም ደስተኛ ነበር ፀሎት ይፀልይ፣ ይዘምራል፣ ለባሃኡላህ ያለውን ፍቅር የሚገልፁ በጣም ውብ ግጥሞችንም ይገጥም ነበር::

ለእነዚህ ሁለት ጀግኖች የእስር ቤት ህይወት በየቀኑ እየከበደ መጣ:: በመጨረሻ ግን ይናፍቁት የነበረው ጊዜ ደረሰ:: አንድ ቀን ጧት አንድ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣን ወደ እስር ቤቱ ይመጣል:: ሰክሮ ስለነበር ነገር መፈለግ ጀመረ:: ሩህላህና አባቱ ያልፈፀሙትን አስከፊ ወንጀል ፈጽመዋል ሲል ዘለፋቸው:: እነርሱ ግን ከወንጀሉ ንጹህ እንደሆኑና በማንም ላይ ተንኮል እንዳልፈጸሙ ረጋ ብለው አስረዱ:: ባለስልጣኑ ይበልጥ በመናደድ የሩህላህ አባት ላይ በመጮህ የሚከተለውን አሰከፊ ጭካኔ ፈጸመ:- **"በመጀመሪያ ማንነ ልግደል አንተን ወይንስ ልጅህን ብሎ አባትየውን በማስፈራራት ጠየቀው:: የሩህላህ አባትም ያለምንም ፍራቻና መደናገጥ እኔን አስቀደምክ ወይንም ልጄን በጽናታችን ላይ ምንም የምታመጣው ለወጥ አይኖርም አለ:: ይህንን እንደሰማ ባለስልጣኑ ወደ ሩህላህን አባት ተጠግቶ በአሰቃቂ መንገድ ገደላቸው::"** "አባዬ! አባዬ! ከአንተ ጋር ውሰደኝ" ሲል ሩህላህ ደጋግሞ ጮኸ:: የአባቱን አርኣያነት ለመከተልና የእራሱን ሕይወት ለመሰዋት ከልቡ ተመኘ::

ባለስልጣኑ ለሩህአላህ ደግና አዛኝ ለመምሰል እንዲህ ሲል አናገረው **"አንተ ገና ልጅ ነህ፤ እኔ ደግሞ በጣም እወድሃለሁ ስታድግም ከፍተኛ ስልጣን እሰጥሃለሁ:: ሃብትም ሆነ ሴላ የፈለከውን ነገር ሁሉ እሰጥሃለሁ አንተ እኔ ባሃኢ አይደለሁም ብቻ በል::"** አለው **"እኔ ስልጣንም ሆነ ገንዘብም አልፈልግም::** እንደ አባቴ በእምነቴ ጸንቼ መስእዋት መሆን ነው የምፈልገው::» ሲል ሩህላህ መለሰለት::

ይህ ልጅ ጽኑ እንደሆነና ሊለወጥ እንደማይችል በተረዳ ጊዜ ሩህላህ እንዲሰቀል ትእዛዝ ሰጠ:: ከዚያም የሁለቱ ጀግኖች አካልም ከእስር ቤቱ አጠገብ በሚገኝ ዛሬ ቫርቂኒያ በምትባል ቦታ ውስጥ ባለ አንድ የውሃ ጉድጓድ ውስጥ ተጣለ::

ሩህላህ ከባሃኢ ጀግኖች መካከል አንዱ ሆነ:: በግጥሞቹ ይገልጽ የነበረውን ሕይወቱን በባሃኡላህ መንገድ መስዋዕት የማድረግ የልቡን ፍላጎት አሟላ::

መ. ጨዋታ:- ተኩላዎቹና ፍየሎቹ

አንድ የፍየል መንጋ ነበር:: እነዚህ ፍየሎች ለምለም ሳር ወደሚገኝበት ሜዳ ለማለፍ አንድ አሮጌ ድልድይ መሻገር ነበረባቸው:: ከድልድዩ በታች ትንንሽ ፍየሎችን መብላት የሚወዱ ተኩላዎች አሉ:: ይሁንና ተኩላዎቹ በጣም ሰነፍና እንቅፋሞች ነበሩ:: ከእንቅልፋቸው የሚነቁት በድልድዩ ላይ የሚሄድ የፍየል ኮቴ በሰሙ ጊዜ ብቻ ነው:: ፍየሎቹ ደግሞ በጣም ብልጦች ስለነበሩ ድምጽ ሳያሰሙ በደልድዩ ላይ መራመድ ተለማምደዋል:: ተኩላዎቹን ላለመቀስቀስ

*በመጀመሪያ ጠጋ ብለው የተኩላዎቹን ማንኮራፋት ያዳምጣሉ:: ከዚያም ቀስ ብለው ይራመዳሉ:: በማንኛውም ጊዜ ተኩላዎቹ ማንኮራፋታቸውን ሲያቆሙ ፀጥ ብለው ይቆማሉ ምክንያቱም ተኩላዎቹ ከእንቅልፋቸው ነቅተዋል ማለት ነውና:: ፍየሎቹ ድምጽ ሳያሰሙ ከቆሙ ተኩላዎቹ ተመልሰው ይተኛሉ::*

*ከፍና ዝቅ ያሉ ድልድዮችን እንጨቶችንና አግዳሚ ወንበሮችን በመጠቀም አስተማሪው ያዘጋጁ:: ሕፃናቱ ድልድዩን ያቋርጡ:: አስተማሪው እንደተኩላዎቹ በመሆን እያጨበጨበ ወይም እየቆረቆረ ማንኮራፋቱን ይግለጽ:: ድምጽ ሲሰማ ማንኮራፋቱን ወይንም ማጨብጨቡን ያቁም:: በዚህ ጊዜ ሕፃናቱ አንድ እግራቸውን አየር ላይ ሆኖም ቢሆን እንኳን እንደዚያው ይቁሙ:: ድምጽ ካሰሙ ግን ተኩላዎቹ ይንቁና ፍየሎቹን ይያዙ::*

*ሠ. ስዕል ቁጥር ሰባትን ቀለም መቀባት::*

# *ትምህርት 8*

*እርስዎና ጥቂት ተማሪዎች ፀሎት ካደረጋችሁ በኋላ ህፃናቱ በቃል ማጥናት የጀመሩትን ፀሎት አብራችሁ ከልሱ:: የእለቱ ቀጣይ እንቅስቃሴዎች የሚከተሉት ናቸው::*

*ሀ. መዝሙሮች (ቀደም ሲል ከተማሯቸው መዝሙሮች መካከል ጥቂቶቹን ይጨምሩ)*

*<u>እንደመሬት ሁኑ</u>*

*ያሰበ ስለምድሪትዋ*
*ይገርማል በትህትናዋ፣*
*የመሬት ሰፊ ሃብቷ*
*አምላክ የሰጣት በችሮታ*
*ለፈለገ የምትሰጠው ስጦታ፣*
*ለመኖር የሚያስፈልገን በጠቅላላ*
*የሚለበስ ሆነ የሚበላ፣*
*ሆኖም ማን ሰምቷታል*
*ከናንተ ይበልጥ ሀብታም ነኝ ስትል፣*
*እስቲ ዛሬን እየው*
*በጣም ትሁት ነው፣*
*ብዙ ፍሬ ተሸክሞ*
*ይታያል ወደመሬት ዘምሞ፣*
*ሊያበላ ፍሬውን አስቀድሞ*
*ሆኖም ማን ሰምቶታል፣*
*ከናንተ ይበልጥ ሀብታም ነኝ ሲል*
*ስለዚህ ሁን እንደመሬት፣*
*እንደዛፍም ፍሬ በመስጠት*
*ወደ ክብር ሰማይ ውጣ ወደክብር፣*
*በትህትና ክንፍ ሳትገደብ ብረር::*

*ለ. ቅዱሳን ጥቅሶችን በቃል መያዝ*

*ራስን ዝቅ ማድረግ አስፈላጊ ምግባር ነው:: በአምላክ ፊት ራሱን ዝቅ የሚያደርግ ሰው የአምላክን ታላቅነትና የእራሱን ዝቅተኛነት ያወቀ ነው:: እራሱን በሙሉ አሳልፎ ለአምላክ ፈቃድ ይሰጣል:: የእራሳችንን ፈቃድና ፍላጎት ለእርሱ ፈቃድ ፍላጎት አሳልፈን ስንሰጥ አምላክ ልባችንን በደስታ ይሞላልናል:: በአምላክ ፊት ራሳችንን ዝቅ እንድናደርግ እንዲረዳን የሚከተለውን ጥቅስ በቃላችን እንያዝ::*

**"የሰው ልጅ ሆይ! በፀጋዬ እንገበኝህ ዘንድ በፊቴ ራስህን ዝቅ አድርግ::"[16]**

*ራስን ዝቅ ማድረግ*

- *ዚነብ ስትፀልይ ግንባሯን ደፍታ በትህትናና ስለአምላክ ታላቅነት እያሰበች ነው፡፡ ዚነብ ራሷን በአምላክ ፊት ዝቅ ታደርጋለች፡፡*
- *ዮንግ ፉ ስለባሃኢ ሃይማኖት ለሰዎች ከማስተማሩ በፊት ስለ አምላክ ታላቅነት ስለእራሱ ደካማነት በማሰብ፤ ከእርሱም እርዳታን ይጠይቃል፡፡ ዮንግ ፉ በአምላክ ፊት ራሱን ዝቅ አድርጓል፡፡*

*ሐ.* *የዕለቱ ትረካ*

*ከአብዱል-ባሃ እጅግ ማራኪ ባህሪያት መካከል አንዱ፣ ራሱን ዝቅ ማድረጉና ትህትናው ነው፡፡ ባሃኢዎች ታላላቅ የመጠሪያ ስሞችን ሊሰጡት በፈለጉ ጊዜ "አብዱል-ባሃ" በተሰኘው ስሙ ብቻ እንዲጠራ እንደሚፈልግ ገለፀላቸው፡፡ አብዱል-ባሃ ማለት* **"የክብሩ (የባሃ) የእግዚአብሔር አገልጋይ"** *ማለት ነው፡፡ አንዳንድ ነገሮች ከልክ ያለፈ ክብደት እንዲሰጣቸውም አይፈልግም ነበር፡፡ አንድ ቀን ከአውሮፖ አገር አብዱል-ባሃን ሊጠይቅ ባሃኢ የሆነ ሰውዬ መጣ፡፡ አብዱል-ባሃንም በተሽቆጠቆጠ ዝግጅት እራት ሊጋብዘው ተዘጋጀ፡፡ አንድ ልዩ የሆነ ልብስ የለበሰ ልጅ እጅግ ውብ የሆነ የእጅ ማስታጠቢያ ይዞ እንዲጠብቅ አድርገ፤ ከዚህም በተጨማሪ እጁን ከታጠበ በኋላ ማድረቂያ የሚሆን ሽቶ የተርከፈከፈበት ፎጣም ተዘጋጅቷል፡፡ አብዱል-ባሃ እጁን ለማስታጠብ የተዘጋጀውን ልጅ፣ ማስታጠቢያውንና ፎጣውን ሲመለከት ዓላማቸው ገባው፡፡ የዚህን ጊዜ ፈጠን ብሎ በአቅራቢያው ባገኘው ውሃ እጆቹን ታጥቦ በቁራጭ ጨርቅ እጆቹን አደረቀ፡፡ ከዚያም ጋባዦቹን በፈገግታ በመቀበል ያዘጋጁት ውሃና ፎጣ እነርሱው እንዲጠቀሙበት ጠየቃቸው፡፡*

*ሠ.* ጨዋታ "*አንዳንድ ጊዜ እረዝማለሁ*"

*አንድ ልጅ ዓይኑን በጨርቅ ይታሰርና ሌሎቹ በሙሉ በእርሱ ዙሪያ ይሁኑ፡፡ በአንድነትም እንዲህ ይበሉ፡፡*

"*እኔ በጣም ረዥም ነኝ*"(*በጣታቸው ይቁሙና የተቻላቸውን ያክል ይንጠራሩ*)
"*እኔ በጣም አጭር ነኝ*" (*ቁጢጥ ብለው የተቻላቸውን ያክል አጭር ለመሆን ይሞክሩ*)
"*አንድ ጊዜ ረዥም ነኝ*" (*እንደገና ይንጠራሩ*)
"*አንዳንድ ጊዜ አጭር ነኝ*" (*እንደገና ቁጢጥ ይበለ«*)

*አጭር ወይም ረዥም እንደሆኑ አስተማሪው በምልክት ያሳዩአቸው፡፡ ከዛም ዓይኑን ለታሰረው ልጅ፡- ልጆቹ "በአንድነት አሁን ምን እንደሆንን ገምት(ቺ) ይበሉ"*
*አይኑ የታሰረው ልጅም በልጆቹ ጽምፅ ከፍተኛነት ዝቅተኛነት ላይ ተመርኩዞ አጭር ወይም ረዥም መሆናቸውን ለመገመት ይሞክሩ፡፡*

*ረ.* ስዕል ቁጥር ስምንትን ቀለም ይቀቡ፡፡

# *ትምህርት 9*

*የእለቱን ትምህርት በቃልዎ ካጠኗቸው ፀሎቶች መካከል አንዱን በመድገም ይጀምሩ፡፡ ከዚያም ከህፃናቱ መካከል ጥቂቶቹ በቃላቸው እንዲፀልዩ ይጠይቁ፡፡ በዚህ ክፍለ ጊዜ ሕፃናቱ በትምህርት ቁጥር 4 በቃላቸው መያዝ የጀመሩትን ፀሎት ማጠናቀቅ አለባቸው፡፡ እርሶም ፀሎቱን በቃላቸው መያዛቸውን ለማረጋገጥ ክለሳ ማድረግ አለብዎ፡፡ ቀጣዮቹ የእለቱ እንቅስቃሴዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡*

*ሀ. መዝሙሮች፡-* (*ከዚህ በፊት ካጠኗቸው መዝሙሮች መካከል ጥቂቶቹን ያካቱ*)

ወንድምህን አስቀድም

ወንድምህን አስቀድም
ወንድምን ማስቀደም ቡራኬ አለው
እንደምትወደው ማሳያ መንገድ አለው፣
እህትህን ማስቀደም ቡራኬ አለው
የበለጠ ስታካፍል ሃብታም ነህ ማለት ነው::
ጠምቶኛል ርቦኛል
ለመብላት ግን ወንድሜ ይቀድማል፣
ስለዚህ ላቅርብለት ምግብና ውሃ
ረሃቡ እንዲቀል ጥሙ እንዲረካ፣
ርቦኛል ርቦኛል
እህቴም ርቧታል፣
ካለኝ ምግብ አካፍላታለሁ
መልካሙን ነገር አደረግሁ::

## ለ. ቅዱሳን ጥቅሶችን በቃል መያዝ

አምላክ ደስተኛ ህይወት እንድንኖር ይፈልጋል:: ሌሎቹን እንዴት መንከባከብና ማስደሰት እንደሚገባን ሁልጊዜ እንድናስብ ይፈልጋል:: ስለሆነም እኛ የምንፈልገውን መልካም ነገሮች ሌሎችም እንዲያገኙ መርዳት አለብን:: እንደውም ለእራሳችን ከምንመኘው የተሻለ ነገር ለሌሎች መመኘት ይኖርብናል:: እስቲ የሚከተለውን የባሃኡላህ ጥቅስ በቃላችን እንያዝ::

**"እርሱ ከራሱ በፊት ወንድሙን የሚያስቀድም የተባረከ ነው"[17]**

### የተባረከ

- በጉድጓዱ ውስጥ ውሃ ቢኖርም ጉድጓዱ ጥልቅ ስለሆነ በባሊ ውሃ መቅዳት አልተቻለም:: ኤሜሊያ ብሩህ አእምሮዋን በመጠቀም ገመድ አምጥታ ባሊውን በገመዱ ካሰረች በኋላ ጉድጓዱ ውስጥ ጨመረችው:: ከዚያም ባሊው ውሃ ሲሞላ በታሰረው ገመድ ጎትታ አወጣችው:: የኤሜሊያ ብሩህ አእምሮ የአምላክ ስጦታ ነው:: እግዚአብሔር ለኤሜሊያ ብሩህ አእምሮ በመስጠት ባረካት::

- የቪክተር ቤተሰብ በየቀኑ ጧት ቤታቸው ፀሎት ያደርጋሉ:: የቪክተር ቤተሰብ የተባረከ ነው::

### ማስበለጥ

- ጆን ዳቦና ቂጣ መብላት ይወዳል:: ከሁለቱ አንዱን መምረጥ ካለበት ግን ዳቦን መብላት ይመርጣል:: ጆን ዳቦን ከቂጣ ያስበልጣል::
- አኒንዶ እደጅ ወጥቶ ከጓደኞቹ ጋር መጫወት ወይንም እቤቱ ቀርቶ አባቱን ሥራ መርዳት ይችላል አኒንዶ ግን ከመጫወት ይልቅ አባቱን መርዳትን መረጠ:: አኒንዶ አባቱን መርዳት አስበለጠ::

ሐ. **የዕለቱ ትረካ**

አብዱል-ባሃ ውድ ያልሆኑ ልብሶችን ይመርጥ ነበር:: ትርፍ ልብስ ሲኖረው ለሌሎች ይሰጣቸዋል:: አንድ ቀን የአቆር አስተዳዳሪ እቤቱ ጋብዞት ነበር:: አብዱል-ባሃ በእለቱ ሊለብሰው የሚገባ ጥሩ ኮት የለውም ስትል ባለቤቱ አሰበች:: ስለዚህ አስቀድማ ወደ አንድ ልብስ ሰፊ ሄዳ ለአብዱል-ባሃ ጥሩ ኮት እንዲሰፋለት አዘዘች:: አሮጌው ኮት በአዲስ ኮት እንደተተካ አያስተውልም ብላ እርግጠኛ ነበረች:: አብዱል-ባሃ የሚፈልገው በጣም ንጹህ ልብስ መልበስ ብቻ ነበር:: ወደ አስተዳዳሪው ቤት የሚሄድበት ቀን ደረሰና ባለቤቱ አዲሱን ኮት ለአብዱል-ባሃ አቀረበችለት:: እርሱ ግን አሮጌውን መፈለግ ጀመረ:: አዲስ ኮት እንደማይፈልግና አሮጌውን ኮት እንዲሰጡት ጠየቀ:: ባለቤቱም ለዛሬው ግብዣ ስትል አዲስ ኮት እንዳሰፋችለት ልታብራራለት ብትሞክርም አልተቀበላትም:: አዲሱን ኮት በገዛችበት ገንዘብ እርሱ ሁልጊዜ የሚለብሰውን ረከስ ያለ አምስት ኮቶች ልትገዛ ትችል እንደነበረ ነገራት:: አንድ ኮት ላይ ለዛውም ለእርሱ ተብሎ ይህንን ያክል ገንዘብ ማውጣት አግባብ እንዳልሆነ ነገራት:: አዲስ ኮት የሚያስፈልገው ከሆነ ይህን ውድ ኮት ልብስ ሰፊው ጋር ወስዳችሁ በምትኩ ውድ ያልሆነ አምስት ኮቶች ማሰፋት ይኖርባችኋል:: "ከዚያም አየሽ ለእኔ አዲስ ኮት ከማግኘቴ በተጨማሪ ለሌሎች የምሰጠው አራት ተጨማሪ ኮቶች ይኖሩኛል"

*መ. ጨዋታዎች፡- ቀንድ አውጣ*

ሁሉም ሕፃናት እጃቸውን ተያይዘው ይሰለፉ:: በአንዱ ጫፍ ያሉ ህፃናት ሳይንቀሳቀቁ ይቁሙ:: በሌላው ጫፍ ያሉት ግን በእነሱ ዙሪያ ይሽከርከሩና ቀስ በቀስ እያደገ የሚሄድ ክብ ይፍጠሩ::

**ለየት ባለ መንገድ ለመጫወት፡-**

ሀ. በመጨረሻ የተሰለፉት በመሽከርከር ሌሎቹ በእነርሱ ዙሪያ እንዲከቡ ያድርጉ:: (አንዱ የሌላውን እግር እንዳይረግጥ ይጠንቀቁ::)

ለ. ክብ ከሰሩ በኋላ መካከል ያሉት ልጆች ቁጢጥ ይበሉና በሌሎቹ እግር ስር ይለፉ:: ይህንን ሲያደርጉ ሁሉም ህፃናት እጃቸውን መላቀቅ የለባቸውም፡፧

*ሠ. ስዕል ቁጥር ዘጠኝን ቀለም መቀባት፡፧*

# ትምህርት 10

ትምህርቱን በፀሎት ከጀመሩ በኋላ ከዚህ ቀደም ሕፃናቱ በቃል ያጠኗቸውን ሁለት ፀሎቶች አብራችሁ ከልሷቸው:: ከዚያም ወደቀጣዩቹ እንቅስቃሴዎች ይሻገሩ::

*ሀ. መዝሙሮች* (ከዚህ ቀደም ካስጠኗቸው መዝሙሮች መካከል ጥቂቶቹን ያካቱ)

<u>እውነተኝነት</u>

ከፀሐይ ይልቅ የሚያበራ እውነተኝነት (2)
ሕዝቦች ሆይ አንደበታችሁን በእርሱ አስውቡት(2)
ታማኝነት ነፍስን ያስጌጣል (2)
ታማኝነት ከፀሐይ ይበልጥ ያበራል(2)

**ለ. ጥቅሶችን በቃል መያዝ**

ህይወታችንን ለማስጌጥና ልባችንን በደስታ ለመሙላት ሲል አምላክ ስለፈጠራቸው ውብ ነገሮች ሁላችንም እናውቃለን:: ይሁንና ከቁሳዊ ነገሮች ይልቅ መንፈሳዊ ባህሪያት የሰውን ልጆች

ደስተኛ ያደርጉአቸዋል ህይወታችንን በደስታ ሊሞሉልን ከሚችሉ በጣም ድንቅ መንፈሳዊ ባህሪያት መካከል ታማኝነት አንዱ ነው። እራሳችንን በታማኝነት ካስጌጥንና የሌሎችን ሰዎች ንብረት አንወስድም። ማንንም አናታልልም። ይህንን የታማኝነት ባህሪ ሁልጊዜ ለማስታወስ እንድንችል የሚከተለውን የባሃኦላህን ጥቅስ በቃላችን እንያዝ። ይህን ማብራሪያ ለሕፃናት በሚገባ መልኩ ማስረዳት ይችላሉ።

> **"ሕዝብ ሆይ፣ አንደበታችሁን በእውነተኛነት አስውቧቸው፤ ነፍሶቻችሁንም በታማኝነት ጌጥ አስጊጧቸው።"[18]**

## ማስዋብ

- ማሊት መናፈሻ ውስጥ ውብ የጽጌረዳ አበቦች ተክላለች። የጽጌረዳ አትክልቶቹ መናፈሻውን አስውበውታል።
- ሱኒል ውሸት ይናገር ነበር። አሁን ግን የሚናገረው እውነትን ብቻ ነው። ሱኒል አንደበቱን በእውነተኛነት አስዋበ።

## ማስጌጥ

- የሚያምር የመርከብ ስዕል በግድግዳው ላይ ተለጥፏል። ስዕሉ ግድግዳውን አስጊጦታል።
- መስከረም ሲመጣ ሜዳው በሚያምሩ አበቦች ያጌጣል።
- የሲንዲ እናት ወደ አስራዘጠኝ ቀን በዓል ከመሄዳቸው በፊት እራሳቸውን ልዩ በሆነ የጆሮ ጉትቻ ያስጌጣሉ።
- አክባር ገና ትንሽ ልጅ እያለ ፀባዩን በመንፈሳዊ ባህሪያት ለማስጌጥ ወሰነ። ከዚያም እጅግ ጥሩ ፀባይ አዳበረ።

## ሐ የዕለቱ ተረካ

ሙላ ባህራም በኢራን አገር የሚኖር ጠንካራና ጽኑ ባሃኢ ነው። አንድ ቀን የሚያሳዝን መልዕክት ከአጎቱ ደረሰው። ደብዳቤው የያዘው መልእክት እንዲህ ነበር፦ አጎቱ ልጁ ይሞትበታል እናም በባሃኢ የቀብር ሥነ-ሥርዓት እንዲቀበር ይደረጋል። ይህም የሙስሊም ቀሳውስትን አናደደ። ቀሳውስቱም አጎቱን ለፖሊስ ከሰው እንዳሳሰሩት ሙላ ባህራም ከደብዳቤው ተረዳ።

ሙላ ባህራም ደብዳቤውን አንብቦ ከጨረሰ በኋላ ስለ ችግሩ በጥልቀት አሰበ። ከዚያም ወደ አንድ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣን ዘንድ በመሄድ እርዳታ ለመጠየቅ ወሰነ። ሙላ ባህራም ባለስልጣኑ ቤት ሲደርስ ሰውየው ለብዙ እንግዶች ግብዣ እያደረገ ደረሰ። ከእንግዶቹም መካከል አንዱ ሙላ ባህራምን ወደቤቱ ሲገባ በር ላይ አይቶት ይህ ቡቱቱ የለበሰን ሰው ከቤት እንዲወጣ ጠየቀ። ይሁንና የቤቱ ባለቤት ሙላ ባህራምን አይቶ በታላቅ ፍቅርና አክብሮት ወደቤቱ እንዲገባ ጋበዘው። እንግዶቹ ባለሥልጣኑ ደሃውንና ዝቅተኛውን ሙላ ባህራምን በከፍተኛ ትህትናና እንክብካቤ እንደተቀበለው ሲመለከቱ በጣም ተደነቁ። የቤቱ ባለቤትም ሙላ ባህራም በፈተና ጊዜ እንኳን እውነተኛና ታማኝ የሆነ ሰው በመሆኑ ለእርሱ ያለኝ ከበሬታ ተገቢ ነው። ሲል አስረዳቸው። ሙላ ባህራምም ችግሩን ለባለስልጣኑ ገለጸ። ባለስልጣኑም የሙላ ባህራም አጎት በአስቸኳይ እንዲፈታ የሚያዝ ደብዳቤ በታላቅ ደስታ ጻፈ። እንግዶቹም በጣም በመገረም ሙላ ባህራም እንዲህ ያለ ከበሬታ ካንድ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣን ሊያስገኝ የሚያስችል የታማኝነትና የእውነተኛነት በሕሪውና ተግባሩ እንዲነገራቸው እንግዶቹ ጋባዣቸውን ጠየቁ። ባለስልጣኑም እንዲህ ሲል አስረዳቸው፦

"ከጥቂት ዓመታት በፊት በአስቸኳይ መክፈል የሚገባኝ እዳ ነበር። ይሁንና በቂ ገንዘብ አልነበረኝም። ስለዚህ ካበዳሪዬ ጋር አንድ ስምምነት አደረግን። ይህም ስምምነት በነበረኝ ገንዘብ ምትክ ንብረት ሊቀበለኝ ነበር ሆኖም ልሰጠው ያሰብኩት ንብረትን ዋጋ ስንተምን ልንስማማ አልቻልንም። የእኔንም ሆነ የእርሱን ጓደኞች ግምትም ልንቀበልም አልፈለግንም ምክንያቱም ሁለታችንም ጓደኞቻችንን ደልለን ለእኛ እንደሚስማማን አድርገው እንዲተምኑ እናደርጋለን ብለን በየበኩላችን ስለፈራን ነበር። ስለዚህ አንድ ነጋዴ ከሰራተኞቹ መካከል አንዱን ልኮ እንዲተምንልን ጠየቅነው። እርሱም ሙላ ባህራምን ላከው። እኔን በመጥቀም እዳዬን በሙሉ መክፈል እንድችል ከፍ አድርጎ እንዲገምትልኝ ስለፈልኩ አንድ ቀን ቀደም ብዬ

ሄድኩና ብዙ ገንዘብ ሰጠሁት፡፡ ስድስት አመት ቢሰፋ ይንን ያህል ገንዘብ ሲያገኝ አይችልም ነበር፡፡ ይሁንና ገንዘቡን አልቀበልም አለ፡፡ ከዚህ ይልቅ ንብረቱን እስኪገምት በትእግስት እንድጠብቅ ነገረኝ፡፡ የሚገርመው ግን የሙሳ ባህሪም ግምት እኔ ያወጣል ብዬ ከጠበኩት በላይ ነበር፡፡ ስለዚህ በጣም ደስ ይለው ዘንድ አሁንም እጅግ ብዙ ገንዘብ ሰጠሁት፡፡ አሁንም ደግሞ አልቀበልም አለኝ፡፡ ንብረቱን በዚያ ዋጋ የተመነበት ብቸኛ ምክንያት ንብረቱ ያንን ያክል ዋጋ ስለሚያወጣ ነው አለ፡፡ የንብረትን ዋጋ መተመን የሥራው ክፍል ስለሆነና ለዚህም ደሞዝ ስለሚከፈለው ከዚህ ሌላ ተጨማሪ ገንዘብ መቀበል ተገቢ እንዳልሆነ ገለጸልኝ፡፡

ሙሳ ባህሪም በዚህ ዘመን የማይገኝ ታማኝነትና ሐቀኝነት አለው ለምን እንዳልኳችሁ አሁን ሲገባችሁ ይችላል፡፡ ሁሉም ሰው እንደ ሙሳ ባህሪም ታማኝ ቢሆን ምንኛ ጥሩ ነበር፡፡" ሲል ባለሥልጣኑ ለእንግዶቹ አስረዳቸው፡፡

*መ. ጨዋታ፡-*

*አስተማሪው በተከታታይ የቅርጾችን ስም ዝርዝር ይጠራ (ለምሳሌ፡- ክብ፣ ሦስት ማዕዘንና ካሬ) ከዛም አንደኛውን ልጅ በቅድመ--ተከተሉ መሰረት እንዲደግም ይጥይቀው፣ በመቀጠል በቅድመ--ተከተሉ መሰረት እንዲስላቸው ያድረግ፡፡ ለእያንዳንዱ ልጅም ቅድመ--ተከተሎቹን በመቀያየር በርካታ እድሎች ይሰጡት፡፡ ልጁ ሶስት ቅድመ--ተከተሎችን ማስታወስ ካልቻለ ባለሁለት ቅድመ--ተከተል ይሰጠው፡፡ ባለሶስት ቅድመ--ተከተል ቀላል ከሆነ ባለአራት ቅደመ--ተከተል ያሰጠው፡፡ በዚህ ሁኔታ ጨዋታውን ማካሄድ ይችላሉ፡፡*

***በተለየ መንገድ ለመጫወት፡-***

*ሀ. የቅርጾቹን ስም ዝርዝር በቃል ከመንገር በተጨማሪ የተለያዩ ቅርጾች የተሳለባቸውን ካርዶች ማሳየት ይቻላል፡፡ ከካርዶቹ አንድ በአንድ ማሳየት ጊዜ ወስደው በደንብ ከተመለከቱት በኋላ በጀመሪያ በቃላቸው እንዲጠሩ ማድረግ በመቀጠልም እንዲስሏቸው ማድረግ፡፡*

*ለ. በአካል እንቅስቃሴ ቅድመ--ተከተል መጫወትም ይቻላል፡፡ ለምሳሌ፡- በመዝለል፣ በመዞር፣ የእግርን ጣቶች በመንካት፣ አፍንጫን በመንካት፣ በማጨብጨብ፣ ወደፊት በመራመድ፡፡ ይህን እንቅስቃሴ በቅደም ተከተሉ መሠረት እንዲተገብሩት ማድረግ፡፡*

*ሐ. ስዕል ቁጥር አስርን ቀለም መቀባት፡፡*

# *ትምህርት 11*

*ከዚህ ክፍለ ጊዜ አንስቶ ባሉት ተከታታይ አራት ክፍለ ጊዜዎች ሕፃናቱ አዲስ ፀሎት ይማራሉ፡፡ ስለዚህ የዕለቱ ትምህርት በፀሎቶች ከተጀመረ በኋላ በሚቀጥለው ፀሎት ውስጥ ያሉ ቃላትና ሐረጎችን ትርጉም ሊያብራራላቸውና የመጀመሪያዎቹን ጥቂት ሐረጎች በቃላቸው እንዲይዙ ሊረዷቸው ይገባል፡፡ ፀሎቱን ለአራት ከፍለው በየቀኑ አንዱን ክፍል ብቻ በቃል እንዲይዙ ማድረግን አይርሱ፡፡*

**"ጌታዬ ሆይ! ጌታዬ ሆይ! በለጋነት ዕድሜ ያለሁ ሕፃን ነኝ፡፡ ከምህረትህ ጡት ወተት መግበኝ% በፍቅርህ እቅፍ ውስጥ አሰልጥነኝ፣ በአንተ መርሆ ትምህርት ቤት አስተምረኝ፣ በበረከትህ ጥላ ሥር አጎልምሰኝ፡፡ ከጨለማ አውጣኝ፣ ደማቅ ብርሃን አድርገኝ፣ ከደስታ ማጣት አድነኝ፣ የጽጌረዳ አትክልት ሥፍራ አበባ አድርገኝ፣ የደጅ--ሰላምህ አገልጋይ እንድሆን አድርገኝ፣ የጻድቃ ንንም ዝንባሌና ጠባይ አጎናጽፈኝ% ለሰው ዘር ዓለም የበረከት መንስኤ አድርገኝ፣ በራሴም ላይ የዘላለም ሕይወት አክሊል ጫንልኝ!**

**በእውነቱ አንተ ኃይል የተመላህ፣ ኃያሉ ሁሉን የምታይ ሰሚው ነህና፡፡"[19]**

***የዕለቱ ክፍለ--ጊዜ ቀጣይ እንቅስቃሴዎች ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፡-***

ሀ. መዝሙሮች (ከዚህ በፊት ከተማሯቸው መዝሙሮች ጥቂቶቹን ያካትቱ)

የለጋስነት ምንጭ

እንደ ምንጭ ሁን እንደፏፏቴ ገስግስ
እንደ ጅረት ሳያቋርጥ እንደሚፈስ፣
ይህንን ያደረገ ሳያመነታ
ይጥለቀለቃል በደስታ፣
ልብህን በየዕለቱ መርምር
ልትሰጥ የምትችለው ካለ ለዘወትር፣
የሕይወትህ ግብ ደስታ ይሁን
መስጠት ይገባል ልብን ሆነ ነፍስን፣
ይህንን ብታደርግ ለዘወትር
ታያለህ እግዚያብሔር ከአንተ ጋር ሲያድር::

ለ. አምላክ ለፍጡሮቹ ቸር ነው:: ሁላችንንም ይንከባከባል:: በየቀኑ የምንመገበውን ይሰጠናል:: ከዚህም ሌላ ሌሎች ብዙ ስጦታዎችን ለግሶናል:: ከእነዚህም መካከል መስማት፣ ማየት፣ ማሰብ ጥቂቶቹ ናቸው:: እርሱ ለእኛ ቸር እንደሆነ ሁሉ እኛም አንዳችን ለሌላችን ቸር እንድንሆን ይፈልጋል:: የእ ኛን እርዳታ ለሚሹ እርዳታችንን መስጠት ይኖርብናል:: ቸር መሆን እንዳለብን ዘወትር እንድናስታ ውስ የሚከተለውን የባሃኦላህ ጥቅስ በቃላቸን እንያዝ::

**"...መስጠትና መቸር የእኔ ባሕሪያት ናቸው፤ በባህሪያቴ ራሱን ያስጌጠ የበጀው ነው::"[20]**

## ቸር

- ራምና ራጂሽ ገንዘብ አጠራቅመው ነበር:: ባጠራቀሙትም ገንዘብ ለታናሽ እህቶቻቸውና ወንድሞቻቸው መጽሐፍት ለመግዛት ወሰኑ:: ራመና ራጃሽ ቸር ናቸው::
- ወ/ሮ ማርፊይ በማለዳ ተነስተው እስከ ረፋዱ ድረስ ዳቦ ሲጋግሩ ነበር:: የጋገሩትን ዳቦዎች ወደ ገበያ ለመሸጥ ከመውሰዳቸው በፊት ሁለት ትልልቅ ዳቦዎችን ለጎረቤታቸው ሰጡ:: ወ/ሮ ማርፊይ ቸር ናቸው::

## ባህሪ

- ጆል አንድ ውብ ጽጌረዳ ለአስተማሪው ስጦታ ሊያበረክት አመጣ:: ውበት የጽጌረዳ ባሕሪ ነው::
- ድንጋዩ በጣም ጠንካራ ነው:: ጥንካሬ የድንጋይ ባሕሪ ነው::
- የቻርሌን አስተማሪው "ከመልካም ባህሪያትህ መካከል አንዱ ጠንክሮ ለመስራት ያለህ ፈቃደኝነት ነው" በማለት ቸርነትን አበረታቱት::

## ማስጌጥ

- ዛሬ የአስራዘጠኝ ቀን በዓል ነው:: ህፃናቱ በስባሰባው አዳራሽ ውስጥ አበባዎችን አኑረው ነበር:: አበባዎቹ የስብሰባውን አዳራሽ አስጌጡት::
- ታ ጄን ውብ ፈገግታ አላት:: ብዙውን ጊዜ ፈገግታዋ ፊቷን ያስጌጠዋል::

## ሐ. የዕለቱ ተረካ

በባሃኦላህና በቤተሰቡ ላይ የደረሱት ችግሮችና መከራዎች ከመጀመራቸው በፊት ባሃኦላህ ሰፊ መሬትና ብዙ በጎች ነበሩት፡፡ እነዚህንም በጎች ተከፋፍለው የሚጠብቁ እረኞችንም አሰማርቶ ነበር፡፡ አንድ ቀን እነዚህ እረኞች ስራቸውን በሚገባ እያከናወኑ እንደሆነ እንዲጎበኝ ልጁን አብዱል-ባሃን ይልከዋል፡፡ በዚያን ጊዜ አብዱል-ባሃ ታዳጊ ወጣት ነበር፡፡ አብዱል-ባሃ ጉብኝቱን ጨርሶ ወደ ቤቱ ሊመለስ ሲዘጋጅ አብሮት ሲዘዋወር የነበረው ሰው "**አባትህ በሚመጡ ጊዜ ለእያንዳንዱ እረኛ ስጦታ የመስጠት ልማድ አላቸው፡፡**" አለው አብዱል-ባሃ የሚያበረክተው ስጦታ ስላልያዘ ለጊዜው ዝም አለ፡፡ ይሁንና እረኞቹ ስጦታ እየተጠባበቁ እንደሆነ በመወትወት ነገረው፡፡ ይህን ጊዜ አብዱል-ባሃ አንድ ሃሳብ ብልጭ አለለትና በጣም ተደሰተ፡፡ ለእረኞቹ የሚጠብቋቸውን በጎች በስጦታ አበረክትላቸዋለሁ ሲል አሰበ፡፡ አብዱል-ባሃ ለእረኞቹ ለማድረግ ስላሰበው ችሮታ ባሃኦላህ በሰማ ጊዜ በጣም ተደሰተ፡፡ ሁሉም ሰው አብዱል-ባሃን የሚንከባከበው አንድ ቀን እራሱንም ጭምር ለሁሉም ስለሚሰጥ ነው በማለት በቀልድ መልክ ተናገረ፡፡ በእርግጥም አብዱል-ባሃ ሕይወቱን ሙሉ ያደረገው ይህንኑ ነበር፡፡ አንድነት በመካከላችን እንዲሰፍናና እውነተኛ ደስታ እንድናገኝ ያለውን ሁሉና እያንዳንዷን የሕይወቱን ደቂቃ ሳይቀር ሰጠ፡፡

### መ. ጨዋታ፡- መረዳዳት

ሁለት ሶስት ወይም አራት የሚሆኑ ሕፃናት ጀርባ ለጀርባ ተደጋግፈው ቁጢጥ ይበሉ፡፡ ከዚያም ሁሉም በአንድ ላይ በመደጋገፍ ለመነሳት ይሞክሩ፡፡

### ሠ. ስዕል ቁጥር አስራ አንድን ቀለም መቀባት፡፡

# ትምህርት 12

ክፍለ-ጊዜው በፀሎት ይጀምርና ባለፈው የትምህርት ክፍለ--ጊዜ በቃል መያዝ የጀመሩትን ፀሎት ያጥኑ፡፡

ቀጣዮቹ የእለቱ እንቅስቃሴዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ. መዝሙሮች (ባለፉት ክፍለ ጊዜዎች ካጠኗቸው መዝሙሮች መካከል ጥቂቶቹን ያካትቱ)

<u>የእግዚአብሔር ፍጡራን</u>

በዚች ታላቅ ዓለም የተፈጠሩ
የሚራመዱ ሆነ የሚበሩ፣
እንደአንተና እንደኔ
ናቸው የአምላክ (ምስለኔ)፣
ደግነትን አሳያቸው ከልብ
የእግዚአብሔርን ፍጥረት ተንከባከብ፣
ይወርድልሃል የቡራኬ ዝናብ
በረንዳው ላይ ያለው ውሻ፣
ታማኝ ጓደኛ ክብካቤን የሚሻ
የሚታለቡ ላሞች ፣
ማር የሚሰጡ ንቦች
አዕዋፋት ጠዋት ጠዋት የሚዘምሩ፣
ይመስገኑ ይከበሩ
እላያችን ላይ የምትዘለው ድመት፣
አህያው ሸክም የምንጭንበት
ሁሉም ናቸው ተፈቃሪ
የተገኙ ከፈጣሪ፡፡

## ለ. ቅዱሳን ጥቅሶችን በቃል መያዝ

ባሃኢዎች ለሰው ልጆች ደህንነት እንዲሰሩ አምላክ ይፈልጋል፡፡ የሰውን ልጅ የሚከፋፍሉ ነገሮች ተወግደው ሁሉም ሰው እንደአንድ ቤተሰብ እንዲኖር ይሻል፡፡ ይህ ሆኖ እንድናይ በልባችን ውስጥ ለሌሎች ያለንን መጥፎ ስሜት ማስወገድ አለብን፡፡ ከሌላ ሃይማኖት ተከታዮች፣ ከሁሉም ብሔረሰብ ዘሮችና ከሌላ አገር ሰዎችም ጋር በደግነትና በፍቅር መቀላቀል አለብን፡፡ ይህንን ሁልጊዜ ለማስታወስ የሚከተለውን የባሃኦላህን ጥቅስ በቃላችን እንያዝ፡፡

**"...እርሱ፣ከሁሉም ሰዎች ጋር በከፍተኛ የደግነትና የፍቅር መንፈስ የሚቀሳቀል የተባረከ ነው፡፡"**[21]

## ሐ. የዕለቱ ትረካ

ሐኪም አቃጃን አይሁድ ዶክተር ነው፡፡ አንድ ቀን ሙሃመድ ባቂር የተባለ ሰውዬ የታመመች ሚስቱን እንዲያክምለት ይጠራዋል፡፡ ሐኪም አቃጃንም የሙስሊሙን ሚስት ከመረመራት በኋላ ትኩሳቷን ለመቀነስ ብሎ ኪኒን ሰጥቷት ወደቤቱ ተመለሰ፡፡

ከጥቂት ሰዓታት በኋላ ሙሃመድ ባቂር በድንጋጤ ተውጦ ወደ አይሁዱ ሐኪም አቃጃን ቤት በድጋሚ ተመልሶ ይመጣል፡፡ ሚስቱ ህመሙ ብሶባት ልትሞት እንደደረሰችም ይነግረዋል፡፡ ጊዜው መሽቶ ስለነበር ሙህመድ ባቂር ኩራዝ ይዞ ፊት ፊት ሐኪም አቃጃን ኋላ ኋላ እየተቻኮሉ ህመምተኛዋ ዘንድ ደረሱ፡፡ ሐኪም አቃጃን ህመምተኛዋን እንደተመለከታት የፈጸመውን ከባድ ስህተት ስለተገነዘበ በጣም ደነገጠ፡፡ በመጀመሪያ በመጣ ጊዜ ትኩሳት ማስታገሻ መስሎት በስህተት የሰጣት ኪኒን በጣም ጎድቷት ነበር፡፡ በዚህ ስህተት ምክንያት ሴትየዋ በጣም ከመታመሟ የተነሳ ለትሞት ደርሳለች፡፡ በተጨማሪ ደግሞ በከተማው ያሉ ሙስሊሞች በአይሁዶች ላይ የሚያደርሱትን ከፍተኛ በደል ሲያስታውስ ሴትዮዋ ከሞተች እርሱ፤ ቤተሰቦቹና በከተማው ያሉ አይሁዶች በሙሉ ይገደላሉ ሲል ፈራ፡፡ ይህን ሲያስብ በጣም በፍርሃት ከመረበሹ የተነሳ ሙህመድ ባቂር የሰነዘረለትን ጥያቄ አድምጦ መልስ የሰጠው በመከራ ነበር፡፡ ሙህመድ ባቂር ለምን ደንግጦ እንደሚንቀጠቀጥ ጠየቀው፡፡ ሐኪሙም እውነቱን ተናገረ፡፡ የፈፀመውን ስህተት ገለጸ፡፡ ሙህመድ ባቂር ግን ያልጠበቀውን መልስ ሰጠው፡፡ "**ሰው ሆኖ ስህተት የማይፈጽም የለም፡፡ አውቀህ ያደረግከው ነገር አይደለም፡፡ አይዞህ ባለቤቴ ብትሞትም ማንም አትወነጀልም፡፡**" አለው፡፡

ሐኪሙ የሰማውን ማመን አልቻለም፡፡ አንድ ሙስሊም አንድን አይሁድ እንዲህ ባለ ትህትና ሊያናግር የሚቻል አይመስለውም ነበር፡፡ ሐኪም አቃጃን በመገረም የሴትየዋን ሕይወት ለማዳን መጣደፍ ጀመረ ቅርብ ወዳለ መድሃኒት ቤት ሄዶ ሊያድናት የሚችለውን መድኃኒት ገዛ፡፡ ሌሊቱን በሙሉም ከእርሷ ጋር በመሆን ሕይወቷን ለማዳን የተቻለውን ሁሉ አደረገ፡፡ ሙሐመድ ባቂርም ለሐኪሙ የሚችለውን ያህል እርዳታ አደረክላት፡፡ ከፍተኛ ጨዋነት፣ ወዳጅነትና ደግነትም አሳየው፡፡ በመጨረሻም ሊነጋጋ ሲል ሴትየዋ እየተሻላት መጣ ከሞት የመትረፍ ምልክቶችን አሳየች፡፡

ሐኪም አቃጃን ሙሐመድ ባቂር ባሳየው ወዳጅነትና ደግነት በጣም ስለተደነቀ መገረሙን መደበቅ ስላልቻለ ለምን እንደዚህ ባለ ከፍተኛ ደግነት እንዳስተናገደው ሙህመድ ባቂርን ጠየቀው፡፡ ሙሐመድ ባቂርም ምክንያቱን እንዲህ በማለት አሰረዳው፡- "**እኔና ባለቤቴ ባሃኢዎች ስለሆንን ከሁሉም ሃይማኖት ተከታዮች ጋር በሰላምና በፍቅር እንኖራለን፡፡**" ሐኪም አቃጃን ወደ ባሃኢ እምነት የተሳበውና ባሃኢ የሆነው በዚህ ሁኔታ ነበር፡፡

## መ. ጨዋታ፡- መልካም ባሕሪዎችን ማወቅ

ሁሉም ሕፃናት እጅ ለእጅ ተያይዘው ክብ ይስሩ፡፡ አስተማሪዋ በእጇ አንድ ነገር ደብቃ ትያዝ፡፡ በእጇ የደ በቀችው ነገር መንፈሳዊ ባህሪያትን ይወክል ፡፡ ለምሳሌ፡- "ደግነት" "ቸርነት"ወዘተ... አስተማሪዋ ከአንዱ ልጅ ወደ ሌላው ልጅ እየሄደች እያንዳንዱ ልጅ እጅ ውስጥ የደበቀችውን ነገር የተወች እየመሰለች ስማቸውን እየጠራች "ዮሐንስ ደግ ነው፣ ማርታ ደግ ናት% ይሳቅ ደግ ነው%" ወዘተ... እያለች ትለፍ፡፡ እያንዳንዱ ልጅም የተደበቀውን ነገር የተቀበለ እንዲመስል እጁን

ይጨብጥ። አስተማሪዋ ከልጆቹ መካ ከል ለአንዱ ልጅ የደበቀችውን ትስጥ። በዚህ መንገድ ልጆቹን ካዳረሰች በኋላ እንዲጫወቱ ታድርግ።

### ሠ. ስዕል ቁጥር አስራ ሁለትን ቀለም መቀባት

# ትምህርት 13

**የእለቱ ትምህርት እርስዎና ጥቂት ሕፃናት በምትደግሟቸው ፀሎቶች ይጀመር። ከዚያም በትምህርት ቁጥር 11 በቃል ማጥናት የጀመሩትን ፀሎት ቀጣይ ክፍል ያጥኑ።**

**ሌሎቹ የዚህ ክፍለ-ጊዜ እንቅስቃሴዎች የሚከተሉት ናቸው።**

### ሀ. መዝሙሮች (ባለፉት ክፍለ ጊዜዎች ከተማሯቸው መዝሙሮች መካከል ጥቂቶቹን ያካቱ)

<u>ደስተኛ መሆን</u>

በእምነታችን አንድ የሚታወቅ ነገር ቢኖር
በቃል ሳይሆን ሁሉም ነገር በተግባር፣
የሚሰራ እንጂ የለም የሚወራ
ሕይወታችን በተግባር ይመራ ፣
መሆን ያስፈልገናል ደስተኛ
ጠንካራ ሰራተኛ፣
እንድንሆን አገልጋዩ
የሕይወት ሙሉ ተከታዩ፣
የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ላክብር
አዎ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ላክብር፣
በዚህ በጠፊ ከንቱ ዓለም ሳለ
ማወቅ የሚገባ ብዙ ነገር አለ፣
ሰዎች ከንቱ ንግግርን ንቀዋል
የምትናገረውን በተግባር አውለው ይሉሃል።

### ለ. ቅዱሳን ጥቅሶችን በቃል መያዝ

አምላክ ኃይል የተመላውና አፍቃሪ ነው። ወሰን ከሌለው ፍቅሩ የተነሳ ሰውን ፈጠረ። ስለዚህ እርሱን ልናፈቅረውና ትእዛዛቱንም ልናከብር ይገባል። ትእዛዛቱም ቀላልም ይሁኑ ከባድ ወይም ለማክበር ፈተናና ችግርን የሚያስከትሉ ቢሆኑም መከበር አለባቸው። ለአምላክ ታዛዦች በፈተናውም ጊዜ ታጋሾች መሆን አለብን። ይህንን ለማስታወስ እንዲረዳን የሚከተለውን የባሃኦላህን ጥቅስ በቃላችን እንያዝ።

**“የፍቅር ምልክቱ በትእዛዜ መጽናትና በፈተናዎቼም መታገስ ነው”[22]**

### ምልክት

- ትላንትና ማታ ናንሲ ታማ ነበር። ዛሬ በጣም ደስተኛ ሆና ዋለች። አይኖቿም አልፈዘዙም። ይህ ናንሲ እየተሻላት እንደሆነ የሚያሳይ ምልክት ነው።

- ኮሊ ለእህቷ ልዩ ስጦታ አበረከተችላት፡፡ ኮሊ እህቷን በጣም ትወዳታለች፡፡ ስጦታው የፍቅሯ ምልክት ነው፡፡

## ጽናት

- ሕፃኑ ልጅ ቀኑን ሙሉ ሲያለቅስ ቢውልም ጄሪ እሹሩሩ ማለቷንና ማባበሏን አላቋረጠችም ነበር፡፡ ጄሪ ህፃኑ ማልቀሱን እስኪያቆም ድረስ በጽናት ማባበሏን ቀጠለች፡፡
- ልጆቹ አሾክ በድብድብ እንዲሳተፍ ሊያግባቡት ሞከሩ፡፡ አሾክ ግን መደባደብ ጥሩ እንዳልሆነ ስለሚያውቅ ሳይስማማ ቀረ፡፡ አሾክ በድብድብ ባለመሳተፉ ጽናት አሳየ፡፡

## ትእዛዝ

- በየቀኑ መጸለይ የአምላክ ትእዛዝ ስለሆነ ጄሪ ሁልጊዜ ጧትና ማታ ፀሎት ታደርጋለች፡፡ በመፀለይም ጄሪ የአምላክን ትእዛዝ ታከብራለች፡፡
- ተሬሳ ውሸት አትናገርም፡፡ ተሬሳ እውነተኛ እንድንሆን የሚያዘውን የአምላክ ትእዛዝ ታከብራለች፡፡

## ሐ. የዕለቱ ትረካ

ከእለታት አንድ ቀን ሐጂ ሙሐመድ የሚባል ጎበዝ አዳኝ ሰውዬ በኢራን አገር ይኖር ነበር፡፡ ተኩሶ ኢላማውን አይስትም፡፡ ፈረስ ላይ ተቀምጦ በፍጥነት እየጋለበ እንኳን በመብረር ላይ ያለችን ወፍ ተኩሶ ይጥላል፡፡ አንድ ቀን የአደን ጠመንጃውን ይዞ እየሄደ ሳለ ከባሃኦላህ ጋር ሽርሽር የወጡ ብዙ ባሃኢዎችን ያገኛል ከእነርሱም ጋር ተቀላቀለ፡፡

ትንሽ ቆይቶ ሐጂ ሙሀመድ አንዲት ወፍ አይቶ ሊተኩስባት ጠመንጃውን ማመቻቸት ጀመረ፡፡ ይህን ጊዜ ባሃኦላህ አይቶት ኖሮ ወፎቹን እንዳይገድል አዘዘው፡፡ የሐጂ ሙሀመድ ሐሳብ እጅግ በጣም በሚወደው አደን ላይ ስለነበር የባሃኦላህን ትእዛዝ ችላ አለ፡፡ ስለዚህ በተመለከታቸው ወፎች ላይ ሁሉ መተኮሱን ቀጠለ፡፡ ነገር ግን ከተኮሳቸው ጥይቶች መካከል አንዱም ወፎቹን ባለመምታቱ በጣም ተገረመ፡፡ ብዙ ጊዜ ደጋግሞ ቢተኩስም ምንም ወፍ ሊገድል አልቻለም፡፡ ትልልቅና ትናንሽ ወፎች ላይ ድጋግሞ ቢተኩስም ሊሳካለት አልቻለም፡፡

ከሽርሽሩ ቦታ በመመለስ ላይ እያሉ የሐጂ ሙሀመድ ዓይን አንድ የሚያምር ትልቅ ነጭ ወፍ ላይ አረፈ፡፡ ወፉ በጣም ትልቅ ስለሆነ በፍጥነት መብረር ስለማይችል ይህንንስ መግደል አያቅተኝም ሲል ሐጂ ሙሀመድ አሰበ፡፡ ቢተኩስበትም ወፉን ሳይመታው ቀረ፡፡

ሐጂ ሙሃመድ በጣም በመገረሙ ስለነገሩ ማሰብ ጀመረ በድንገትም አንድ እጅግ ጠቃሚ የሆነ ነገር በጭንቅላቱ መጣ፡፡ ባሃኦላህ የሰጠውን ግልጽ ትእዛዝ አስታወሰ፡፡ በአደኑ በመመሰጡ የተነሳ የባሃኦላህን ትእዛዝ አላከበረም ነበር፡፡ ያን ቀን ሐጂ ሙሀመድ ሁልጊዜ የአምላክን ትእዛዝ ለማክበር ጠንካራ ውሳኔ አደረገ፡፡

## መ. ጨዋታ

አንድ ልጅ ዓይኑን ይታሰር፡፡ ሌላ ልጅ እንደ መሪው ይሁንና አደጋ እንዳይደርስበት እየተጠነቀቀ ወደ ተለያየ አቅጣጫ እየመራ ይወሰደው፡፡

### ለየት ባለ መንገድ ለመጫወት

ሀ. የሕፃናቱን ትእዛዝ የመስጠትና የመቀበል ችሎታ ለማዳበር ዓይኑ የታሰረውን ልጅ ሌላ ልጅ በድምጽ ብቻ ወደተለያየ አቅጣጫ ይምራው፡፡ ዓይኑ የታሰረው ልጅ ምናልባት እንዳይወድቅ መሪው (ወይም አስተማሪው) ከቅርብ ሆኖ ይጠብቀው፡፡

## ሠ. ስዕል ቁጥር አስራ ሶስትን ቀለም መቀባት፡፡

# ትምህርት 14

**ክፍለ-ጊዜውን በፀሎት ከጀመራችሁ በኂላ፣ የእለቱን በቃል የማጥናት ክፍለ-ጊዜን፣ በትምህርት 11 የጀመሩትን የቃል ጥናት የሚያገባድዱበት ይሁን።**

**የዕለቱ ትምህርት ቀጣይ እንቅስቃሴዎች የሚከተሉት ናቸው።**

*ሀ. መዝሙሮች (ቀደም ባሉት ክፍለ ጊዜዎች ካጠኗቸው መዝሙሮች ጥቂቶቹን ይጨምሩ)*

*ፍቅሬ ምሽግህ ነው*

*የህያው ልጅ ሆይ!*
*ፍቅሬ ምሽግህ ነው*
*እዚያ የሚገባ ሰላምና ዋስታና አለው፣*
*ከዚያ ፊቱን የሚመልስ*
*በእውነት ተንከራትቶ ይጠፋል*
*የሕያው ልጅ ሆይ ፍቅሬ ምሽግህ ነው*
*የሕያው ልጅ ሆይ ፍቅሬ ምሽግህ ነው።*

## ለ. ቅዱሳን ጥቅሶችን በቃል መያዝ

*የአምላክ ፍቅር እንደ ምሽግ ነው። ምሽግ ማለት ጠንካራ አጥር፣ ግርግዳ፣ በሮችና መስኮቶች እንዳሉት ማንም ሊደፍረው በማይችል ቤት የመሰላል። ማንም ሊጎዳን ቢፈልግ ወደዚህ ምሽግ ብንገባ ከሁሉም እንጠበቃለን። አምላክን ማፍቀር በምሽግ ውስጥ እንደመሆን ነው። በዚህ ምሽግ ውስጥ ከሆንን ማንም ሊጎዳን አይችልም% ደህንነት እናገኛለን። ይህንን ለማስታወስ የሚከተለውን የባሃኦላህን ጥቅስ በቃላችን እንያዝ።*

**“የሕያው ልጅ ሆይ! ፍቅሬ ምሽጌ ነው፤ ወደዚያ የሚገባ ደህንነትና ዋስትና አለው፤ ፊቱን ከዚያ የሚመልስ ግን በእርግጥ ተንከራቶ ይጠፋል።”** [23]

### *ምሽግ*

- *እራሳቸውን ከጠላቶች ለመከላከል ሰዎቹ በከተማው ዙሪያ ትልቅ ግንብ ሰሩ። ከተማው ምሽግ ሆነ።*
- *አንድ የጎረቤት ልጅ እነዳኒ ቤት ላይ ሁል ጊዜ ድንጋይ ይወረውር ነበር። በመጀመሪያ ይህ ዳኒን ስለሚያስደነግጠው ይናደድ ነበር። ይሁንና የአምላክን ትእዛዝ በማስታወስና በእርሱም የጠባቂነት ምሽግ በመተማመን በልጁ ላይ ድንጋይ ለመወርወር ያሰበውን ሃሳብ ተወው። የአምላክ ትእዛዝ ለዳኒ ምሽግ ሆነለት። ከጥቂት ጊዜ በኂላ ልጁ የዳኒ ጓደኛ ሆነ።*

### *ደህንነትና ዋስትና*

- *በጎቹ ወደጫካ ውስጥ ገብተው ተሰወሩ። ተኩላዎቹ እንዳይበሏቸው ባሂይህ በጎቹን ፈልጋ ማግኘት ነበረባት። እናም ፈልጋ አገኛቻቸው ደህንነትና ዋስትናቸው እንዲጠበቅ ወደ በረታቸው አስገባቻቸው።*

- የማርክ ጓደኞች ማርክ ያደረጋቸውን ጥፋቶች እያነሱ ይወቅሱት ነበር፡፡ የማርክ ልብ በመጀመሪያ አዘነ፡፡ በኋላ ግን ልቡን ወደ አምላክ መለሰና በፍቅሩ ተሞላ፡፡ ወደ አምላክ ልቡን ሲመልስ ማርክ ደህንነትና ዋስትናን አገኘ፡፡

**መጥፋት**

- እንጨት እሳት ውስጥ ሲገባ ይነዳል፡፡ እንጨትነቱ ይጠፋል፡፡
- ቅጠሎች ከዛፍ ላይ ሲረግፉ ቀስ በቀስ ይደርቁና በስብሰው አፈር ይሆናሉ፡፡ ቅጠሎቹ ይጠፋሉ፡፡

## ሠ. የዕለቱ ትረካ

ከዕለታት አንድ ቀን ሦስት ትንንሽ አሣዎች በትልቅ ሐይቅ ውስጥ ይኖሩ ነበር፡፡ ቀኑን ሙሉ በሐይቁ ውስጥ በደስታ ሲዋኙና ሲጫወቱ ይውላሉ፡፡ ሐይቁ ከአደጋ የተጠበቀ ነበር፡፡ ትልልቅ አሳዎችም ሆነ የተራቡ አዞዎች በሐይቁ ውስጥ የሉም፡፡ ሐይቁ የተረጋጋና አሳዎቹን ከእናታቸው ነጥሎ ወደዳር የሚጥላቸው ማእበል የሌለው ነበር፡፡ በሐይቁ ውስጥ ሌሎችም አሳዎች ይኖሩ ስለነበር እነዚህ ሶስት አሳዎች አብረዋቸው የሚጫወቱ ብዙ ጓደኞች ነበሯቸው፡፡ የዋና ውድድር ያደርጋሉ፤ እየዘለሉ ወደ ውሃው ውስጥ ይጠልቃሉ፡፡ ድብብቆሽም ይጫወታሉ፡፡ ከድንጋይ ወይም ከተክል በስተጀርባ ይደበቁና እናታቸው ወይም አባታቸው ወይም አያታቸው ሲያልፉ በድንገት ወጥተው በመጮህ ያስደነግጧቸዋል፡፡ ዘመዶቻቸውም እንደደነገጡ ያስመስሉላቸዋል፡፡ ይሁንና በሐይቁ ውስጥ ምንም የሚያስፈራ ነገር እንደሌለ ያውቃሉ፡፡

አንድ ቀን ሶስቱ አሳዎች ሄደው ወደማያውቁበት የሐይቁ አካባቢ ሄዱ፡፡ መጫወት ፣ በፍጥነት መዋኘትና በዓየር ላይ መዝለል ጀመሩ፡፡ ከሦስቱ አንዱ በድንገት ከፍ ብሎ ሲዘል አንድ ትልቅ ግድግዳ በሩቅ አየ፡፡ እንደዚህ አይነት ነገር ከዚህ በፊት አይቶ አያውቅም፡፡ በፍጥነት ወደውሃ ውስጥ ጥልቆ ያየውን ነገር ለሁለቱ ወንድሞቹ ነገራቸው፡፡ ነገር ግን ወንድሞቹ አላመኑትም፡፡ በሐይቃችን ውስጥ ግድግዳ ምን ይሰራል? ሲሉ ጠየቁት፡፡ እኔ እንጃ ሲል መለሰላቸው፡፡ ነገርግን እኔን ካላመናችሁ ከሐይቁ በላይ ዝለሉና ተመልከቱ፡፡

ሁለቱ ወንድማማቾች በወንድማቸው ላይ እየሳቁ ከፍ ብለው ለመዝለል እንዲችሉ በፍጥነት መዋኘት ጀመሩ፡፡ ነገር ግን ገና ሳይዘሉ ከግድግዳው ጋር ተጋጩ፡፡ ውይ! ሲሉ ጮሁ፡፡ የተጋጨውን አፍንጫቸውን ይዘው አንገታቸውን ከውሃው ውጭ ብቅ አድርገው ተመለከቱ፡፡ እውነትም ግድግዳ አለ ትልቅም ነው፡፡ ወደ ሐይቁ ዳር እየዋኙ ተጠጉ፡፡ ለካስ ግድግዳው እስከዳርቻው ይዘልቃል! ወደ ጎንም ዋኙ፡፡ ግድግዳው እዛም ድረስ አለ፡፡ ወደታችም ዋኙ፡፡ ግድግዳውም ወደታችም አለ፡፡ ሶስቱ ትንንሽ አሳዎች ለምን ይህ ግድግዳ እንደተደረገ ሊገባቸው ስላልቻለ አያታቸውን ለመጠየቅ ወሰኑ፡፡ እቤታቸው ሲደርሱ አያታቸው እንቅልፍ ይዟቸው አገኟቸው፡፡ ስለግድግዳው ለማወቅ በጣም ስለጓጉ ከእንቅልፋቸው ቀሰቀሷቸው፡፡

"አያቴ!" ሲሉ ሁሉም በአንድ ጊዜ ጮሁ፡፡
"አንድ ግድግዳ አለ!" አለ የመጀመሪያው አሳ፡፡
"ስፋቱ ከዳር እስከዳር ይደርሳል! አለ" ሌላው፡፡
"ከላይ እስከታችም ይዘልቃል!" አለ ሦስተኛው
"ምን?" አሉ አያትየው "ግድግዳ?"
"አዎ!" ሲሉ ሦስቱም በአንድ ላይ ጮኹ
"ግድግዳ?" አሉ አያትየው ሪዛቸውን እያባበሱ፡፡
"አባባ! ግድግዳው እዚያ ምን ይሰራል?" ሲሉ ሦስቱ ትናንሽ አሣዎች ጠየቁ፡፡

"ግድብ ነው ከአደጋ ይጠብቃል፡፡ አዞዎች፣ ትልልቅ የተራቡ አሣዎችና ሌሎች ሊበሉን የሚፈልጉ እንሰሳዎች እንዳይመጡብን ይከላከልልናል፡፡ ምንም ነገር ሳያስጨንቀን የምንኖረው ግድቡ ስላለ ነው፡፡ ግድቡ ይጠብቀናል፡፡ ምሽጋችን ነው፡፡" አሉ አያትየው፡፡

"አባባ ከግድቡ ባሻገር ምን አለ?" ሲሉ አያታቸውን ጠየቁ፡፡

“ብዙ አደጋዎች አሉ::ከግድቡ ከወጣን በሕይወት ሳንመለስ እንችላለን::” አሉ አያትየው::

ለተወሰነ ጊዜ ሦስቱ ትንንሽ አሣዎች በዚህ ማብራሪያ ረኩ:: ይሁንና ከግድቡ ባሻገር ምን እንዳለ ለማወቅ ያላቸው ፍላጎት ከቀን ወደቀን እየጨመረ መጣ:: በመጨረሻም አንድ ቀን ግድቡን ዘለው አልፈው ምን እንዳለ ለማየት ወሰኑ:: እናም ከግድቡ ራቅ ብለው በፍጥነት በመዋኘት ተንደርድረው ግድቡ አጠገብ ሲደርሱ በጣም ከፍ ብለው ዘለሉና አለፉት::

በመጀመሪያ ያስተዋሉት ነገር የውሃው ከፍታ ዝቅተኛ መሆኑን ነው:: ስለዚህም ዘለው ሲገቡ ወደቁ:: በጣም ከመፍራታቸው የተነሳ ወዲያውኑ ወደነበሩበት ሐይቅ ለመመለስ ፈለጉ:: ነገር ግን እንዴት ለመመለስ እንደሚችሉ ማወቅ አልቻሉም:: ብዙ ጊዜ ደጋግመው ቢዘሉም አልቻሉም:: በመጨረሻም እየዘለሉ የወደቁበት ገላቸው ቆሰለ:: ኃይቁ ማእበላማ ስለሆነ ዘለው በተመለሱ ቁጥር ከድንጋይ ጋር ይጋጩና አፍንጫቸው በአሸዋው ላይ ይተከል ነበር:: በመጨረሻም ውሃ በፍጥነት በማይፈስበት የውሃ ክፍል ደረሱ:: አንድ ለስላሳ ድንጋይ ተደግፈው አረፍ አሉ::

“ሰውነቴ በሙሉ ቆስሏል! አለ አንዱ ትንሽ አሣ::
“እኔማ ከአፍንጫዬ እስከ ጭራዬ ነው የሚያመኝ አለ ሌላው::”

“ከሐይቁ መውጣት አልነበረብንም” አለ ሦስተኛው::

በድንገት አንድ አዞ በአጠገባቸው እየዋኘ አለፈ:: እስከዛሬ አዞ የሚባል አይተው አያውቁም ነበር:: አፉ ውስጥ የሞሉትን ጥርሶች ሲመለከቱ በድንጋጤ “እንደበቅ” ሲሉ ጮኹ:: እንደአጋጣሚ አዞውን ያላየ ሌላ አሳ እየዋኘ አለፈና አዞው አይቶት ፊቱን አዙሮ በአንድ ጉርሻ ዋጠው:: እንደገና የምበላው ነገር ካገኘሁ ብሎ ፊቱን ወደእነሱ አቅጣጫ ሲያዞር ሶስት ትንንሽ አሳዎች ከቋጥኝ በስተጀርባ ተደብቀው አልታዩትም:: አዞውም ተጨማሪ ምግብ ለማግኘት እየዋኘ ጉዞውን ቀጠለ::

“እንዴት አድርጎ አሳውን እንደዋጠ ተመለከታችሁ?” ሲል አንዱ ትንሽ አሳ ወንድሞቹን ጠየቀ::
“አዎን!” ሲል ሁለተኛው መለሰ::

“እኛንም የሚውጠን እንደዚህ ነው” አለ ሶስተኛው:: ሁሉም በድንጋጤ ተርበተበቱ :: ጭራቸውም በፍርሃት ተንቀጠቀጠ:: “ከዚህ ብንጠፋ ይሻላል” አሉ::

ወራጁን ውኃ እየሰነጠቁ ወደላይ መዋኘት ጀመሩ:: በአሸዋው ላይ እየተሳቡ፣ ከድንጋዮቹ ጋር እየታገሉ፣ ባለ በሌለ ጉልበታቸው እየዋኙ ግድቡ ጋ ደረሱ:: ብዙ ታገሉ:: በመጨረሻም ከግድቡ ጫፍ ላይ ዲደርሱ ጭንቅላታቸውን ከውኃው ውጪ ብቅ አድርገው እንደገና በውኃው ተገፍትረው እንዳይወድቁ የግድቡ ድንጋይ ላይ ተጣብቀው ወደውጭ ተመለከቱ:: ግድቡ በጣም ከፍታ ቦታ ላይ ስለነበረ ዘለው ሐይቁ ውስጥ የመግባት ተስፋቸው ተሟጠጠ “በቃ ምሽጋችን ወደሆነው ግድብ ስመመለስ አንችልም” እያሉ ማልቀስ ጀመሩ:: የዚህን ጊዜ አንድ ትልቅ አሳ በአጠገባቸው አለፈ:: ትንንሾቹ አሣዎች ሲያዩት በጣም ከመፍራታቸው የተነሳ ዓይናቸው ተጎልጉሎ ሊወጣ ነበር:: አፉን በኃይል ከፍቶ ወደ እነርሱ እየቀረበ መጣ:: ለማምለጥም ሆነ ለመደበቅ ጊዜ አልነበራቸውም:: በድንጋጤ ሦስቱም የሚችሉትን ያክል ዘለሉ:: ድንጋጤው ከግድቡ በላይ ለመዝለል የሚያስችል ኃይል ሰጥቷቸው ነበርና ሲወድቁ ያረፉት ግድቡን አልፈው በሰላማዊው ሐይቅ ውስጥ ነበር::

“ሁለተኛ ምሽጋችንን ለቀን አንሄድም!” ብለው እያለቀሱ ወደ እናታቸው ተመለሱ::

*መ. ጨዋታ :- “በሬን የሚያንኳኳው ማን ነው?”*

አንድ ልጅ ዓይኑን ይታሰርና ጀርባውን ለተቀሩት ልጆች ይስጥና በወንበር ላይ ይቀመጥ:: አስተማሪው ለሌላ ልጅ ምልክት ሲያሳይ ልጁ ይነሳና ዓይኑን ወደታሰረው ልጅ ሄዶ ልጁ የተቀመጠበትን ወንበር ያንኳኳ:: ዓይኑን የታሰረው ልጅም “በሬን የሚያንኳኳው ማን ነው?” ብሎ ይጠይቅ:: ሌላው ልጅ ድምጹን ለወጥ አድርጎ “እኔ ነኝ” ይበል:: የተቀመጠውም ልጅ ማን እንደሆነ ለማወቅ ይሞክር:: ዓይኑን የታሰው ልጅ ሦስት እድሎች ይሰጡት ከዚያም ሌላ ልጅ ይታሰርና በተመሳሳይ መንገድ ጨዋታው ይቀጥላል::

*ሠ. ስዕል ቁጥር አስራ አራትን ቀለም መቀባት::*

# ትምህርት 15

ይህ ክፍለ-ጊዜ የዚህ መጽሐፍ የመጨረሻ ትምህርት ነው፡፡ እንደምታውቁት በዓመት ውስጥ እያንዳንዱን ትምህርት ቢያንስ ሦስት ጊዜ መድገም ይኖርባችኋል፡፡ ይህም ሕፃናቱ ትምህርቱን በሚገባ እንዲገነዘቡት ይረዳቸዋል፡፡

ሕፃናቱ ባለፉት አራት ክፍለ--ጊዜዎች በቃላቸው ለመያዝ ያጠኑት የነበሩትን ፀሎት በዚህ ክፍለ--ጊዜ መከለስ እንደሚገባዎ ያስታውሱ፡፡

ቀጣዮቹ እንቅስቃሴዎች :-

ሀ. መዝሙሮች:- (ከዚህ ቀደም ካጠኗቸው መዝሙሮች መካከል ጥቂቶቹን ያካቱ )

<u>የባሃኢነት አርዓያ</u>

አብዱልባሃን እወደዋለሁ
አፈቅረዋለሁ፣
እርሱም ይወደኛል
ያፈቅረኛል፣
የባሃኢነትን አርዓያ ያሳያል
በእግዚአብሔር በማመን ፣
ባሃኢ እንደርሱ ይሆናል፡፡
አብዱልባሃን እወደዋለሁ
አፈቅረዋለሁ፣
እርሱም ይወደኛል
ያፈቅረኛል፣
የባሃኢነትን አርዓያ ያሳያል
ሳይቋረጥ ይፀልያል፣
ባሃኢ እንደርሱ ይሆናል
አብዱልባሃን እወደዋለሁ
አፈቅረዋለሁ ፣
እርሱም ይወደኛል
ያፈቅረኛል፡፡
የባሃኢነትን ምሳሌ ያሳያል
የኔ ፈቃድ ይቀራል፣
የእግዚአብሔር ይፈፀማል
ባሃኢ እንደርሱ ይሆናል፡፡

## ለ. ቅዱሳን ጥቅሶችን በቃል መያዝ

አንዳንድ ጊዜ በህይወታችን አስቸጋሪ ነገሮች ያጋጠሙንና ምን ማድረግ እንደሚገባን ግራ ይገባናል፡፡ ፈጣሪ አምላካችን ሁሉን አዋቂ ነው፡፡ አንድ ሰው ሲከፋ ወይም ችግር ሲገጥመው ያውቃል፡፡ ስለሚወደን ሁል ጊዜ እኛን ይንከባከበናል ከአደጋም ይጠብቀናል፡፡ ሁሉን ነገራችንን ለአምላክ አደራ መተውና ችግር ሲገጥመን እንዲረዳን እርሱን መጠየቅ አለብን፡፡ ሁልጊዜ አምላክን ለማስታወስ እንድንችል እንዲረዳን የሚከተለውን የባሃኡላህ ጥቅስ በቃላችን እንያዝ፡፡

**“እምነትህን በእግዚአብሔር ላይ አድርግ፤ ጉዳዮችህንም ለጥበቃ ለእርሱ ስጥ፡፡”24**

እምነት

- ኤድዋርድ ችግር ስለገጠመው ሁንግ ዊይን እርዳታ ለመጠየቅ ሄደ፡፡ ሁንግ ዊይ የሚችለውን ሁሉ እርዳታ እንደሚያደርግለት ኤድዋርድ እርግጠኛ ነበር፡፡ ኤድዋርድ በሁንግ ዊይ ላይ እምነቱን ጣለ፡፡

- አቲኖ የቤቷን ጣራ ለመስራት ፈለገች፡፡ ነገር ግን ለብቻዋ ልትሰራው ስለማትችል እርዳታ ፈለገች፡፡ የአቲኖ ጓደኞች እንደሚያግዟት ነገሯት፡፡ በጓደኞቿ ላይ እምነቷን በመጣል አቲኖ ለስራው የሚያስፈልጉትን እቃዎች ገዛች፡፡

ጉዳዮች

- ዛሬ ጧት አቶ ፖልሰን በመጀመሪያ ወደ ቢሮ፣ ቀጥሎ ወደ ገበያ፣ ከዚያም ወደ አጎታቸው ቤት ይሄዳሉ፡፡ እያንዳንዱ ቦታ ብዙ የሚሰሩት ነገር አለ፡፡ አቶ ፖልሰን ዛሬ ብዙ ጉዳዮች አሉባቸው፡፡
- ሮዝ ወንድሞቿንና እህቶቿን ትንከባከባለች፤ ትምህርት ቤት የተሰጣትን ሥራ ትሰራለች፣ የታመመ ጎረቤቷን ትጠይቃለች፡፡ ሮዜ ጉዳዮቿን ለመፈጸም ስትሯሯጥ ትውላለች፡፡

## ሐ. የዕለቱ ትረካ

አቶ ሲና በጣም የሸመገሉ ሰው ናቸው፡፡ የባሃኢን እምነት ለማስተማር ወደ ሩቅ ቦታዎች ለብዙ ዓመታት ተጉዘዋል፡፡ ዛሬም ሩቅ የሆነ ቦታ የማስተማር ጉዞ ለማድረግ ተነስተዋል፡፡ ሐቢብ የተባለ ልጃቸውም ለመጀመሪያ ጊዜ አብሯቸው ሊጓዝ ተዘጋጅቷል፡፡ ምንም እንኳን እለቱ በጣም ቀዝቃዛና የሚበርድ ቢሆንም አቶ ሲና በቶሎ ጉዟቸውን ለመጀመር ጓጉተዋል፡፡ ስለዚህ በቅሏቸውን አዘጋጅተው ጉዟቸውን ጀመሩ፡፡ የመጀመሪያው ቀን በጣም እስከሚጨልም ድረስ ሲጓዙ ቆይተው አንድ ከተማ ደረሱ፡፡ እዚያም ያገኙትን ምግብ ያለማማረጥና ያለመጸየፍ በልተው አረፍ አሉ፡፡ የከተማው ሰዎች ግን ሊያስተናግዷቸው አልፈቀዱም ነበር፡፡ ስለዚህ በአንድ በረት ውስጥ ማደር ነበረባቸው በረቱ በጣም ከማርጀቱ የተነሳ ብዙ ዝናብ ያንጠባጥብ ነበር፡፡

ለሊቱን እዛው አሳለፈው፡፡ ጠዋት ፀሐይ ስትወጣ በቅሏቸው ላይ ወጥተው ጉዟቸውን ቀጠሉ፡፡ ቀኑን ሙሉ ሳያርፉ ተጓዙ፡፡ ሲመሽ ለማረፊያ ያገኙት ሆቴል ያረጀና ቆሻሻ የሆነ ሆቴል ነበር፡፡ አልጋዎቹ በቁንጫ የተሞሉ ነበሩና እንቅልፍ ሳይወስዳቸው ነጋ፡፡ በዚህ ሁኔታ ለብዙ ቀናት ተጓዙ፡፡

ሐቢብ አባቱን “ታላቁ ወንድሜ ለምን አብሮህ አልሄደም እንዳለ አሁን ገና ገባኝ” አላቸው፡፡ አቶ ሲናም ሳቅ አሉና “አዎን ልጄ፤ በዚህ አከባቢ መጓዝ አንዳንድ ጊዜ አይመችም፡፡” በማለት መለሱለት፡፡ መንገዱ አስቸጋሪ ቢሆንም በመጨረሻ ባሃኢዎች ያሉበት ከተማ ሲደርሱ ታላቅ ደስታ ተሰማቸው፡፡ ባሃኢዎቹም በደስታ ተቀበሏቸው፡፡ አቶ ሲናም ባሃኢዎቹን ማበረታታትና የባሃኦላህን ትምህርቶች የበለጠ እንዲረዱ በማስተማር እዛው ሰነበቱ፡፡

በሌላ ጊዜ ደግሞ አቶ ሲና ከልጃቸው ሐቢብ ጋር የማስተማር ጎዞ ለማድረግ አሰቡና ለሐቢብ እንዲህ አሉት፡፡ **“አንድ ባሃኢ ባልንጀራዬ የሚኖርበት ከተማ ከዚህ አይርቅም፡፡ በመካከላችን ያለው አንድ መንደር ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ባለው ከተማ ማንንም ስለማላውቅ ሳናርፍ ብንሄድ አመሻሹ ላይ ባልንጀራዬ ቤት እንደርሳለን፡፡”**

እናም ጉዟቸውን ቀጠሉ፡፡ ብዙም ሳይሄዱ ዝናብ መዝነብ ጀመረ፡፡ በመካከላቸው ያለውን መንደር ሲያልፉ ዝናቡ በጣም አብስብሷቸው ነበር፡፡ ነገር ግን ሳያቋርጡ ጉዟቸውን ቀጠሉ፡፡ በዝናቡ ምክንያት ወንዝ ሞልቶ ጫካውን ሁሉ አጥለቅልቆት ነበር፡፡ ስለዚህ መንገዳቸውን ለማግኘ ት አልቻሉም፡፡ መምሸት ሲጀምር አቅጣጫቸው ጠፋባቸው፡፡ ይባስ ብሎ አቶ ሲና ታመሙ፡፡ ብዙም ሳይቆዩ ሰውነታቸውን ማንቀሳቀስም ሆነ መናገር አቃታቸው፡፡ ሐቢብም አባቱን ወዳለፉት መንደር ለመመለስ ወሰነ፡፡ ሊያሳርፉቸው የሚችልበት ቢያንስ የከብት በረት አገኛለሁ ሲል አሰበ፡፡

በመጨረሻም በብርድ ሊሞቱ ትንሽ ሲቀራቸው በጭቃ ተጨማልቀው እመንደሩ ደረሱ፡፡ ሰዎቹም በጥሩ ሁኔታ አቀባበል አደረጉላቸው፡፡ ወዲያውኑ ወደ አንደኛቸው ቤት ወሰዷቸው፡፡ የቤቱ ባለቤትም አቶ ሲናን አልጋ ላይ አስተኛቸው፡፡ ብርድ ልብስ አለበሳቸው፡፡ እሳት አሞቃቸው፡፡ የሚችለውን ሁሉ አደረገላቸው፡፡ አንዲት አሮጊት ሴትዮም ከእርሳቸው አጠገብ ቁጭ ብለው አደሩ፡፡ ከማዘናቸው የተነሳ ለቅሶአቸውን ሊያቆሙ አልቻሉም፡፡ ሊነጋጋ ሲል አቶ ሲና እያገገሙ ሄዱና መናገር ጀመሩ፡፡

አቶ ሲና በመጀመሪያ ከአሮጊቷ ሴትዮ ጋር መነጋገር ጀመሩ፡፡ አሮጊቷም ከሦስት ቀናት በፊት አቶ ሲናና ልጃቸውን በሕልማቸው እንዳዩዋቸው ተናገሩ፡፡ በሕልማቸውም ልክ ትላንትና እንደነበሩት ራሳቸውን ስተው ነበር ያዩአቸው፡፡ ስለዚህ ወደመንደሩ መምጣታቸው ልዩ ትርጉም እንዳለው አውቀዋል፡፡

አሮጊቷ ሴትዮም "ወዴት ነበር የምትሄዱት?" ሲሉ አቶ ሲናን ጠየቁ፡፡ "እቶ ሲናም ከዚህ ቀጥሎ ባለው መንደር ውስጥ የሚኖር አንድ ባልንጀራዬን ልንጠይቅ እየሄድን ነበር፡፡" ሲሉ መለሱ፡፡ ከዛም አቶ ሲና በዚያ መንደር ውስጥ ያለው ባልንጀራቸው የእኚህ አሮጊት የልጅ ልጅ እንደሆነና አሮጊቷም ባሃኢ እንደሆኑ ተረዱ፡፡ ይግረማችሁ ብለው የዚያ መንደር ሰዎች በሙሉ ባሃኢዎች እንደሆኑ ነገሯቸው፡፡

የአምላክ ኃይልና መሪነት ታላቅ ነው፡፡ ዝናብ እንዲዘንብና ጫካው በጎርፍ እንዲጥለቀለቅ ያደረገው እርሱ ነው፡፡ አቅጣጫቸውን እንዲስቱ አቶ ሲና እንዲታመሙ ያደረገው በዚያ መንደር ውስጥ ወዳሉት ወንድሞቻቸውና እህቶቻቸው እንዲመሩና በዚያውም የመንደሩን ባሃኢዎች እንዲያነቃቁና እንዲያበረታቱ ነበር፡፡ አምላክ ኃያል እንደሆነና ሰዎችንም እንደሚመራ ማንም ሰው መጠራጠር የለበትም፡፡

*መ. ጨዋታ "የድምጾች ቅንብር"*

*ሁሉም ልጆች ክብ ሰርተው ይቀመጡ፡፡ ረጋ ብለው የሚከተሉትን እንቅስቃሴዎች በተሰጠው ቅደም ተከተል መሰረት ይስሩ፡፡*


- *በእግራቸው መሬቱን ይርገጡ፡፡*
- *በእጃቸው ያጨብጭቡ*
- *ጣታቸውን በማፋጨት ያጩሁ*
- *በዚህ ቅደም ተከተል እንቅስቃሴዎቹን ይደጋግሙ፡፡*

*ሁሉም ሰው እነዚህ እንቅስቃሴዎች በተሰጠው ቅደም ተከተል በሚገባ ማከናወን እንደቻሉ ከሶስተኛው እንቅስቃሴ (ጣታቸውን በማፋጨት ካጮሁ) በኋላ የአንድ ልጅ ስም ይጠራ፡፡ እንደገና ሁሉንም እንቅስቃሴዎች ካደረጉ በኋላ የሌላው ልጅ ስም ይጠራ፡፡ በዚህ መንገድ የሁሉም ልጆች ስም ተጠርቶ እስከሚያልቅ ድረስ ይቀጥል በመጨረሻም ሌሎቹ እንቅስቃሴያቸውን ሲቀጥሉ አንዱ ልጅ የሁሉንም ስም በየተራ ይጥራ፡፡*

*ጨዋታውን በተለየ መንገድ ለማጫወት ፡-*


*የልጆቹን ስም በመጥራት ምትክ የተለያዩ ቅርጾችን፣ ቀለሞችን፣ ቁጥሮችን ወ.ዘ.ተ መጥራት ይቻላል፡፡*

*ሠ. ስዕል ቁጥር አስራ አምስትን ቀለም መቀባት፡፡*




**"So powerful is the light of unity that it can illumine the whole earth."**


“የአንድነት ብርሃን በጣም ኃይል የተመላ ስለሆነ መላውን ምድርን ለማብራት ይችላል።”



“የመንፈስ ልጅ ሆይ! የመጀመሪያ ምክሬ ይህ ነው፡-… ንጹህ፤ ሩኅሩኅና አንጸባራቂ ልብ ይኑርህ።”




"በፍትሕ መንገድ ተራመድ፤ ይህ፤ በእውነቱ ቀጥተኛው መንገድ ነው።"



“…በልብህ አትክልት ሥፍራ ከፍቅር ጽጌረዳ በስተቀር ሌላ አትትክል”



“ዛሬ ስመሳው የሰው ዘር አገልግሎት ራሱን የሚሰጥ ሰዉ በእውነቱ ሰው ነው።”



"እውነተኛነት የሰው መልካም ምግባራት ሁሉ መሠረት ነው።"



“በጌታህ እምነት ጽኑ ሆነህ ከቆየህ፤ ደረጃህ እጅግ በጣም ከፍተኛ ይሆናል።”




“የሰው ልጅ ሆይ! በፀጋዬ እጎበኝህ ዘንድ በፊቴ ራስህን ዝቅ አድርግ።”



“እርሱ ከራሱ በፊት ወንድሙን የሚያስቀድም የተባረከ ነው።”




"ሕዝብ ሆይ፣ አንደበታችሁን በእውነተኛነት አስውቧቸው፤ ነፍሶቻችሁንም በታማኝነት ጌጥ አስጊጧቸው።"




"መስጠትና መቸር የእኔ ባሕሪያት ናቸው፤ በባሕሪያቴ ራሱን ያስጌጠ የበጀው ነው።"




“እርሱ፣ ከሁሉም ሰዎች ጋር በከፍተኛ ደግነትና የፍቅር መንፈስ የሚቀሳቀል የተባረከ ነው።”



“የሕያው ልጅ ሆይ! ፍቅሬ ምሽጌ ነው፤ ወደዚያ የሚገባ ደህንነትና ዋስትና አለው፤ ፊቱን ከዚያ የሚመልስ ግን በእርግጥ ተንከራቶ ይጠፋል።”



“የፍቅር ምልክቱ በትእዛዜ መጽናትና በፈተናዎቼም መታገስ ነው”



“እምነትህን በእግዚአብሔር ላይ አድርግ፤ ጉዳዮችህንም ለጥበቃ ለእርሱ ስጥ።”

# የልጆች ትምህርት ክፍለ-ጊዜን በብቃት መምራት

## ዓላማ

የልጆች ትምህርት ክፍለ-ጊዜን ለማካሄድ የሚያስፈልገንን ችሎታንና ክህሎት ለማዳበር፣ ክፍለ-ጊዜዎቹን ለመምራት (ለማካሄድ) ፍቅርና ግንዛቤ እንዲኖረንና የመማር ማስተማር ሂደቱ ሥነ-ሥርዓትን የጠበቀ ለማድረግ፡፡

## ምዕራፍ 1 - የልጆች ትምህርት ክፍለ--ጊዜዎችን ማካሄድ

የዚህ ክፍል ዓላማ ስለልጆች ትምህርት ክፍለ--ጊዜዎች ምንነት መሠረታዊ ሃሳቦችን ማስጨበጥና ክፍለ--ጊዜዎቹንም በብቃት ለመምራት የሚያስችሉ ጥቂት ዘዴዎችን ለመማር ነው:: ከዚህ ርዕሰ-ምዕ ራፍ በፊት በነበረው ክፍል የሕፃናት ትምህርት የሚያካትታቸውን የትምህርት እንቅስቃሴዎች ተምረ ዋል:: እነዚህም ጥቅሶችንና ፀሎቶችን በቃል ማጥናት፤ መዝሙር፣ ታሪክ፣ ጨዋታና ስዕሎችን ቀለም መቀባት ናቸው:: ለጥረትዎ ስኬታማነት ስለእያንዳንዱ የትምህርት ክፍለ-ጊዜ ይዘት፣ የሚኖርዎት እውቀትና ትምህርቱንም ለመስጠት ያለዎት የዝግጅትና መነሳሳት ወሳኝ ነው:: ይሁንና መልካም ውጤት ለማ ግኘት እውቀትና መነሳሳት በቂ አይደሉም:: የትምህርት ክፍለ ጊዜዎችን የሚመሩበት መንገድና ከሕፃናቱና ከወላጆቻቸው ጋር ሊኖርዎ የሚገባ መልካም ግንኙነት ውጤታማነትዎን አመርቂ ያደርገዋል:: እንዲህ አይነቱ ግንኙነት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ማፍቀርና በጥልቅ ከበሬታ ላይ መመ ስረት እንዳለበት ያውቃሉ:: ስለሆነም በዚህ ምስጉን በሆነ የአገልግሎት መስክ ውጤታማ ለመሆን ስለሚያስችልዎ አንዳ ንድ ዘዴዎች ማሰብ ጠቃሚ ነው::

## ምዕራፍ 2 - ክፍለ ጊዜዎቹን ማቀናጀት

እንደሚያውቁት ልጆች ለትምህርት ሲመጡ ዝም ብለውና ተረጋግተው አይቀመጡም:: የእርስዎም ዓላማ እንዲህ እንዲሆኑ መሆን የለበትም:: አፍላ ጉልበታቸውን በመማር ላይ እንዲያውሉ ዕድሎችን መጠቀም አለብዎ:: ይህንን ለማድረግ በእርጋታ ጊዜ የሚከናወኑ፣ እንዲሁም በፍጥነትና በእንቅስቃሴ ውስጥ እያሉ የሚከናወኑ የትምህርት ዓይነቶችን ማቀድ ያስፈልጋል:: ክፍለ-ጊዜዎችን ከትምህርት እንቅስቃሴዎቹ ጋር ማቀናጀት የትምህርት ዝግጅቱ ዋና ክፍል ነው:: ክፍለ ጊዜው በሚገባ የተቀናጀ ከሆነ ህፃናቱ ትኩረታቸውን ሰጥተው ለመማር ይቀላቸዋል::

የሚከተሉትን ሦስት ነጥቦች ከግምት ውስጥ ቢያስገቡ ስለክፍለ ጊዜዎ ቅንጅት ማሰብ ለመጀመር ይጠቅምዎታል::

- እያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ ግልጽና አንድ ወጥ በሆነ መንገድ ተጀምሮ ስርዓት ባለው መንገድ መጠናቀቅ አለበት::
- የክፍለ ጊዜዎቹ እንቅስቃሴዎች ወጥነትና በእየለቱ መደጋገሙ ልጆቹ የእንቅስቃሴዎቹን ቅደም ተከተል እንዲለምዱት ያስችላቸዋል:: ስለዚህ ሕፃናቱ የቱ እንቅስቃሴ ከየትኛው እንደሚቀጥልና አስተማሪውም ከእነሱ ምን እንደሚጠብቅ አስቀድመው ቀስ በቀስ ማወቅ መቻል አለባቸው::

- ለእያንዳንዱ የትምህርት እንቅስቃሴ የሚመደበው ጊዜ ሊለዋወጥ ይችላል:: ይህም የሚወሰነው በሕፃናቱ መመሰጥና አለመድከም ላይ ነው:: ከሕፃናቱ ጋር የሚከናወኑ

አምስት እንቅስቃሴዎች የሚከተሉት ናቸው:-

- ከባሃኢ ቅዱሳን ጽሑፎች የተገኙ ፀሎቶችንና ጥቅሶችን በቃል መያዝ
- መዘመር
- ታሪክ መተረክ
- መጫወት
- ከመንፈሳዊ ጽንሰ ሐሳቦች ጋር ግንኙነት ያላቸው ስዕሎችን ቀለም መቀባት::

ለእያንዳንዱ የትምህርት እንቅስቃሴ የሚመደበው የጊዜ መጠን የተለያየ ነው። ይኸውም፣ ትምህርቱ በሚጠይቀው የትኩረትና የእንቅስቃሴ መጠን ይወሰናል። አንዳንዶቹ ብዙ እንቅስቃሴን የሚሹ ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ በተረጋጋ ሁኔታ የሚተገበሩ ናቸው።

- ከአምስቱ የትምህርት ክፍሎች መካከል ከፍተኛ እንቅስቃሴ የሚጠይቁ የትኞቹ ናቸው?

____________________________________________

____________________________________________

በተረጋጋ ሁኔታ የሚፈፀሙት የትኞቹ ናቸው? ________________________

____________________________________________

____________________________________________

የትምህርት ክፍለ-ጊዜዎቹ የሚጠይቁትን የትኩረትና የእንቅስቃሴ መጠን ወይንም ጊዜ ማወቅ ክፍለ ጊዜዎን በቅደም ተከተል ለመምራትና ለማቀናጀት ይረዳዎታል። የሚከተለውን የትምህርት ክፍለ ጊዜ ቅደም ተከተል ያንብቡና እንቅስቃሴዎቹ ምክንያታዊ በሆነ ቅደም ተከተል ተቀናጅተው እንደሆነ ይወስኑ።

ልጆቹ ከክፍሉ ውጭ ይሰለፉና በሰልፉ መሰረት ወደ ክፍል ይግቡ። ለጊዜው የተፈጠረውን ስርዓትና መረጋጋት በመጠቀም ትምህርቱን በፀሎት ይጀምራሉ። ከዚያም በቃላቸው የጠኗቸውን ጥቅሶች ይከልሳሉ። አዲስ ጥቅስም ያስጠኗቸዋል። በመቀጠልም መዝሙር ያዘምሯቸዋል። በዚህም መነቃቃትን ከፈጠሩ በኋላ አንድ ታሪክ ይተርኩላቸዋል። ከዚያም በኋላ ወደ ጨዋታ ይሸጋገራሉ። ከጨዋታ ሲመለሱም የስዕል ወረቀቶችን ከሰጧቸው በኋላ ለጥቂት ጊዜ ቀለም እንዲቀቡ ይተዋቸዋል። የትምህርት ክፍለ ጊዜውን ለማጠናቀቅ፤ ሁሉም ሕፃናት በእርጋታ ተቀምጠው ምን እንደተማሩ እንዲያስታውሱ ይረዷቸዋል። ከዚያም የመዝጊያ ፀሎት ይደረጋል።

ከዚህ ቀጥሎ የትምህርት እንቅስቃሴዎቹን በቅደም ተከተል ይደርድሯቸው። ለእያንዳንዱ እንቅስቃሴ የሚያስፈልገውን የጊዜ (ደቂቃና ሰዓት) መጠን ይወስኑ።

| እንቅስቃሴ | ጊዜ |
| --- | --- |
| ________________ | ________________ |
| ________________ | ________________ |
| ________________ | ________________ |
| ________________ | ________________ |

## ምዕራፍ 3 - በትምህርቶቹ ቅደም ተከተል መሠረት ክፍለ-ጊዜውን መጀመር

ሁኔታዎች የሚፈቅዱ ከሆነ፣ ሕፃናቱ ወደ ክፍል ከመግባታቸው በፊት ይሰለፉ:: በዚህ ጊዜ የስም ጥሪ ማድረግ ይቻላል:: እያንዳንዱ ልጅ ስሙ ሲጠራ ከሰልፉ ወጣ ብሎ "እንደምን አደራችሁ!" ካለ በኋላ ተመልሶ ቦታውን ይያዝ:: ከፊት የሚሰለፉና ክፍል ውስጥም ከፊት የሚቀመጡ ልጆች በየክፍለ ጊዜው ይቀያይሩ:: ይህም በየክፍለ-ጊዜ ለሚያሳዩት ጨዋነት ወይም ታታሪነት ሽልማት ሊሆን ይችላል:: ሕፃናቱ ተሰልፈው እያሉ አስተማሪው ስለመልካም ፀባይ አስፈላጊነት ይንገሯቸው:: ለምሳሌ:- "**ልጆች አሁን ወደ ክፍላችን ከገባን በኋላ ፀጥ ብለን እንቀመጥና ጥቂት ፀሎቶችን እናደርጋለን:: ዛሬ በተለይ እርስ በእርሳችን ለመከባበር እንሞክራለን::**" በማለት ሊጀምር ወይም ልትጀምር ትችላለች::

ወደክፍሉ ከገቡ በኋላ ሕፃናቱ ቦርሳ ወይንም ሌሎች ነገሮችን ከያዙ ያስቀምጡና ለመፀለይ ይዘጋጁ:: ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ ትምህርቱ የሚካሄደው በዚህ መልክ መሆኑን ሕፃናቱ ከተረዱ ትምህርቱን ለመጀመርና ስነ-ሥርዓትን ለመጠበቅ ቀላል ይሆናል::

### የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድንዎ ተወያዩባቸው::

1. ልጆቹ መጋፋት፣መጯጯህና ሰልፍን መረበሽ ቢጀምሩ ምን ያደርጋሉ?

ሀ. ______________________________

______________________________

ለ. ______________________________

______________________________

ሐ. ______________________________

______________________________

2. አንድ ልጅ ከሌላው አጠገብ መሰለፍ አልፈልግም ቢል ምን ያደርጋሉ?

ሀ. ______________________________

______________________________

ለ. ______________________________

______________________________

ሐ. ______________________________

______________________________

3. በክፍል ውስጥ ልጆቹ ለመቀመጫ በመሻማት መደባደብ ቢጀምሩ ምን ያደርጋሉ?

ሀ. ______________________________________________

______________________________________________

ለ. ______________________________________________

______________________________________________

ሐ. ______________________________________________

______________________________________________

## ምዕራፍ 4 - የፀሎት ክፍለ-ጊዜ

የየእለቱን የትምህርት ክፍለ ጊዜ በፀሎት መጀመር በጣም አስፈላጊ ነው:: ከሁሉም በፊት በፀሎት አማካኝነት ሕፃናቱ የአምላክን ቡራኬና እርዳታ ያገኛሉ:: አእምሯቸው ይነቃቃል፣ የመረዳትና የማሰብ ችሎታውም ይጨምራል:: ከዚህም ሌላ ፀሎት የአምልኮ መንፈስን ስለሚፈጥር የትምህርቱ ሂደት እንዲሰምር እገዛ ያደርጋል::

አብዱል-ባሃ እንዲህ ይላል:-

> **"በየእለቱ ጠዋት፣ የባሃኢን ሕፃናት በአንድ ላይ በመሰብሰብ የፀሎት ስርዓቶችንና ፀሎቶችን አስተምሯቸው:: ይህ እጅግ በጣም የሚያስመሰግን ተግባር ነው፤ ስልጆቹም ልቦች ሐሴትን ያመጣል፤ እነርሱ ሁልጊዜ ጠዋት ጠዋት ፊቶቻውን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መመለስ፣ የጌታን ስም በማውሳትና ስሙንም በማወደስ፤ በእጅግ በጣም ጥዑም ድምጽ ማዜምና መድገም ይገባቸዋል::"[1]**

በክፍል ውስጥ ፀሎት ሲደረግ ልጆቹ የፀሎት ሥነ-ሥርዓቶችን በሙሉ መጠበቅ አለባቸው:: ይኸውም በፀጥታና በአክብሮት መንፈስ መቀመጥ ይኖርባቸዋል::

አንድ ፀሎት ተደርጎ ሌላ ከመጀመሩ በፊት ሁሉም ሰው ፀጥ እንዳለ ጥቂት ጊዜ ማለፍ ይኖርበታል:: ትንንሽ ልጆች በፀጥታ ለረዥም ጊዜ መቀመጥ አይችሉም:: ስለዚህ በጨኸትና በእንቅስቃሴ መካከል ሁሉም ሕፃናት ፀሎት ከሚያደርጉ ይልቅ መንፈሳዊ ሁኔታው ተጠብቆ ጥቂት ሕፃናት ብቻ ቢፀልዩ ይሻላል:: ለዚህም ፀሎት የሚያደርጉትን ሦስት ወይም አራት ሕፃናት አስቀድሞ መምረጥ ያስፈልጋል:: ፀሎት መፀለይም በአስተማሪው ተጀምሮ የተመረጡት ሕፃናት ቢቀጥሉ ይመከራል::

### የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድንም ይወያዩባቸው::

- የትምህርት ክፍለ ጊዜዎችን በፀሎት መጀመር የሚያስፈልገው ለምንድን ነው?
- ሕፃናቱ በፀሎት የሚያገኙት በረከት ምን ምን ናቸው?
- ሕፃናቱ እንዴት መጸለይ አለባቸው?

- *ለፀሎት በአክብሮት መቀመጥ ምን ማለት ነው? ሊያሳዩ ይችላሉን?*
- *በፀሎት ጊዜ አንድ ልጅ በፀሎታዊ ሁኔታ ውስጥ መሆን ባለመቻሉ ከጓደኛው ጋር ማውራት ይጀምራል:: በዚህ ጊዜ የሚከተሉትን እርምጃዎች ይወሰዱ ይሆናል:: የእያንዳንዱ እርምጃ ውጤት ምን ይሆናል?*

  ⇒ *ፀሎቱን አቋርጦ የሚያወሩትን ህፃናት ዝም እንዲሉ ማስታወስ*

  ⇒ *የሚያወራው ሕፃን ከክፍሉ እንዲወጣ መጠየቅ*

  ⇒ *የሚያወራው ሕፃን ለብዙ ቀናት ፀሎት እንዳያደርግ ማድረግ*

  ⇒ *ሕፃኑን ችላ ብሎ ፀሎቱን መቀጠል*

  ⇒ *ሕፃኑን መስደብ*

- *አንዳንድ ህፃናት በፀሎት ጊዜ የሚረብሹ ጓደኞቻቸውን መስደብ ጀመሩ እንበል:: በዚህ ጊዜ የሚከተሉትን እርምጃዎች ይወሰዱ ይሆናል:: የእያንዳንዱን እርምጃ ጠቀሜታ ያስረዱ?*

  ⇒ *ሕፃናትን የማረም ሃላፊነት የአስተማሪው ብቻ እንደሆነ ማስታወስ*

  ⇒ *ሕፃናቱ እርስ በእርስ እንዲተራረሙ መተው*

  ⇒ *ፀሎቱን አቁሞ ህፃናቱ ፀጥ እንዲሉ ማዘዝ*

  ⇒ *ክፍለ ጊዜው ከመጀመሩ በፊት ምን ማድረግና እንዴት መሆን እንዳለባቸው ማስታወስ::*

  ⇒ *ወሬ የሚያወራውን ህፃን ከክፍል እንዲወጣ ማድረግ::*

# *ምዕራፍ 5 - ሥነ-ሥርዓት*

አብዱል-ባሃ እንዲህ ይላል

> **"ገና ከህፃንነቱ ወቅት/ጊዜ ጀምሮ፣ በሕፃኑ ሕልውና ውስጥ መለኮታዊ የሆነ መሰረት እንዲጣልና የቅድስና መዋቅር ይተከል ዘንድ፣ ትምህርት በተሟላ ሁኔታ መሰጠት ስለሚኖርበት፣ ጠባዩን ለማረቅና ለማነጽ ሁኔታው መመቻቸት ስላለበት፣ የሕፃና ትምህርት ቤት የከፍተኛ ድስፕሊንና የሥነ-ሥርዓት ስፍራ መሆን አለበት::"** [2]

*የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ያቀፈው የትምህርት ክፍለ-ጊዜ ውጤታማ እንዲሆን አስተዋጽኦ ከሚያደርጉ ነገሮች አንዱና ዋንኛው በመልካም ባሕሪ መተነጻቸው ነው :: በማስተማር ጥበብ መካን ማለት እያንዳንዱ ልጅ በደስታ የተሞላ ሆኖ፣ ነገር ግን ስነ-ሥርዓቶችን እንዲጠብቅ የሚያስችል የመማር ማስተማር ሁኔታን ለመፍጠር መቻል ነው:: እንደዚህ ዓይነቱን የማስተማር ጥበብ ለመፍጠር ስለሚያስፈልጉ ብዙ ዝርዝር ነገሮችን ወደፊት ከልምድ ይማራሉ:: ይሁንና የሚከተሉት ሐሳቦች አገልግሎትዎን ለመጀመር በሥርዓት እንዲዘጋጁ ይረዳዎታል::*

ሕፃናት አዲስ ነገርን የማወቅ ተፈጥሮአዊ ፍላጎት አላቸው። ትኩረታቸውን የሚስብ በጣም ከባድ ወይም ቀላል ያልሆነ ነገር ከተሰጣቸው ሳይረብሹ ይሰራሉ።

**ለምሳሌ፡- ከዚህ በታች በተሰጡት ሁኔታዎች ችግሮች እንዳይፈጠሩ አስተማሪው ምን ማድረግ ይችላል?**

- አንድ ልጅ ወይም የተወሰኑ ልጆች አንድን ተግባር አጠናቀው ሌላ የሚሰሩት አልነበራቸውም አስተማሪው ምን ማድረግ ይገባዋል?
- አንድ ልጅ ወይም የተወሰኑ ልጆች ማከናወን የሚገባቸውን ነገር ምን እንደሆነ አልተረዱም ወይም ስራው በጣም ክብዷቸዋል።
- ሥራው ለአንዱ ወይም ለብዙ ልጆች በጣም ቀላል ነው።
- አንድን እንቅስቃሴ ለመጀመር አስተማሪው ልጆቹን ለረዥም ሰዓት ደጅ ያቆያቸዋል።

**ከላይ የተዘረዘሩትን እያንዳንዱን ሁኔታዎች በሚገባ ካጤኑ በኋላ በክፍሉ ውስጥ ረብሻ እንዳይፈጠር የሚረዱ ሐሳቦችን ቀጥለው ይፃፉ፡-**

**1.** ____________________________________________

____________________________________________

____________________________________________

**2.** ____________________________________________

____________________________________________

____________________________________________

**3.** ____________________________________________

____________________________________________

____________________________________________

**4.** ____________________________________________

____________________________________________

____________________________________________

**የመፍትሄ ሐሳቦችን ዘርዝረው ከጻፉ በኋላ በቡድንዎ ውስጥ ይወያዩባቸው።**

ከአንድ እንቅስቃሴ ወደሌላ በሚሸጋገሩ ጊዜ መጯጯህ ሊፈጠር ይችላል። አንዳንድ ልምድ ያላ ቸው አስተማሪዎች መዝሙር ማዘመርን ይመርጣሉ። ሕፃናት እንዲዘምሩ ማድረግ ረብሻ እንዳይፈጠርና ሐሳባቸው እንዳይበታተን ይረዳል። ብዙውን ጊዜ ሕፃናትን የማያስደስቱ እንቅስቃሴዎችን በመዝሙር ለማጣፈጥ ይቻላል። ለምሳሌ ክፍሉን ለማሰናዳትና ለማጽዳት በሚነሱ ጊዜ "**አሁን ክፍሉን የምናፀዳበት ጊዜ ነው።**" እያሉ ማዘመር ይቻላል።

## *ምዕራፍ 6 - ደንቦችና መመሪያዎች*

አብዱል-ባሃ እንዲህ ይላል

> **“የስሕተት መሠረታዊ መንስዔ ድንቁርና ነው፤ ስለዚህም የግንዛቤና የዕውቀትን መሳሪያዎች አጥ ብቀን መያዝ አለብን፡፡ የመልካም ጠባይ ትምህርት መሰጠት አለበት፡፡ ... ሁሉም የመንግስተ ሰማይ የሆኑትን የመንፈስ ጠባዮች ይሳበሱ ዘንድ፤ መጥፎና የማይገባ(ጉድለት) ያለበት ጠባይ ከመያዝ የባሰ ምንም ኃይለኛ ገሃነም፣ ምንም አቃጣይ አዘቅት እንደሌለ፣ መወገዝ የሚገባቸው ባሕሪያት ከማሳየት የባሰ የጨለመ ጥልቅ ጉድጓድ ወይም አስከፊ ስቃይ እንደሌለ ... ያለምንም መጠራጠር ይገነዘቡ ዘንድ፤ ብርሃን በሰፊው መሰራጨት አለበት፡፡”[3]**

*ልጆች ሲያጠፉ መሳደብና የጉልበት ቅጣት ማድረስ በመንፈሳዊ ትምህርት ሥርዓት ውስጥ ቦታ የለውም፡፡ የባሃኣላህ ተከታይ የሆነ ሁሉ መልካም ባሕሪ እንዲያዳብር የሚረዳው ለአምላክ የሚኖረው ፍቅር በመሆኑ የሕፃናት አስተማሪም ለልጆቹ ከመጀመሪያው የትምህርታቸው ቀን ጀምሮ የአምላክን ፍቅር ማስረጽ መጀመር አለበት፡፡ በዚህ ፍቅር ምክንያት ሕፃናት በመንፈሳዊ ሕግጋት መሠረት የመኖር ፍላጎታቸው በየቀኑ ያድጋል፡፡ የባሃኢ ሕይወት ምሉዕ አርኣያ የሆነው የአብዱል-ባሃ ታሪኮች በዚህ መንገድ እንዲመሩ ይረዳቸዋል፡፡*

*ይሁንና ምንም እንኳን በታላቅ ፍቅር ቢንከባከቧቸውም አንዳንድ ጊዜ እንደሚፈለገው ስርዓትን ላይጠብቁ ይችላሉ፡፡ የሚከተሉት ሐሳቦች በክፍል ውስጥ ስነ-ሥርዓትን ለማስጠበቅ ይረዳዎ ይሆናል፡-*

- *መጀመሪያ ጊዜ ትምህርቱን ሲጀምሩ ያሉት ተከታታይ ክፍለ-ጊዜዎች በቀጣይነት ለሚያካሂዱት የትምህርት ወቅት የበለጠ አስፈላጊዎች ናቸው፡፡ በእነዚህ የመጀመሪያ ክፍለ ጊዜዎች ስነ-ስርዓትን ማክበርና እርስ በእርስ የመከባበር ልማድ ከተፈጠረ ዓመቱን ሙሉ ሊቀጥል ይችላል፡፡ ይህንን ልማድ ለማዳበር አስተማሪው እጅግ አስፈላጊ የሆኑትን የስነ-ስርዓት መመሪያዎችን በግልጽ ማስረዳት አለበት፡፡ አስተማሪው እነዚህን መመሪያዎች በሥራ ላይ የሚያውልበት መንገድ ወሳኝ ነው፡፡ አስተማሪው የማያወላውልና የማይለዋወጥ አሰራር የሚከተል፣ በሌላ በኩል ሕፃናቱን የሚወድና ለእነርሱም የሚሳሳ መሆን አለበት፡፡*
- *በመጀመሪያዎቹ ክፍለ ጊዜዎች በጣም ጥቂት ነገር ግን አስፈላጊ የስነ-ስርዓት ደንቦችንና መመሪያዎችን መምረጥ አለበት፡፡ እነዚህንም ደንቦችና መመሪያዎች ሊረዱት በሚችሉት አነጋገር ለሕፃናቱ ይብራሩ፡፡* **“ሕፃናት ሥርዓትን መጠበቅ አለባቸው”** *የሚል በግልጽ ማክበር ያለባቸውን ደንብና መመሪያን የሚገልጽ መመሪያ እንዳያወጡ፡፡ ይልቁንም* **“ሕፃናት መጣላት የለባቸውም ወይም ሕፃናቱ መናገር ሲፈልጉ በየተራ መናገር አለባቸው”** *የሚሉ መመሪያዎች ተጨባጭ ስለሆኑ ለመረዳት ቀላል ይሆናሉ፡፡*

### ከቡድንዎ ጋር ተወያይተው ከዚህ በታች ከተሰጠው ዝርዝር ላይ አራት መመሪያዎችን ይጨምሩ፡፡

ሕፃናቱ

⇒ *መጣላት የለባቸውም*

⇒ በፀጥታ ማዳመጥ አለባቸው

⇒ በጨዋነት ተራቸውን መጠበቅ አለባቸው

⇒ ሥራቸውን ማጠናቀቅ አለባቸው

⇒ ____________________

⇒ ____________________

⇒ ____________________

⇒ ____________________

- ልጆቹ እነዚህን መመሪያዎች መረዳታቸውንና በተግባር ማዋል መጀመራቸውን ካረጋገጠ በኋላ ሌሎች አዳዲስ መመሪያዎችን መጨመር ይችላል፡፡ ይህንንም ሲያደርግ በአንድ ጊዜ ብዙ መመሪያዎችን መጨመር እንደሌለበት ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡ አንድ ልጅ በተደጋጋሚ መመሪያዎቹን ባያከብር አስተማሪው ልጁን ሊያስተካክል የሚችልባቸውን መንገዶች ማሰብ ይኖርበታል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ አስተማሪው ትእግስት የሚያጣው መፍትሄ የሚሆን ነገር ማሰብ ሳይችል ሲቀር ነው፡፡ እስቲ የሚከተሉትን የአብዱል-ባሃን ቃላት እናስታውስ፡፡

> “…እናት ልጅዋ መልካም ተግባር ሰርቶ በአገኘችው ቁጥር ታመስግነው ታጨብ ጭብለትም(ታበረታታውም)፤ ልቡንም ታስደስተው፤ እጅግ በጣም ትንሽም ቢሆን የማያስፈለግ ጠባይ ቢገልጽ (ቢያሳይ)፤ ልጁን ትምከር፤ትቅጣው፤ በምክንያታዊነት ላይ የተመሰረተ ዘዴ ትጠቀም፤ ካስፈለገ ትንሽ የቃል ቅጣትም እንኳ ቢሆን፤ ነገር ግን ቢደበደብና ስድብ ቢወርድበት የልጁ ጠባይ ሙሉ በሙሉ ስለሚበላሽ ልጁን መምታትም ሆነ ማዋረድ አይፈቀድም፡፡”[4]

## ምዕራፍ 7 - ወዳጅነትና ግብረ-ገባዊ አነጋገር

አንድ ሰው ልጆችን ለማነጋገር የሚጠቀምባቸው ቃላት ሰውየው ስለሕፃናቱ ያለውን ስሜት ይገልፃሉ፡፡ የሚከተሉትን ሁለት አነጋገሮች ለምሳሌ እንመልከት፡፡

እለይኒ! አርፈሽ ተቀመጪና ከሌሎቹ ጋር አብረሽ ዘምሪ!

እለይን የኔ ቆንጆ እስቲ ከሌሎቹ ጋር አብረሽ ዘምሪ፡፡

በግልጽ እንደሚታየው ሁለተኛው አነጋገር ለዘብ ያሉ ቃላትን ይዟል፡፡ ይሁንና ቅን የሆነ ፍቅር ሳይሰማን “የኔ ቆንጆ” ልንል እንችላለን፡፡ ወዳጅነት ከሁሉ አስቀድሞ በአስተማሪው ቅንነት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ከዚያም በምንጠቀመው ቃላት፣ በጽሞነዊ በአነጋገር ወይም በማናሳየው እንክብንቤ ሊገለጽ ይችላል፡፡ ከልጆች ጋር ስንነጋገርና ስለ ልጆች ስንናገር የምንጠቀምባቸው ቃላት

ስለእነርሱ ያለንን አመለካከት ይጠቁማሉ፡፡ ለምሳሌ፡- ብዙ ጊዜ ደደብና ባለጌ እየተባለ ለሚሰደብ ልጅ የሚኖርዎ ስሜት ምንድን ነው? ፍቅር ይሰማዎታል? ይወዱታል? ርህራሄ ይሰማዎታል? ስለ ንቁና ተባባሪ ልጅ በሚያስቡ ጊዜ በልብዎ ውስጥ ምን ዓይነት ስሜት ይቀሰቀስቦታል?

**አሁን ደግሞ የሚከተሉትን ቃላት አንብቡና አንድ ባሃኢ አስተማሪ ልጆችን ለማበረታታት ሊጠቀምባቸው የሚገባው ተገቢ ቃላትን አመልክቱ። በተጨማሪ አብዛኛውን ጊዜ የምትሰሙአቸው ቃላቶች የትኞቹን እንደሆኑ አመልክቱ።**

| | | |
|---|---|---|
| ደደብ | ተባባሪ | ንቁ |
| ረባሽ | እራስ ወዳድ | ደስተኛ |
| ዲዳ | ዋጋቢስ | ድንቅ |
| ታዛዥ | ተወዳጅ | አስቀያሚ |
| ጎበዝ | ብልሹ | ጨዋ |
| በጥባጭ | ሴታሴት | |

የባሃኢ ልጆች አስተማሪ ሊሸሻቸው የሚገባ በዓለም ላይ ያሉ ሁለት ተቃራኒ አስተሳሰቦች አሉ። አንዱ ልጆችን ለአስከፊ ቅጣት የሚዳርገውና በግትር ስርዓቶች እንዲሰለጥኑ የሚያስገድደው አሮጌ ባህላዊ አስተሳሰብ ሲሆን፣ ሁለተኛው ይህን ግትር አስተሳሰብ ለመቃወም ቁጥራቸው እየጨመረ የመጣ ሰዎች ልጆችን እንደፈለጋቸው የሚለቁና ፍጹም ነፃነት የሚሰጡ ናቸው። የባሃኢ አስተማሪ ተግባር የሕፃናቱን ባህሪ በፍቅር፣ በትእግስትና በጥበብ ለማነጽ የመጠነኛ ነትን(ልከኝነትን) መንገድ መከተል አለበት።

ልጆች ባሕሪያቸውን እንዲያሻሽሉ አስተማሪው በየክፍለ-ጊዜዎቹ ከሚያስተምሩአቸው ትምህርቶች በተጨማሪ ሊረዷቸው ከሚችሉበት መንግዶች መካከል ጥቂቶቹ እነዚህ ናቸው:-

- **ምክር:-** እርዳታ ለሚያስፈልገው ልጅ አስተማሪው ጊዜ ወስዶ ሊያነጋግረውና ሊመክረው ያስፈልጋል። በእርግጥ በዚህ ጊዜ አስተማሪው በጣም በፍቅር ሊያነጋግረው ይገባል። ይሁንና በሚናገረው ነገር የማያወላውልም መሆን አለበት። ቁጣ ወይም ትእግስት ማጣት ሊታይበት አይገባም።
- **ሙገሳ:-** አስተማሪው የአብዱል-ባሃን ምክር ተከትሎ የሕፃናቱን መልካም ተግባሮች ማሞገስ ከቻለ የአስተማሪው ሙገሳ ያልታከለባቸው ተግባሮችን አስተማሪው እንዳልወደዳቸው ህፃናቱ ያስተውላሉ።
- **ጥፋት ሲፈጽሙ:-** አንድ ልጅ እንዳያደርግ የተመከረውን ነገር ካደረገ አስተማሪው አለመደሰቱን በግልጽ መናገር ይችላል። ይህም በጠንካራ ሆኖም ከበሬታን ባዘለ አነጋገር ሊነገር ይችላል። ፍቅር የተሞላ እንክብካቤን አስተማሪው ላስለመደው ልጅ ይህ በጣም ከፍተኛ ቅጣት ነው።

**ልጆችን በሚመክሩ ጊዜ ልትጠቀሙባቸው ስለሚገቡ ቃላት በቡድንዎ ውስጥ ተወያዩ።**

## ምዕራፍ 8 ሽልማት

የአብዱል-ባሃን ምክር ተግባራዊ ለማድረግ ሕፃናቱን የምናሞግስባቸውን፣ የምናበረታታባቸውንና የምና ስደስትባቸውን መንገዶች ማሰላሰል አለብን። ምሳሌ:-

- ሕፃናት ሁልጊዜ ሥነ-ሥርዓቶችን እንዲያከብሩ መጠበቅ የለብንም። ሥርዓትን በሚጠብቁ ጊዜም አስተማሪው ሊያሞግሳቸውና ሊሸልማቸው ይገባል።

- አንዳንድ ጊዜ ብርቱካንን ወይንም ጣፋጭ ነገሮችን በሽልማት መልክ ሊሰጡ ይችላሉ። በተጨማሪም የሚወዱትን ነገር እንዲያደርጉ መፍቀድ ሽልማት ይሆናል።

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልሱ :-**

⇒ ሕፃናቱ ክፍል ውስጥ ሲረብሹ አስተማሪው ዝም ካለ ምን ሊፈጠር ይችላል?

⇒ ሕፃናቱ ሥርዓትን ሲጠብቁ እንደሚያስደስታት የምትገልጽላቸው አስተማሪ ባለችበት ክፍል ውስጥ ምንን ማስተዋል ይቻላል?

⇒ ሕፃናቱ ሥርዓትን መጠበቅ የማይችሉ ናቸው ብላ ታስብ እንደነበረና አሁን ግን ጨዋ ዎች ሆነው እንዳገኘቻቸው አስተማሪዋ ለሕፃናቱ ብትነግራቸው የሚኖረው ውጤት ምን ይሆናል?

አሁንም ደግሞ ሕፃናቱ ማከናወን የሚወዷቸውንና እንደሽልማት ልንጠቀምባቸው የምንችላቸ ውን ተግባራት ያስቡ፡፡ የሚወዱትን ነገር እንዲያደርጉ በሽልማት መልክ ሲፈቅዱ የሽልማቱንም ምክ ንያት አብረው ቢገልጹ የበለጠ ኃይል ይኖረዋል፡፡ ለምሳሌ **"ጀሚላ ለክፍል ጓደኞቿ ትሁት ስለሆነች ዛሬ የስዕል ወረቀቱን ለሁላችሁም ታድላለች፡፡"** ማለት ያለንምንም ማብራሪያ ወረቀቱን እንድታድል ከመፍቀድ የተሻለ ኃይል ይኖረዋል፡፡

**እንደሽልማት ልንጠቀምባቸው ከምንችላቸው ተግባራት ጥቂቶቹን ይዘርዝሩ፡-**

⇒ ከአስተማሪው ጎን መቀመጥ

⇒ ጨዋታ መምረጥ

⇒ ____________________

⇒ ____________________

⇒ ____________________

## ምዕራፍ 9 - ቅጣት

አንዳንድ ጊዜ አስተማሪው ጠንከር ያሉ እርምጃዎችን መውሰድ አለበት፡፡ የዚህን ጊዜ እንደአስፈላጊነቱ ሕፃናቱን በግልጽ ሊቀጣ ይችላል፡፡ እንደምሳሌ ሊወሰዱ ከሚችሉ ቅጣቶች መካከል ያጣፋውን ልጅ ስዕል ቀለም እንዳይቀባ ማቀብ፣ ለተወሰነ ጊዜ በጨዋታ ውስጥ እንዳይሳተፍ መከልከል እና ሌሎችም ተመሳሳይ ቅጣቶች ያስፈልጋሉ፡፡ እነዚህን ቅጣቶች ሲተገብሩ ሦስት መሠረታዊ ሃሳቦችን ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡ በመጀመሪያ የቅጣቱን ምክንያት በግልጽ ማስረዳት አለብዎት፡፡ ለምሳሌ፡- **"እንዲህ እንዲህ ዓይነት ጥፋቶችን በመፈጸምህ ጨዋታ ውስጥ ከመሳተፍህ በፊት አምስት ደቂቃ መጠበቅ አለብህ"** መባል አለበት፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የሚቀጧቸው ጥፋቱ እንደተደረገ ወዲያውኑ መሆን አለበት፡፡ ምክንያቱም ሕፃኑ ያደረገውን ጥፋት በቶሎ ሊረሳ ስለሚችል ነው፡፡ በመጨረሻም ቅጣቱ መጠነኛና ምክንያታዊ መሆን አለበት፡፡ ለምሳሌ በቅጣት ስም አንድ ልጅ ሳምንቱን ሙሉ በጨዋታ እንዳይሳተፍ መከልከል አግባብነት የለውም፡፡

**በመቀጠል በሦስተኛው መሰረታዊ ሐሳብ ላይ በቡድንም ውስጥ ይወያዩ፡፡ ተገቢ የሆኑ ቅጣቶችና ለባሃኢ ትምህርት ክፍለ-ጊዜ ተገቢ ያልሆኑ ቅጣቶችን ዝርዝር በየተራ ያስፍሩ ፡-**

ተገቢ ቅጣቶች

⇒ ________________________________________

________________________________________

⇒ ________________________________________________

________________________________________________

ተገቢ ያልሆኑ ቅጣቶች

⇒ ________________________________________________

________________________________________________

⇒ ________________________________________________

________________________________________________

## ምዕራፍ 10 ትብብር (ስዕሎችን ቀለም በመቀባት ክፍለ- ጊዜ)

ስዕሎችን ቀለም የመቀባት ክፍለ-ጊዜ በባሃኢ የሕፃናት ትምህርት የታነጹ ልጆች ከሌሎች ልዩ የሚያደርጋቸውን መንፈሳዊ ባህሪያትን ለማንጸባረቅ እድል ይሰጧቸዋል። በዚህ ክፍለ-ጊዜ በተለይ ትእግስትን፣ ሥርዓትን፣ መተባበርንና መካፈልን ለማዳበር መጠቀም ይቻላል። ሕፃናቱ ቀለም የመቀባት ከፍተኛ ፍላጎት ስለሚያሳዩ አስተማሪው ክፍለ-ጊዜውን በሚገባ መምራት ካልቻሉ ግርግር ሊፈጠር ይችላል።

በዚህ ክፍለ-ጊዜ አስተማሪዋ ሕፃናቱ ቀለም ለመቀባት የሚያመቻቸውን ሁኔታ በማመቻቸት ልትረዳቸው ያስፈልጋል። በቅድሚያ ታጋሽ፣ ተባባሪና ጨዋ ለሆኑ ልጆች ቦታ ትስጥ። የሚጋፉ፣ የሚጮሁና የሚጨቃጨቁ ሕፃናት ካሉ ተራቸውን ይጠብቁ። ሆኖም በሚቀጥለው ክፍለ-ጊዜ እነዚህ ሕፃ ናት ትእግስትን ካሳዩ አስተማሪዋ ይህንን እድል ተጠቅማ ለመልካም ባህሪያቸው እንደሽልማት እዲ ሰማቸው በቅድሚያ ቦታ ትሰጣቸው።

የቀለም እርሳሶችን በምታከፋፍል ጊዜ እነዚሁኑ መመሪያዎችን መከተል አለበት። በመጀመሪያ ሕፃናቱ የሚያስፈልጉአቸውን የቀለም እርሳሶች አስተማሪዋ ከያዘችው የቀለም እርሳሶች መያዣ ውስጥ መምረጥ ይችላሉ። ቀለም መቀየር ሲፈልጉ ይጠቀሙበት የነበረውን ቀለም መልሰው በምትኩ ሌላ ሊወስዱ ይችላሉ። ስለዚህ ሕፃናቱ ቀስ በቀስ የሚጠቀሙበትን ቀለም ብቻ መያዝ ይለምዳሉ። ከብዙ ክፍለ-ጊዜዎች በኋላ ሕፃናቱ የበለጠ ስነ-ሥርዓትን መጠበቅ ሲያዳብሩ ቀለሞቹን አንድ ማዕከላዊ ቦታ ላይ ማስቀመጥ ይቻላል። ሕፃናቱ የሚጠቀሙበትን አንድ ቀለም ብቻ መያዝን ልማድ ካደረጉ የተሻለ ሥርዓትንና የትብብር ስሜትን አዳብረዋል ማለት ነው። ነገር ግን ከአንድ በላይ ቀለሞችን በመያዝ ለእራሳቸው ጥቅም ብቻ ማስቀመጥ ከጀመሩ አስተማሪው እንደገና ቀለሞቹን ማከፋፈል መጀመር አለበት።

## ጥያቄዎች

- ቀለም በመቀባት ጊዜ ሕፃናት ሊያዳብሩ የሚችሏቸውን አራት መንፈሳዊ ባህሪያትን ይዘርዝሩ

________________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

- በመጀመሪያው ክፍለ-ጊዜ ቀለሞችን ማከፋፈል ያለበት ማን ነው? ለምን?

- ሕፃናቱ ስነ-ስርዓትን በመጠበቅና በመተግበር እድገት ማሳየት አለማሳየታቸውን አስተማሪው እንዴት ሊያውቅ ይችላል?

## ምዕራፍ 11- መልመጃዎች (ስለ ሥነ-ሥርዓትና ባሕሪ)

ይህ ምዕራፍ ከሥነ-ሥርዓትና ባህሪ ጋር የተያያዙ ብዙ ጥያቄዎችና መልመጃዎችን ይዟል:: በእነዚህ መልመጃዎች ላይ በጥልቀት ማሰብና በእያንዳንዱም ላይ ከአስጠኚዎና ከቡድንዎ ጋር መወያየት አለ ብዎ::

1. **ሁል-ጊዜ ኩማርና ሳንጄይ የሚሰጣቸውን ትምህርት በአጭር ጊዜ ውስጥ ወዲያው ይረዱና ሌሎች እየተማሩ ሳለ እነሱ መጫወት ይጀምራሉ::** ይህ የሚያሳየው:-

    ሀ. እነዚህ ልጆች በጣም ረባሾች እንደሆኑ ነው
    ለ. እንደደከማቸው ነው
    ሐ. ትምህርቱ በጣም ከባድ ስለሆነ ነው
    መ. ትምህርቱ ቀላልና አጭር በመሆኑ ሰልችቷቸው ነው
    ሠ. አስተማሪው ደክሞታል ማለት ነው

2. **ጊታ ለጥያቄዎች መልስ አትሰጥም፣ በሃሳብም የተዋጠች ትመስላለች:: ይህ ማለት:-**

    ሀ. ጊታን በጣም ጥሩ ልጅ ናት ማለት ነው
    ለ. ድክሟት ሊሆኑ ይችላል ማለት ነው
    ሐ. ትምህርቱ በጣም ከብዷታል ማለት ነወ
    መ. በቃል ማጥናት አትወድም ማለት ነው
    ረ. አሟት ሊሆን ይችላል ማለት ነው

3. **ትምህርቱ ከተጀመረ ከአምስት ደቂቃ በኋላ ሕፃናቱ መቅበጥበጥ ጀመሩ፣ ትኩረታቸው ወደ ትምህርቱ ሊሆን አልቻለም:: ይህ የሚያመለክተው:-**

    ሀ. ሕፃናቱ መጥፎ ፀባይ እንዳላቸው ነው
    ለ. እንደደከማቸው ነው
    ሐ. የቃል ጥናት እንደማይወዱ ነው
    መ. ትምህርቱ በጣም ቀላል በመሆኑ ነው
    ሠ. አስተማሪዋ የምታስተምረው በስሜትና በፍላጎት አለመሆኑን ነው

4. ሁንግ ዌይ ለአስራ አምስት ደቂቃ በሚገባ ትምህርቱን ይከታተል ነበር፣ ከዚያ በኋላ ግን ሚንግ ሊንግን ማስቸገር ጀመረ:: ይህ የሚያመለክተው:-

ሀ. ሁንግ ዌይ ሁልጊዜ ልጆቹን እንደሚያስቸግር ነው
ለ. ሁንግ ዌይ በጣም ቁንጥንጥ እንደሆነ ነው
ሐ. እንደደከመው ነው
መ. አስተማሪውን እንደማይወድ ነው
ሠ. ትምህርቱን እንዳልወደደው ነው
ረ. በአንድ ተግባር ላይ ለረዥም ጊዜ ማተኮር እንደማይችል ነው

5. ከላይ የተጠቀሱትን አራት ችግሮች ለመፍታት ምን ዓይነት መፍትሄ ይሰጣሉ?

ለ1ኛው ሁኔታ:-

______________________________________________
______________________________________________
______________________________________________

ለ2ኛው ሁኔታ:-

______________________________________________
______________________________________________
______________________________________________

ለ3ኛው ሁኔታ

______________________________________________
______________________________________________
______________________________________________

ለ4ኛው ሁኔታ

______________________________________________
______________________________________________
______________________________________________

6. አንድ ልጅ ሌላውን የሚያስቸግርበት ምክንያት ረባሽ ስለሆነ ይሁን ወይም ስለደከመው እንዴት መለየት ይችላሉ?

______________________________________________
______________________________________________
______________________________________________

7. አንድ ልጅ ደክሞት ይሁን ወይስ ትምህርቱ በጣም ከብዶት መሆኑን በምን ማወቅ ይች ላሉ፡፡

________________________________________

________________________________________

________________________________________

**8. አስተማሪዋ ትእግስቷን ጨረሰችና በልጆቹ ተናደደች፡፡ ይህ የሚያመለክተው፡-**

ሀ. ሕፃናቱ አናዳጆች መሆናቸውን ነው
ለ. አስተማሪዋ ትእግስተኛ አለመሆኗን ነው
ሐ. አስተማሪዋ ሕፃናቱን አለመረዷቷን ነው
መ. አስተማሪዋ እንደደከማት ነው
ሠ. አስተማሪዋ ለማስተማር ከመምጣቷ በፊት አለመዘጋጀቷን ነው
ረ. ተማሪዎቹ መረበሽ አምሯቸዋል ማለት ነው
ሰ. አስተማሪዋ ሕፃናትን ማስተማር ማቆም አለባት ማለት ነው
ሸ. ልጆቻቸውን እንዲቀጡ አስተማሪዋ ለወላጆቻቸው መንገር አለባት ማለት ነው

**9. አስተማሪዋ በልጆቹ ላለመናደድ ምን ማድረግ አለባት?**

ሀ. ማስተማሩን ማቆም
ለ. ጨዋ ተማሪዎችን ብቻ መቀበል
ሐ. ትምህርቱ ከመጀመሩ በፊት መጸለይ
መ. የሕፃናቱን ባሕሪ ለመረዳት መሞከር

**10. ትምህርቱ እንደተጀመረ ሳቺኮ ማልቀስ፣ መጋፋትና ቅድሚያ ካላገኘሁ ማለት ጀመረች፡፡ ይህ የሚያመለክተው ሳቺኮ የ________________ ባህሪ እንዳላት ነው፡፡**

ሀ. ትእግስት
ለ. የመሪነት
ሐ. እራስ ወዳድነት
መ. መተባበር

**ለመልስዎ ምክንያት ይስጡ፡-**

________________________________________

________________________________________

________________________________________

**11. ሳቺኮ ላሳየችው ባሕሪ አስተማሪው መስጠት የሚገባው ምላሽ**

ሀ. ዝም እንድትል የፈለገችውን ቅድሚያ መስጠት
ለ. በአንዱ ጨዋታ እንዳትካፈል መከልከልና በሚቀጥለው ጨዋታ ለመካፈል መጮህና መጋፋት ማቆም እንዳለባት መንገር፡፡
ሐ. ታጋሽ የሆነ ልጅ መርጦ "**ቶቶ ታጋሽ ስለሆነ ቅድሚያ ይሰጠዋል**" ማለትና ራሔልም ረጋ እያለች ከሄደች ሦስተኛ ወይም አራተኛ እንደምትሆን መንገር፡፡

መ. ዝም እንድትል ከተነገራት በኋላ አንደኛ እንድትሆን መፍቀድ

**መልስዎን ያብራሩ**

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

**12. ልጆቹ ስዕሎቹን ቀለም በሚቀቡበት ጊዜ አስተማሪው ምን ማድረግ አለበት?**

ሀ. አስተማሪዋ አንድ ቦታ በመቀመጥ ልጆቹ የቀቡትን ስዕል ሊያሳይዋት ወይም የቀለም እርሳስ ለመቀይር ሲፈልጉ ብቻ ወደ እርሷ እንዲመጡ ማዘዝ፡፡

ለ. አስተማሪዋ የቀለም እርሳሶችን ለማከፋፈልና የሚያስፈጋቸውን ነገር ለማሟላት በተማሪዎቹ መካከል መዘዋወር

ሐ. አስተማሪዋ ተማሪዎቹ ስዕሎቹን ቀለም መቀባት እንዲጀምሩ ካደረገች በኋላ ከክፍሉ ወጥታ ከጓደ ኞቿ ጋር ማውራት፡፡

**13. አስተማሪዋ የቀለም እርሳሶችን በጠረጴዛው ላይ ስታስቀምጥ አንዳንዶቹ ልጆች ለጊዜው የሚያስ ፈልጋቸውን ቀለም ብቻ በመያዝ ሲተባበሩና ሲያካፍሉ ሌሎቹ ግን ከአንድ በላይ ወስደው ለእራሳቸው ጥቅም ብቻ ሊያውሉ ይፈልጋሉ፡፡ የዚህን ጊዜ አስተማሪዋ ምን ማድ ረግ አለባት?**

ሀ. ከሌሎች ጋር መተባበርና መካፈልን ያዳበረች አንዲት ልጅን መርጣ ሁሉንም የቀለም እርሳሶች ለኧሳ ሰጥታት እንድታከፋፍል ማድረግ

ለ. የያዙትን ትርፍ የቀለም እርሳሶች ሁሉ በመሰብሰብ ለእያንዳንዱ ልጅ አንድ አንድ ብቻ መስ ጠትና ራስ ወዳድ የሆኑትን ልጆች ለጥቂት ደቂቃዎች ቀለም እንዳይቀቡ የስዕል ወረቀቶቹን መቀማት

ሐ. የቀለም እርሳሶቹንና የስዕል ወረቀቶቹን መሰብሰብና የስዕል ክፍለ-ጊዜውን ማለፍ ፡፡

መ. አንዳንዶቹ ልጆች ከሚገባቸው በላይ ብዙ የቀለም እርሳሶችን በመውሰዳቸው እርሳስ ስላለቀ ያል ወሰዱ ልጆች የሚጠቀሙበት ተጨማሪ ማምጣት፡፡

ሠ. ለጊዜው የማይጠቀሙበትን የቀለም እርሳሶች ሁሉ በጠረጴዛው ላይ እንዲያስቀምጡ ሁሉንም ልጆች መጠየቅ፡፡

**የመረጡትን መልስ በይበልጥ ያብራሩ፡-**

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

## ምዕራፍ 12- የተማሪዎች የመማር እንቅስቃሴና እድገት መቆጣጠሪያ ቅጽ

የልጆች ትምህርት ክፍለ ጊዜ ውጤታማነት የሚወሰነው በአስተማሪው ባሕሪና የክፍለ-ጊዜዎቹ እንቅስቃሴዎች በሚከናወንባቸው አመርቂነት ነው፡፡ ይሁንና አስተማሪው ክፍለ ጊዜውን የሚያቀናጅበትና የልጆቹን እድገት የሚከታተልበት ስልት ሊኖረው ይገባል፡፡ ከሚያስፈልጉት ስልቶች መካከል አንዱ ቀጥሎ የምንመለከተው የተማሪዎች የመማር እንቅስቃሴና እድገት መቆጣጠሪያ ቅጽ ነው፡፡

### ከዚህ በመቀጠል የቅጹን ዓላማና አጠቃቅም የሚገልጽ ምሳሌ ቀርቦሎታል፡-

በሃይ ፓስቸርስ ማህበረሰብ ውስጥ የምትኖር አንጄላ የምትባል ወጣት ሴት ሕፃናትን የማስተማር ፍላጎት አላት፡፡ ማህበረሰቡን በፍቅርና በአንድነት የተሞላ ገነት ለማድረግ የሕፃናቱን መንፈሳዊ ባህሪያት ለማዳ በር ትፈልጋለች፡፡ አንጄላ ለማህበረሰቡ በሙሉ በየሳምንቱ እሁድ የሕፃናት ትምህርት ለማካሄድ እንደምት ጀምርም ገለጸች፡፡ የማሕበረሰቧን ልጆች ማስተምር ስትጀምር እያንዳንዱ ልጅ የተዘጋጁትን ትምህርቶች በሙሉ መማር እንዳለበት ተሰማት፤ በተጨማሪም አንዳንዶቹ ልጆች ከሌሎቹ በተሻለ ፍጥነት የመረዳት ችሎታ እንዳላቸውም ታውቃለች፡፡ ስለዚህ የእያንዳንዱን ልጅ እድገት ለመከታተል እንዲያስችላት የእያንዳንዱን ልጅ ሁኔታ መመዝገብ አለብኝ ስትል ወሰነች፡፡

ከጥቂት ወራት በኋላ ፋጤ የሚከተለውን በመዝገቧ አስፍራ ነበር፡፡

*መስከረም 1 ቀን የሚከተሉት ልጆች ትምህርቱን ለመከታተል ተመዘገቡ፡፡*

| | |
|---|---|
| **ጁዲ** - እድሜ 5 | **ኢንስ** -እድሜ 5 |
| **ፍራንክሊን** -- እድሜ 5 | **ማይክል** - እድሜ 5 |
| **ሞውሪስ** - እድሜ 6 | **ኦርሊን**- እድሜ 5 |
| **ማርታ**- እድሜ 6 | **አሌክሳንደር** -እድሜ 6 |
| **ሉሲ** - እድሜ 6 | **ጆይ** - እድሜ 5 |
| **ማርሴላ** - እድሜ 6 | **ኢሌይን**- እድሜ 5 |
| **ፖውላ** - እድሜ 6 | **አንድሬ**- እድሜ 6 |

ልጆቹን የተማሪዎች የመማር እንቅስቃሴና እድገት መቆጣጠሪያ ቅጽ ላይ መዘገበች፡፡
(የመመዝገቢያውን ቅጽ ናሙና ከዚህ ምዕራፍ በስተመጨረሻ ላይ መመልከት ይችላሉ)

አንጄላ የመጀመሪያውን ክፍለ-ጊዜ **በመስከረም 6** ቀን ጀመረች፡፡ ጁዲ፣ፍራንክሊን፣ማርታ፣ሉሲ፣ማርሴላ፣ማይክል፣ኦርሊን፣ኢሌይን እና አንድሬ የመጀመሪያውን ጥቅስ በቃላቸው በመያዛቸው ተደሰተች፡፡ ያለምንም እርዳታ ጥቅሶቹን በቃላቸው ከያዙት ልጆች ስም ፊት ለፊት ቀኑን ፃፈች፡፡
(ይህንን መረጃ በስተመጨረሻ ባለው መመዝገቢያ ቅጽ ላይ ማየት ትችላላችሁ)

ሁለተኛው የትምህርት ክፍለ-ጊዜ የተካሄደው በሳምንቱ **መስከረም 13** ቀን ሲሆን በቃል የሚጠናው ጥቅስም ከመጀመሪያው ከበድ ያለ ነበር፡፡ ስለዚህ ፍራንክሊን፣ማርሴላ፣ኢሌይን እና

አንድሬ ብቻ ሁለተኛውን ጥቅስ በቃላቸው ለመያዝ ቻሉ፡፡ ከእነሱ በተጨማሪ ሞውሪስ፣ፖውል እና አሌክሳንደር የመጀመሪያውን ጥቅስ በቃላቸው አጠናቀው ያዙ፡፡

ሦስተኛውን ክፍለ-ጊዜ ያካሄደችው **በመስከረም 20** ቀን ሲሆን በዚህ ክፍለ-ጊዜ አዲስ ጥቅስ ከማስጠናት ይልቅ ባለፉት ክፍለ-ጊዜዎች የተማሯቸውን ሁለት ጥቅሶች ለመከለስ ወሰነች፡፡ በክለሳውም ጆይ የመጀመሪያውን ጥቅስ አጠናቆ በቃሉ ሲይዝ ጁዲ፣ ሞውሪስ፣ ሉሲ፣ ማርታ፣ ፖውላ፣ ማይክል እና አሌክሳንደር ሁለተኛውን ጥቅስ በሚገባ አጠናቀቁ፡፡

**መስከረም 27** አንጄላ በተካሄደው አራተኛ ክፍለ-ጊዜ ሶስተኛውን ጥቅስ ማስተማር ጀመረች፡፡ በዚህ ክፍለ ጊዜ መጨረሻ ፍራንክሊን፣ ሞውሪስ፣ ሉሲ፣ ማርሴላ፣ ፖውላ እና

ኢሌይን ሶስተኛውን ጥቅስ በቃላቸው ያዙ። ኢንስ ደግሞ የመጀመሪያውን ጥቅስ አጠናቀቀች። አንጄላ ኢንስ በእናቷ እርዳታ የመጀመሪያውን ጥቅስ በመያዟ በጣም በመደሰት ቀኑን በቅጹ ላይ በታላቅ እርካታ ጻፈች።

በተማሪዎቹ የእድገት ሂደት መመዝገቢያ ቅጽ ውስጥ ያሉ ሰንጠረዦች እየሞሉ በመሄዳቸው አንጄላ ለማስተማር የበለጠ ጉጉት እያደረባት መጣ። አንድ ቀን ጎረቤቶቿ በሕፃናቱ ላይ ለውጥ አየን ሲሉ አስተያየት ሰጡ። አንጄላም በምታካሂደው የሕፃናት ትምህርት በጣም ተደስተው ነበር። ይህንን ስትሰማ አንጄላ የበለጠ ለመስራት ተነቃቃች። የሕፃናቱንም ትምህርት በታላቅ ፍቅርና ጽናት በመቀጠል ከዚህ የሚከተሉትን ውጤቶች አገኘች።

### የጥቅምት 4 ውጤት

ሦስተኛውን ጥቅስ የያዙ፡- ጁዲ፣ ማርታ፣ ኦርሊን፣ አሌክሳንደርና ጆይ ሲሆኑ
4ኛውን ጥቅስ የያዙ፡- ፍራንክሊን፣ ሉሲ፣ ፖውላ፣ አንድሬ፣ ኢሌይን፣ ማርሴላ፣ ሞወውሪስና ማይክል ነበሩ።

### ጥቅምት 18 ውጤት

5ኛውን ጥቅስ የያዙ፡- ጁዲ፣ ማርታ፣ ሉሲና አሌክሳንደ።
(ማስታወሻ፡- አብዛኞቹ ልጆች ጉንፋን ይዟቸው ስለነበር አልመጡም)

### የጥቅምት 24 ውጤት

5ኛውን ጥቅስ የያዙ፡- ፍራንክሊን፣ አንድሬ ፣ ኢንስና ኦርሊን።
(ማስታወሻ፡- አብዛኞቹ ልጆች አሁንም አልተሻላቸውም ነበር)

### የኅዳር 1 ውጤት

አንጄላ ጥቅሶቹን በቃል ለማጥናት ለተቸገሩት ልጆች ልዩ እርዳታ በማድረጓ ፋጡማና ሐሰን 3ኛውን ጥቅስ ከዲጃ ደግሞ 4ኛውን ጥቅስ በቃላቸው ያዙ።

### የኅዳር 8 ውጤት

6ኛውን ጥቅስ የያዙ፡- ሞውሪስ፣ ሉሲ፣ አንድሬ፣ ኢንስ፣ ማይክል፣ ኦርሊንና ጆይ ነበሩ።

## አሁን የምዝገባ ቅጹን በመመልከት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልሱ።

- ስድስት ጥቅሶችን በቃላቸው ያጠኑ ልጆች ስንት ናቸው?

________________________________________

- አራተኛውን ጥቅስ አጠናቀው ያላጠኑ ልጆች ስንት ናቸው?

________________________________________

- ጆይ ያጠናቸው ስንት ጥቅሶችን ነው?

________________________________________

- በሚቀጥለው ክፍለ-ጊዜ (እሁድ) የበለጠ እንዲራመዱ አልማዝ መርዳት ያለባት ልጆች እነማን ናቸው?

___

- ማርታ አጥንታ ማጠናቀቅ የሚገባት የትኞቹን ጥቅሶች ነው?

___

- አንድሬ አጥንቶ ማጠናቀቅ የሚገባው የትኞቹን ጥቅሶች ነው?

___

- ጆይን ሊረዱባቸው የሚችሉባቸውን ሦስት መንገዶች ይጻፉ

___

___

___

- በሚቀጥለው ክፍለ-ጊዜ አንጄላ ምን ማስተማር አለባት፡፡

___

___

- ቅጹን በመመርመር በጥቅምት 4 ከተካሄደው ክፍለ ጊዜ በኋላ አንጄላ የተለየ ነገር ማድረግ ነበረባት ብለው ያስባሉን?

___

___

## የእድገት ሂደት መመዝገቢያ ቅጽ(ናሙና)

| ስም<br>ዕድ | ዕድሜ<br>ጥቅ | ጥቅስ<br>1 | ጥቅስ<br>2 | ጥቅስ<br>3 | ጥቅስ<br>4 | ጥቅስ<br>5 | ጥቅስ<br>6 | ጥቅስ<br>7 | ጥቅስ<br>8 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ጁዲ | 5 | መ6 | መ 20 | ጥ4 | | ጥ 18 | | | |
| ፍራንክሊን | 5 | መ 6 | መ 13 | መ27 | ጥ4 | ጥ 24 | | | |
| ሞውሪስ | 6 | መ13 | መ 20 | መ27 | ጥ 4 | | ሀ 8 | | |
| ማርታ | 6 | መ 6 | መ20 | ጥ4 | | ጥ 18 | | | |
| ሉሲ | 6 | መ 6 | መ 20 | መ27 | ጥ 4 | ጥ 18 | ሀ 8 | | |
| ማርሴላ | 6 | መ 6 | መ 13 | መ27 | ጥ 4 | | | | |
| ፖውላ | 6 | መ13 | መ 20 | መ27 | ጥ 4 | | | | |
| ኢንስ | 5 | መ27 | | ሀ1 | | ጥ 24 | ሀ 8 | | |
| ማይክል | 5 | መ 6 | መ 20 | | ጥ 4 | | ሀ 8 | | |
| ኦርሊን | 5 | መ 6 | | ጥ4 | | ጥ24 | ሀ 8 | | |
| አሌክሳንደር | 6 | መ13 | መ 20 | ጥ4 | ሀ1 | ጥ 18 | | | |
| ጆይ | 5 | መ20 | | ጥ4 | | | ሀ 8 | | |
| ኢሌይን | 5 | መ 6 | መ 13 | መ27 | ጥ4 | | | | |
| አንድሬ | 6 | መ 6 | መ 13 | ሀ1 | ጥ4 | ጥ24 | ሀ 8 | | |

**እርስዎም የሕፃናት ትምህርት ማካሄድ ሲጀምሩ ተማሪዎች የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ ለመመዝገብ በገጽ 104 ላይ የሚገኘውን የመመዝገቢያ ቅጽ መጠቀም ይችላሉ።**

# የእድገት ሂደት መመዝገቢያ ቅጽ

| ስም | ዕድሜ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |

## ምዕራፍ 13 ቤተሰብና አስተማሪ

ጥሩ የልጆች የትምህርት ክፍለ-ጊዜን በብቃት የሚካሄድበትን ስልትና ዘዴ ከማወቅም በተጨማሪ ከቤተሰቦቻቸው ጋር የወዳጅነት ግንኙነት መመስረት ያስፈልግዎታል፡፡ ልጆች በእያንዳንዱ የሕይወታቸው ደቂቃ ሁሉ አዳዲስ ነገሮችን እንደሚማሩ ሁላችንም እናውቃለን፡፡ ወደ ትምህርት ቤት መሄጃ እድሜ ላይ ከመድረሳቸው በፊት እንኳን ሕፃናት ብዙ ነገሮችን ይማራሉ፡፡ መናገርና መራመድ ይችላሉ፡፡ ቤታቸውንና የጓደኞቻቸውንና የዘመዶቻቸውን ቤት ይለያሉ፡፡ ብዙ የእንስሳትና የአትክልት ዓይነቶችን ያውቃሉ፡፡ በገንዘብ የሚገዙ ነገሮችንም እንዳሉ ያውቃሉ፡፡ እነዚህ ትምህርት ቤት ከመሄዳቸው በፊት ከሚማሯቸው ብዙ ነገሮች መካከል ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ ይህንን ሁሉ የሚማሩት የት ነው? እለት ከእለት ከቤተሰቦቻቸው እና ከጎረቤቶቻቸው ጋር በሚያደርጉት ግንኙነት ሲሆን አብዛኛውን ነገሮች የሚማሩት ደግሞ ወላጆቻቸው ወንድሞቻቸውና እህቶቻቸው የሚያደርጉትን ነገር እየተመለከቱና እንደ እነርሱም ለማድረግ እየሞከሩ ነው፡፡ ይሁንና ልጆች ከቤተሰቦቻቸው የሚያገኙት ትምህርት ፈር በያዘ መልኩ ወይንም በበቂ ሁኔታ አይደለም፡፡ አባት ብዙ ጊዜውን ሥራ ቦታ ስለሚያሳልፍ ከልጆቹ ጋር  የሚያገና ኝበት ጊዜ ውስን ነው፡፡ እናት ደግሞ በተጨማሪ የቤት ውስጥ ሥራዎች ስለሚኖሩባት ሕፃናቱን በበቂ ሁኔታ ለማስተማር በቂ ጊዜ አይኖራትም፡፡ ስለሆነም ሕፃናቱ ቤተሰባቸውን በመመልከትና ከእነሱ በመኮረጅ እን ደቤተሰቦቻቸው ይሆናሉ፡፡ ልጆች ከቤተሰባቸው የሚማሩበት ዋናው መንገድ ይህ ነው፡፡ ሌሎችም የቤተ ሰቡ አባላት በቂ ጊዜ ስለማይኖራቸው ሕፃናትን በበቂ ሁኔታ ለማስተማር ክፍለ-ጊዜን ለማዘጋጀት ይቸገ ራሉ፡፡ ስለዚህ አንድ ሰው ጊዜውን ለሕፃናት ትምህርት ለማዋል ሲወስን ለማህበረሰቡ ትልቅ ዋጋ ያለው አገልግሎት እያበረከተ ነው፡፡ በተጨማሪም የሕፃናት ትምህርት ለማካሄድ በሚወሰንበት ጊዜ ልጆች በቀላሉና በቶሎ ሊማሩ የሚችሉበት እድሜ ከጥቅም ላይ አዋለ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ በሕፃናቱ ቤተሰቦችና በአስተማሪዎቻቸው መካከል ያለው ግንኙነት በጣም አመርቂ ሊሆን ይገባል፡፡ ቤተሰብ ልጆቻቸውን በአግ ባቡ እንደሚያስተምሩላቸው በአስተ ማሪዎቹ ላይ አመኔታ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ በትምህርት ክፍለ-ጊዜ ውስጥ ሕፃናቱ ወላጆቻቸው በሚፈልጉት መንፈሳዊ ትምህርቶችና ዓላማዎች መሰረት መታነጽ አለባ ቸው፡፡ ወላጆችም ደግሞ ለልጆቻቸው ጥሩ አርዓያ በመሆንና በትምህርት ክፍለ-ጊዜው የተማሩትን በተግባር ላይ እንዲያውሉ በአስተማሪውና በቤተሰብ መካከል ጥብቅና በፍቅር የተሞላ ዘላቂ ግንኘ ነት መመስረት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

- ልጆች በቤት ውስጥ ከሚማሩት ነገሮች መካከል ጥቂት ምሳሌዎችን ይጥቀሱ

________________________________________

________________________________________

________________________________________

- ልጆች ከቤተሰቦቻቸው የእለት ከእለት ኑሮ የሚማሩት እንዴት ነው?

________________________________________

________________________________________

________________________________________

- ቤተሰቦች ልጆችን ለማስተማሪያ የሚጠቀሙበት ዋናው ዘዴ ምንድን ነው?

________________________________________

________________________________________

* በሕፃናት ቤተሰቦችና በባሃኢ የሕፃናት አስተማሪ መካከል በጣም የጠበቀ ግንኙነት መፍጠር የሚያስፈልገው ለምንድን ነው?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

# ምዕራፍ 14 ከቤተሰቦች ጋር የሚኖር ግንኙነት

በመደበኛ የቀለም ትምህርት ቤቶች ውስጥ በሚያስተምሩ አስተማሪዎችና በተማሪዎቻቸው ቤተሰቦች መካከል ያለው ግንኙነት ጥሩ አይደለም:: የሚያሳዝነው ይህ ግንኙነት በባሃኢ ሕፃናት አስተማሪዎችና በተማሪዎቻቸው ቤተሰቦች መካከል ለሚኖረው ግንኙነት እንቅፋት መሆኑ ነው:: በአብዛኛዎቹ መደበኛ ትምህርት ቤቶች ወላጆችና አስተማሪዎች እርስ በእርስ ያላቸው ግንኙነት ያለመተማመንና የመወነጃጀል ነው:: ስለሆነም ልጆቹ ስለሚያሳዩት ስርዓት አልበኝነት በወላጆች ምክንያት ነው ሲሉ አስተማሪዎች ያማርራሉ:: ወላጆች ደግሞ ልጆቻቸውን እንዴት ማስተማር እንደሚ ገባቸው አስተማሪዎቹ አያውቁም ሲሉ ያማርራሉ:: ባሃኢ የሕፃናት አስተማሪዎች ይህንን ተስፋፍቶ የሚገኝ አስከፊ ሁኔታን ለማስወገድ የተቻላቸውን ሁሉ ማድረግ እንደሚገባቸው ግልጽ ነው:: የአንድ ባሃኢ ተግባር ስህተታቸውን ከማጉላት ታቅቦ ይቅርባይ መሆንና ረዳታቸው መሆን ነው:: ስለዚህ አስተማሪው ከሕፃናቱ ወላጆች ጋር በመቀራረብ ስለ ሕፃናቱ የቤትና የክፍል ውስጥ ባሕሪ በየጊዜው ለመመካከር ጥረት ማድረግ አለበት:: ከወላጆች ጋር ተደጋጋሚና የወዳጅነት ውይይቶች የማድረግ ባህል ሊዳብር ይገባል:: በእነዚህ ወይይቶች የሕፃናቱ ባሕሪና የትምህርት ውጤት በየጊዜው በመደበኛነት መገ ምገምና መበረታታት አለበት:: ከዛም ባደረጉት ምክክር ያገኙ ትን ሃሳቦች የልጁ ባህሪንና የትምህርት ውጤቱን የበለጠ አመርቂ ለማድረግ እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ ሊወስኑ ይችላሉ::

በእነዚህም ቅድመ ሁኔታዎችና በታላቅ ብልሃት የልጁ ድክመቶች ላይ መወያየት ይቻላል:: ዋናው ዓላማም በቤተሰብና በአስተማሪው መካከል ገንቢ የግንኙነት መንገድ መፍጠሪያ መንገድ ለማግኘት ሊሆን ይገባል:: ልጁም ያሉበትን ድክመቶች ለማሻሻል ይረዳዋል::

በቤተሰቦችና በአስተማሪዎች መካከል ሊኖር የሚገባ ግንኙነት በጣም ሰፊ ርዕስ በመሆኑ በዚህ ክፍል ሙሉ ለሙሉ ለመሸፈን አይቻልም:: የሕፃናት ትምህርት ማህበረሰቡ እንዲዳብር አስተዋጽኦ ለማድረግ እንዴት መጠቀም እንደሚቻል ቀስ በቀስ ይማራሉ:: አሁን ግን ገና ጀማሪ በመሆንዎ ብዙ ነገር ከእርስዎ አይጠበቅም፤ ለአሁኑ ከእርስዎ የሚጠበቀው ዋና ነገር ምሳሌ የሚሆን የሕፃናት ትምህርት ክፍለ-ጊዜ መክፈት ነው:: በዚህም የማህበረሰብዎ ሰዎች የሚሰጠውን ትምህርት ጥራትና በሚያስተምሯቸውም ሕፃናትን መሻሻል በአድናቆት እንዲመለከቱ ሊያደርጓቸው ይገባል:: ይሁንና ከላይ እንደተጠቀሰው እዚህ ውጤት ላይ ብቻዎን ለማድረስ አይችሉም:: ከሕፃናቶቹ ቤተሰብ ጋር ለመወያየትና በአገልግሎትም እንዲተባበሩዎ የሚያስችልዎትን አጋጣሚዎች ሁሉ መጠቀም አለብዎ::

ከቤተሰቦች ጋር የሚያደርጓቸውን እነዚህን ውይይቶች ለመጀመር ሕፃናት እንዲያዳብሯቸው የሚፈልጓቸውን መንፈሳዊ ባህሪያት ይዘርዝሩ:: እያንዳንዱን ባሕሪ የሚደግፍ ጥቅስም ከቅዱሳን ጽሑፎች ያግኙ:: በተጨማሪም አብዛኞቹን ጥቅሶች ሕፃናቱን ለማስተማሪያ በተዘጋጀው ርዕስ ምዕራፍ ውስጥ ያገኙአቸዋል:: ከሕፃናቱ ቤተሰቦች ጋር ለሚያደርጉት ውይይት እነዚህን ባህሪያት ለማዳበር ስለሚችሉባቸው መንገዶች መመካከር ያስፈልጋል:: የሚሰነዝሯቸው አስተያየቶች ገንቢ መሆን አለባቸው በምንም ዓይነት ሁኔታ አፍራሽ ሐሳቦችንና ትችት ላለመሰንዘር መጠንቀቅ እንዳለብዎ ደግመው ያስታውሱ::

***REFERENCES***


1. Bahá'ulláh, "Bahá'i  Education, A Compilation", P.9 (1977 U.S. Eddition)

2. 'Abdu'l-Bahá, "Selections from the Writings of 'Abdul-Bahá, p.133 (1978 Bahá'i World Centre Edition)

3. 'Abdu'l-Bahá "Bahá'i Education, A Compilation", p.33

4. Bahá'u'lláh, "Gleanings from the Writings of Bahá'u'lláh", CXXIII, p. 260 (1976 U.S. Edition)

5. 'Abdu'l-Bahá, "Selections from the Writings of 'Abdul-Bahá, p.142

6. Bahá'u'lláh, "Gleanings from the Writings of Bahá'u'lláh, CXXVIII, p. 277

7. Bahá'u'lláh, "Synopsis and Codification of the Kitab-i-Aqdas", p.12

8. Bahá'u'lláh, "Gleanings from the Writings of Bahá'u'lláh", CLIII, p. 325-326

9. Bahá'u'lláh, "The Hidden Words", No. 9, Arabic

10. Bahá'u'lláh, "Geanings from the the Writings of Bahá'u'lláh", CXXVIII, p. 275

REFERENCES


1. ‘Abdu’l-Bahá, “Tablets of ‘Abdu’l-Bahá”, Vol III, P. 579

2. ‘Abdu’l-Bahá, “Bahá’i Prayers”, (U.S. 1985 Edition) P. 37

3. ‘Abdu’l-Bahá, “The Promulgation of Universal Peace”, (U.S. 1982 Edition) P. 52

4. Ibid., pp. 35-36

5. Bahá’u’lláh, “Gleanings from the Writings of Bahá’u’lláh”, CXXXII, (U.S. 1976 Edition) P. 288

6. ‘Abdu’l-Bahá, “Bahá’i Prayers”, p. 35

7. Bahá’u’lláh, “The Hidden Words”, No. 1 (Arabic)

8. Bahá’u’lláh, “Bahá’i Prayers”, pp. 144-145

9. Bahá’u’lláh, “Gleanings from the Writings of Bahá’u’lláh”, CXVIII, p. 250

10. ‘Abdu’l-Bahá, “Bahá’i Prayers”, p. 152

11. Ibid., pp. 36-37

12. Bahá’u’lláh, “Hidden Words”, No. 3 (Persian)

13. Bahá’u’lláh, “Gleanings from the Writings of Bahá’u’lláh”, CXVII, p. 250

14. Bahá’u’lláh, “The Advent of Divine Justice”, (U.S. 1984 Edition) p. 26

15. Bahá’u’lláh, “Gleanings from the Writings of Bahá’u’lláh”, CXV, p. 246

16. Bahá’u’lláh, ‘The Hidden Words”, No. 42 (Arabic)

17. Bahá’u’lláh, “Tabelts of Bahá’u’lláh”, p. 71

18. Bahá’u’lláh, “Gleanings from the Writings of Bahá’u’lláh”, CXXXVI, p. 297

19. ‘Abdu’l-Bahá, “Bahá’i Prayers”, pp. 37-38

20. Bahá’u’lláh, “The Hidden Words” No. 49 (Persian)

21. Bahá’u’lláh, “Gleanings from the Writings of Bahá’u’lláh”, CLVI, p. 334

22. Bahá’u’lláh, “The Hidden Words”, No. 48 (Arabic)

23. Ibid., No. 9 (Arabic)

24. Bahá’u’lláh, “The Advent of Divine Justice”, p. 82

# *REFERENCES*


1. ‘Abdu’l-Bahá, “Selections from the Writings of ‘Abdu’l-Bahá”, No. 115, p. 139

2. Ibid., No. 111, , p. 137

3. Ibid., p. 136

4. Ibid., p. 125